ቁርአን እና እውቀት



በኡስታዝ ወሒድ ዑመር

ነቅልና አቅል በቁርአን እሳቤ

ክፍል አንድ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

መግቢያ
ሁለት እሳቤዎች እውቀት ሆነው ለሰው ልጆች ይጠቅማሉ፣ አንዱ ነቅል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አቅል ነው፡፡ “ነቅል” نقل አላህ በነቢያቱ ለሰው ልጆች የሚያስተላልፈው ግልጠተ-መለኮት*Revelation* ሲሆን፣ አቅል عقل ደግሞ አላህ ለሰው ልጆች እንዲያመዛዝኑ፣ እንዲያስተነትኑ፣ እንዲያስተውሉ፣ እንዲመራመሩ የሰጠው አመክንዮ*Reason* ነው፣ እነዚህን ሁለት እሳቤዎች ጥልልና ጥንፍፍ ባለ መልኩ እንዳስሳቸው፡-

እሳቤ አንድ
ነቅል
አላህ በነቢያቱ ለሰው ልጆች የሚያስተላልፈው ግልጠተ-መለኮት ወህይና ተንዚል ይባላል፡-
ነጥብ አንድ
ወህይ
ወህይ وَحْيٌ የሚለው ቃል አውሃ أَوْحَى ማለትም ገለጠ ከሚል ግስ የመጣ ሲሆን ትርጉሙ ግልጠት አሊያም ግህደት የሚል ፍቺ አለው፣ ወህይ የሚለው ቃል በቁርአን 6 ጊዜ ተወስቷል፡-11:37 20:114 21:45 23:27 42:51 53:4 አላህ የወይህ ባለቤት ሲሆን ከነቢያች በፊት ላሉት ነቢያትና ለነቢያች መጽሐፍን የሚገልጠው እርሱ ነው፡-
4:163 እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደ ነበሩት ነቢያት *እንዳወረድንእَوْحَيْنَا፣ ወደ አንተም *አወረድን أَوْحَيْنَا፤ ወደ ኢብራሂምም፣ ወደ ኢስማዒልም፣ ወደ ኢስሐቅም፣ ወደ ያዕቆብም፣ ወደ ነገዶቹም ወደ ዒሳም፣ ወደ አዮብም፣ ወደ ዩኑስም፣ ወደ ሀሩንና ወደ ሱለይማንም *አወረድንእَوْحَيْنَا፤ ለዳዉድም ዘቡርን ሰጠነው።

አውሃይና أَوْحَيْنَا ገለጥን አሊያም አወረድን የሚለው ቃል የመጀመሪያ መደብ ያለቀ አላፊ ግስ ሆኖ የመጣ ሲሆን አላህ በቁርአን 24 ጊዜ አውሃይና ብሏል፣ እንዲሁ ኑሂ نُوحِي የምንገልጥ አሊያም የምናወርድ የሚለው ቃል የመጀመሪያ መደብ ያላለቀ አላፊ ግስ ሆኖ የመጣ ሲሆን አላህ በቁርአን 5 ጊዜ ኑሂ ብሏል፡-
21:25 ከአንተ በፊትም፣ እነሆ ከኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ፣ በማለት ወደርሱ *የምናወርድለትنُوحِي ቢሆን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም።
12:109 ካንተ በፊትም ከከተሞች ሰዎች ወደነርሱ ራዕይ *የምናወርድላቸው نُوحِي የሆኑን ወንዶችን እንጂ አልላክንም፤
21:7 ከአንተም በፊት ወደነሱ *የምናወርድላቸው نُوحِي የኾኑ እንጂ ሌላን አልላክንም፤
16:43 ከአንተም በፊት ወደነሱ ወሕይን *የምናወርድላቸውን نُوحِي ሰዎችን እንጂ፣ ሌላን አልላክንም፤
3:44 ይኽ ወደ አንተ *የምናወርደዉ نُوحِيهِ የሆነ ከሩቅ ወሬዎች ነዉ፤

ምንኛ ያማረ ቃል ነው? አላህ እውነት ተናገረ፣ ጥንት ለነቢያት ተውሂድን ሲገልጥ የነበረው አንዱ አምላክ ዘመኑ ሲደርስ ቁርአንን በነቢያች ላይ ገልጦታል፡-
42:3 እንደዚሁ አሸናፊው፣ ጥበበኛው አላህ ወዳንተ *ያወርዳል يُوحِي ፤ ወደነዚያም ከአንተ በፊት ወደነበሩት ሕዝቦች፣ አውርዷል።

ነጥብ ሁለት
ተንዚል
ተንዚል تَنزِيل የሚለው ቃል ነገዘለ نَزَّلَ ማለትም አወረደ አሊያም ገለጠ ከሚል ግስ የመጣ ሲሆን *የተወረደ* አሊያም *የተገለጠ* ማለት ነው፣ ተንዚል የሚለው ቃል በቁርአን 15 ጊዜ ሰፍሮ ይገኛል፣ ለናሙና ያክል ይህ በቂ ነው፡- 41:2 41:42 46:2 32:2 5:2 39:1 40:2 20:4
ይህም ቃል ወህይ ከሚለው ቃል ጋር ተለዋዋጭ ሆኖ የሚመጣ ቃል ነው፣ ቁርአን አሊያም ሌሎች ኪታቦች ወረዱ ሲባል በወረቀት የተጻፈ ጥቅል ወረደ ማለት ሳይሆን የአላህ ንግግር ተገጠለ ማለት ነው፣ ምክንያቱም ወረቀት ልብ ላይ ሊወርድ አይችልም ባይሆን ወህይ እንጂ፡-
6:7 ባንተም ላይ **በወረቀት የተጻፈን መጽሐፍ** ባወረድንና በእጆቻቸው በነኩት ኖሮ እነዚያ የካዱት ሰዎች «ይህ ግልጽ ድግምት እንጅ ሌላ አይደለም» ባሉ ነበር፡፡
2:97 ለጂብሪል ጠላት የኾነ ሰው በቁጭት ይሙት በላቸው፡፡ እርሱ ቁርኣኑን ከበፊቱ ለነበሩት መጻሕፍት አረጋጋጭ ለምእመናን መሪና ብስራት ሲኾን በአላህ ፈቃድ **በልብህ** ላይ አውርዶታልና፡፡
26:192-194 እርሱም ቁርኣን በእርግጥ ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው፡፡ እርሱን ታማኙ መንፈስ አወረደው፤ ከአስጠንቃቂዎቹ ትኾን ዘንድ *በልብህ* ላይ አወረደው፡፡

አንዘልናሁ ٱنْزَلْنَاهُ አወረድነው የሚለው ቃል አንድ ጊዜ መውረድን ለቁርአን ከተጠበቀው ሰሌዳ ወደ ቅይቢቱ ሰማይ መውረድና ለሌሎቹ መጽሐፍት መውረድ አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን 16 ጊዜ ተጠቅሷል፣ ነገዘልናሁ وَنَزَّلْنَاهُ አወረድነው የሚለው ቃል ደግሞ ቀስ በቀስ መውረድን የሚያሳይ ሲሆን በነቢያን ቀልብ ላይ የወረደውን ቁርአን ለማመልከት አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን 12 ጊዜ ተጠቅሷል፣ ይህ የስነ-ቋንቋ ሙግት ታሳቢና ዋቢ ያደረገ ነው፡-
57:25 መልክተኞቻችንን በግልጽ ማስረጃዎች በእርግጥ ላክን፤ ሰዎችም በትክክል ቀጥ እንዲሉ መጽሐፎችንና ሚዛንን ወደነርሱ አወረድን وَأَنْزَلْنَا ።
2:213 አላህም ነቢያትን አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች አድርጎ ላከ፡፡ ከእነርሱም ጋር መጻሕፍትን በሰዎቹ መካከል በዚያ በርሱ በተለያዩበት ነገር ይፈርድ ዘንድ በእውነት አወረደ وَأَنْزَلَ፡፡

ቁርአንን ሆነ የቀድሞ መጽሐፍት ያወረደው የዓለማቱ ጌታ አላህ ነው፡-
2:4 ለእነዚያም ወደ አንተ በተወረደው ٱنْزِلَ እና ከአንተ በፊትም በተወረደው ٱنْزِلَ የሚያምኑ በመጨረሻይቱም ዓለም እነርሱ የሚያረጋግጡ ለኾኑት መሪ ነው፡፡
4:60 ወደ እነዚያ፣ እርሱ ባንተ ላይ በተዋረደው ٱنْزِلَ እና ከአንተ በፊትም በተወረደው ٱنْزِلَ አምነናል ወደሚሉት አላየህምን?
4:162 ግን ከነርሱ ውስጥ በዕውቀት የጠለቁትና ምእምናኖቹ በአንተ ላይ በተወረደው ٱنْزِلَ እና ከአንተም በፊት በተወረደው ٱنْزِلَ መጽሐፍ የሚያምኑ ሲኾኑ፤
3:3 ከርሱ በፊት ያሉትን መጻሕፍት የሚያረጋግጥ ሲሆን መጽሐፉን ባንተ ላይ ከፋፍሎ በዉነት አወረደ نَزَّلَ። ተዉራትንና ኢንጅልንም አውርዷል وَأَنْزَلَ።

ኢንሻላህ በሚቀጥለው ክፍል ስለ አቅል እሳቤ እንዳስሳለን።

ነቅልና አቅል በቁርአን እሳቤ

ክፍል ሁለት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው::

እሳቤ ሁለት
አቅል
አላህ ለሰው ልጆች እንዲያመዛዝኑ፣ እንዲያስተነትኑ፣ እንዲያስተውሉ፣ እንዲመራመሩ የሰጠው አመክንዮ*Reason* ነው፣ ይህ አመክኖ አቅል عقل ይባላል፣ አቅል የቀጥታ ትርጉሙ *ግንዛቤ* ማለት ነው፣ አላህ ስለ አቅል በተለያየ ጉዳይ ላይ ይነግረናል፡-
ነጥብ አንድ
ቁርአንና አቅል
አላህ ቁርአን ያወረደው የግንዛቤ ባለቤቶች በአቅላቸው አስተንትነው እንዲገነዘቡ ነው፡-
12:2 በእርግጥ እኛ ትገነዘቡ تَعْقِلُون ዘንድ ዐረብኛ ቁርአን ሲሆን አወረድነው።
43:3 በእርግጥ እኛ ትገነዘቡ تَعْقِلُون ዘንድ ዐረብኛ ቁርአን አደረግነው።
2:242 እንደዚሁ አላህ አንቀጾቹን ትገነዘቡ تَعْقِلُون ዘንድ ለናንተ ያብራራላችኋል::
21:10 ክብራችሁ በውሥጡ ያለበትን መጽሐፍ ወደናንተ በእርግጥ አወረድን፤ አትገነዘቡምን? أَفَلَا تَعْقِلُون.

ነጥብ ሁለት
እንስሳና አቅል
ሰው ከእንስሳ የሚለውየው በአቅሉና በቀውሉ ነው፣ ያ የተገነዘብውን ስሜትና ሃሳብ በአንደበቱ መግለጹ ነው፣ ሰው አላህ ያወረደውን ቁርአንና በፍጥረት ውስጥ ያሉትን ነገሮች በአቅሉ ካልተመራመረና ካላስተነተነ እንደ እንስሳ ነው፡-
25:44 ይልቁንም አብዛኛዎቻቸው የሚሰሙ፣ ወይም የሚገነዘቡ يَعْقِلُون ፣ መሆናቸውን፣ ታስባለህን? እነርሱ እንደ እንሰሳዎች እንጂ ሌላ አይደሉም፣
2:171 የነዚያም የካዱት ምሳሌ እንደዚያ ድምጽንና ጥሪን በስተቀር ሌላን በማይሰማ እንስሳ ላይ እንደሚጮህ ብጤ ነው:: እነርሱ ደንቆሮዎች፣ ዲዳዎች፣ ዕውሮች ናቸው፤ ስለዚህ እነርሱ አይገነዘቡም يَعْقِلُون لَا::
8:22 ከተንቀሳቃሾች ሁሉ አላህ ዘንድ መጥፎ ተንኮለኞች እነዚያ የማይገነዘቡት يَعْقِلُون لَا ደንቆሮዎቹ ዲዳዎቹ ናቸው።
10:42 አንተ ደንቆሮዎችን የማይገነዘቡ يَعْقِلُون لَا ቢኾኑም ታሰማለህን?
23:80 የሌሊትና የቀን መተካካትም የእርሱ ነው:: አትገነዘቡምን? أَفَلَا تَعْقِلُون.

ነጥብ ሶስት
ህዋስና አቅል
ህዋሳት የሚባሉት መስሚያ፣ ማያም፣ ልብም ናቸው፣ መስሚያ፣ ማያም፣ ልብም እንሰሳዎች አላቸው ነገር ግን የሚያገናዝቡበት አቅል የላቸውም፣ ሰውም የሚያገናዝብበትን አይን፣ ጆሮ፣ ልብ ካልተጠቀመበት አላህ ይጠይቀዋል፣ አላህ የሰጠውን የማገናዘቢያ አቅል ካልተጠቀመ ይቀጣዋል፡-

67:10 የምንሰማ ወይንም የምናገናዝብ نَعْقِلُ በነበርን ኖሮ በነዳጅ እሳት ጓዶች ውስጥ ባልሆን ነበር ይላሉ።
17:36ለአንተም በርሱ *ዕውቀት* የሌለህን ነገር አትከተል፤ መስሚያ፣ ማያም፣ ልብም፣ እነዚህ ሁሉ ባለቤታቸው ከነሱ ተጠያቂ ነውና።አታውቁምን?

ለዚህ ነው አላህ አቅላችንን መጠቀም እንዳለብል ሲነግረን አታውቁምን? አያስተውሉምን? አትገነዘቡምን? አታስተነትኑምን? አታስተነትኑምን? አትሰሙምን? አታዩምን? አትመለከቱምን? የሚለን፡-

21:10 ክብራችሁ በውሥጡ ያለበትን መጽሐፍ ወደናንተ በእርግጥ አወረድን፤ አታውቁምን?
30:8 በነፍሶቻቸው ሁኔታ አያስተውሉምን ? أَوَلَمْ يَتَفَكَّرُوا
56:62 የፊተኛይቱንም አፈጣጠር በእርግጥ አውቃችኋል፤ አትገነዘቡምን?
6:50 «ዕውርና የሚያይ ይስተካከላሉን አታስተነትኑምን?» በላቸው፡፡
28:71 «አላህ በእናንተ ላይ ሌሊትን እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ ዘውታሪ ቢያደርገው ከአላህ ሌላ ብርሃንን የሚያመጣላችሁ አምላክ ማነው አትሰሙምን?» በላቸው፡፡
31:20 አላህ በሰማያት ያለውንና በምድርም ያለውን ሁሉ ለናንተ ያገራላችሁ ጸጋዎቹንም ግልጽም ድብቅም ሲሆኑ የሞላላችሁ፣ መሆኑን አታዩምን?
51:21 በነፍሶቻችሁም ውስጥ ምልክቶች አሉ ፤ ታዲያ አትመለከቱምን?

ነጥብ አራት
የግንዛቤ ባለቤትና አቅል
አላህ የሚያገናዝቡ ሰዎችን ልሊቀውሚን የዕቂሉን يَعْقِلُونَ لِقَوْمٍ የሚያገናዝቡ ሕዝቦች ይላቸዋል፡-
13:4 ለሚያገናዝቡ ሕዝቦች يَعْقِلُونَ لِقَوْمٍ ታምራት አለበት።
16:12 ለሚያገናዝቡ ሕዝቦች يَعْقِلُونَ لِقَوْمٍ በእርግጥ ታምራቶች አሉ።
29:35 በእርግጥ ለሚያገናዝቡ يَعْقِلُونَ لِقَوْمٍ ሰዎች ከርሷ ግልጽ ምልክትን አስቀረን።
30:24 ለሚያገናዝቡ ሕዝቦች يَعْقِلُونَ لِقَوْمٍ ታምራቶች አሉበት።
30:28 ለሚያገናዝቡ ሕዝቦች يَعْقِلُونَ لِقَوْمٍ አንቀጾችን እንገልጻለን።
45:5 ለሚያገናዝቡ ሕዝቦች يَعْقِلُونَ لِقَوْمٍ ማስረጃ አልሉ።
16:67 ለሚያገናዝቡ ሕዝቦች يَعْقِلُونَ لِقَوْمٍ እርግጠኛ ምልክቶች አሉ፡፡

አላህ ቁርአንን ያወረደው የአእምሮ ባለ-ቤቶችም አንቀጾቹን እንድናስተነትን ነው፡-
38:29 ይህ ወዳንተ ያወረድነው ብሩክ መጽሐፍ ነው፡፡ አንቀጾቹን እንዲያስተነትኑና لِيَدَّبَّرُوا የአእምሮ ባለ ቤቶችም እንዲገሰጹ አወረድነው፡
47:24 ቁራንንም አያስተነትኑምን?أَفَلَا يَتَدَبَّرُونَ በውነቱ በልቦቻቸው ላይ ቁልፎቿ አልሉባትን?
4:82 ቁርአንን አያስተነትኑምን? أَفَلَا يَتَدَبَّرُونَ ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ፣ በርሱ ውስጥ ብዙ መለያየት ባገኙ ነበር።

23:68 የቁርኣንን ንግግሩንም አያስተነትኑምን أَفَلَمْ يَدَّبَّرُوا ወይስ ለመጀመሪያዎቹ አባቶቻቸው ያልመጣ ነገር መጣባቸውን?

መደምደሚያ
96:1-5 አንብብ በዚያ ሁሉን በፈጠረው ጌታህ ስም። ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው ጌታህ ስም። አንብብ፤ ጌታህ በጣም ቸር ሲሆን፤ ያ በብዕር ያስተማረ፤ ሰውን ያልወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲሆን።

ኢቅራ اِقْرَأْ ማለትም *አንብብ* የሚለው ትዕዛዛዊ ግስ*imperative verb?* ሁለት ጊዜ መምጣቱ ሁለት ይዘት እንዳለው ምሁራን ይናገራሉ፡-
አንደኛ ይዘት *አንብብ በዚያ ሁሉን በፈጠረው ጌታህ ስም* ማለት መለኮታዊ መገለጥ የሆነው ቁርአንን እያንዳንዱን ሱራ በአላህ ስም መነበቡም ሲያመለክት ይህ ነቅል የሚባለውን የእውቀት ምንጭ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡-
7:52 *ከእውቀት* ጋርም የዘረዘርነው የሆነን መጽሐፍ ለሚያምኑ ሕዝቦች መመሪያና እዝነት ሲሆን፣ በእርግጥ አመጣንላቸው።
13:37 እንደዚሁ በዐረብኛ የተነገረ ፍትሕ ሲሆን አወረድነው፤ *ዕውቀቱ* ከመጣልህም በኋላ፥ ዝንባሌዎቻቸውን ብትከተል፥ ከአላህ ቅጣት ምንም ረዳትም ጠባቂም የለህም።
17:36ለአንተም በርሱ *ዕውቀት* የሌለህን ነገር አትከተል፤ መስሚያ፣ ማያም፣ ልብም፣ እነዚህ ሁሉ ባለቤታቸው ከነሱ ተጠያቂ ነውና።

ሁለተኛው ይዘት ደግሞ *አንብብ፤ ጌታህ በጣም ቸር ሲሆን፤ ያ በብዕር ያስተማረ፤ ሰውን ያልወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲሆን* ስለሚል በብዕር ማለትም በትምህርት የሚገበይ እውቀትን ማንበብ ያሳያል፣ አላህ ሰውን ያላወቀውን ሁሉ አሳውቆታል፣ ሳይንስ*science* የሚለው ቃል ሳይንሲያ ከሚል ከላቲን ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ እውቀት ማለት ነው፣ ይህ ቋንቋዊ ፍቺው ሲሆን ሙያዊ ፍቺው ደግሞ ህይወት ስላላቸውና ስለሌላቸው ነገሮች የሚያጠና የምርምር ዘርፍ ነው፣ ይህ የምርምር ጥናት እንደሚመጣ አላህ በቁርአን ነግሮናል፡-

41.53 እርሱም ቁርአን እውነት መሆኑ ለነርሱ እስከሚገለጽላቸው ድረስ፣ በአጽናፍቹ ውስጥና በራሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ታምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን፤ ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ መሆኑ አይበቃቸውምን?

27:92-93 ታምራቶቹን ወደፊት ያሳያችኋል፤ ታውቁታላችሁ በላቸው፤

ዛሬ የስነ-ምርምር ጥናት ተመራማሪዎች በአጽናፎች ያሉትን ፈለኮች፣ ፕላኔቶች፣ ምህዳሮች፣ ፍኖተ-ሃሊብ፣ ከላስተሮች፣ አድማሳትን መርምረው አይተዋል፣ ይህን ቁርአን በወረደበት ጊዜ የማይታሰብ ነው፣ ነገር ግን አላህ በአጽናፎች ያሉትን ታምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን ብሎ ቃል በገባው መሰረት ተፈጽሟል፣ ቁርአን እውነት መሆኑ በዚህ ይገለጻል። በራሶቻቸውም ያሉትን ስነ-አካል Physiology፣ ስነ-ልቦና Psychology፣ ስነ-መንፈስ Pneumatology፣ ስለ-ህይወት Biology፣ የወንድ ጾታ ጥናት Andrology፣ የሴት ጾታ ጥናት gynaecology መርምረው አይተዋል፣ ይህን ቁርአን በወረደበት ጊዜ የማይታሰብ ነው፣ ነገር ግን አላህ በራሶቻቸውም ያሉትን ታምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን፤ ታምራቶቹን ወደፊት ያሳያችኋል፤ ታውቁታላችሁ ብሎ በገባው ቃል መሰረት ዛሬ በዘመናችን አይተናል፣ አውቀናል። ቁርአን እውነት መሆኑ በዚህ ይገለጻል፤

ዋቢ መጽሐፍት፡-

1. Revelation and Reason in Islam
AvA.J. Arberry Volume 3.
2. Ibn Taymiyyah Fatawa 3:338-9 – Taken from “Ibn Taymiyyah Expounds on I

ሳይንስ የሚጻረረው ቁርአንን ወይስ ባይብልን?

ክፍል አንድ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

56:57-59 እኛ ፈጠርናችሁ፤ አታምኑምን? በማኅፀኖች የምታፈሱትን አያችሁትን? እናንተ ትፈጥሩታላችሁን? ወይስ እኛ ፈጣሪዎቹ ነን።

መግቢያ

ይህን እርሰ-ጉዳይ የመረጥኩበት ምክንያት የኢስላም ጠላቶች የአላህን ቃል በስነ-ምርምር ጥናት ለማጠልሸት ሲዳዱ በማዳመጤ ነው፣ ይኸውም የወንድ የዘር ሴል*sperm cell* የሚመነጠው ከየት ነው? በሚል የአላህን ቃል በስነ-ምርምር ጥናት ሲመዝኑ ማየቱ የሚያስገርም ሆኖ ሳለ ነገር ግን የራሳቸው መጽሐፍ በስነ-ምርምር ጥናት እንዴት እንዳልመዘኑት እጅጉን አስደመሙኝ፣ ለዛሬ የሁለትን መጽሐፍት ስለ የወንድ የዘር ሴል ምን እንደሚል በአላህ ፈቃድ ከቁርአን እንዳስሳለን፡-

1.የወንድ የዘር ሴል በቁርአን

ኑጥፋት ٱلنُّطْفَة የፍትወት ጠብታ*sperm-drop* ማለት ሲሆን አላህ በቁርአን 12 ጊዜ አውስቶታል፣ ከእርሱም በተጠበቀው መርጊያ በማህጸን የሰው ልጆችን ፈጥሯል፡-

16:4 ሰውን ከፍትወት ጠብታ ٱلنُّطْفَةِ ፈጠረው፤ ከዚያም እርሱ ወዲያውኑ ትንሣኤን በመካድ ግልጽ ተከራካሪ ይሆናል።

22:5 እላንተ ሰዎች ሆይ! ከመቀስቀስ፣ በመጠራጠር ዉስጥ እንደ ሆናችሁ አፈጣጠራችሁን ተመልከቱ፤ እኛም ከዐፈር ፈጠርናችሁ ከዚያም ከፍቶት ጠብታ ፣ ከዚያም ከረጋ ደም፣ ከዚያም ከቁራጭ፣ ስጋ ፍጥረትዋ ሙሉ ከኾነችና ሙሉ ካልሆነች ችሎታችንን ለናንተ ልንገልጽላችሁ ፈጠርናችሁ፤
40:67 እርሱ ያ ከዐፈር፣ ከዚያም ከፍትወት ጠብታ ፣ ከዚያም ከረጋ ደም፣ የፈጠራችሁ ነው። ከዚያም ሕጻናት አድርጎ ያወጣችኋል፤
23:12-13 በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው። ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍትወት ጠብታ አደረግነው።
53:45-46 እርሱም ሁለቱን ዓይነቶች ወንድና ሴትን ፈጠረ። ከፍትወት ጠብታ በማኅፀን ውስጥ በምትፈስስ ጊዜ፤
36:77 ሰውየው እኛ ከፍቶት ጠብታ የፈጠርነው መሆናችን አላወቀምን?

በተመሳሳይም አምሻጂን ቅልቅሎች*mixtures* በማለት ሰው የተፈጠረበትን የወንድ የዘር ሴልና የሴት እንቁላልን*egg cell* ያሳየናል፦
76:2 እኛ ሰዉን፥ በሕግ ግዳጅ የምንሞክረዉ ስንሆን፥ ቅልቅሎች ከሆኑ የፍትወት ጠብታ ፈጠርነዉ፤ ሰሚ ተመልካችም አደረግነዉ።

ታዲያ የወንድ የዘር ሴል*sperm-drop* ከየት ይመጣል ይላል? እውነት የኢስላም ጠላቶች እንደሚሉት ይሆን? ይህን ለማየት መጀመሪያ ጥቅሱን ረጋ ብለን እንመልከተው፦
86:5 ሰውም ከምን እንደተፈጠረ ይመልከት። ከተስፈንጣሪ ውሃ دَافِقٍ مَاءٍ፤ተፈጠረ። ከጀርባ الصُّلْبِ እና ከእርግብግቦቶች وَالتَّرَائِبِ መካከል يَخْرُجُ مِنْ የሚወጣ ከሆነ ውሃ።

ነጥብ አንድ
ተስፈንጣሪ ውሃ دَافِقٍ مَاءٍ
ማኢን ءٍمَاውሃ ማለት ሲሆን ዳፊቂን دَافِقٍ ደግሞ ተስፈንጣሪ*ejected* ማለት ነው፣ በጥቅሉ ተስፈንጣሪ ውሃ “Spurt of water” ማለት ነው፣ ይህም ቃል በቁርአን 1 ጊዜ ብቻ መጥቷል፣ ታዲያ የወንድ የዘር ሴል*sperm-drop* የሚል የት አለ? የሚል የለም፣ ከዚያ ይልቅ ተስፈንጣሪ ውሃ “Spurt of water” ነው የሚለው፣ ነጥቡ ከዚህ ነው የሚጀምረው፣ ስፐርም የሚመረተው ከቴስቲክል*Testicle* ሲሆን ይህ የሚገኘው በወንድ የዘር ከረጢት ሲሆን አላህ እየነገረን ያለው ግን ከጀርባ እና ከእርግብግቦቶች መካከል ስለሚወጣ ተስፈንጣሪ ውሃ ነው፣ ይህን የኢንግሊሽ ቁርአን ትርጉም ስፐርም አላሉትም፣ ከዛ ይልቅ እንደ አማርኛው ተስፈንጣሪ ፈሳሽ አሊያም ውሃ ብለው ነው ያስቀመጡት፦
“Created from a drop emitted” (Yusuf Ali).
“Created from a gushing fluid” (Pickthal).
“Water pouring forth” (Shakir).
ታዲያ ይህ ተስፈንጣሪ ውሃ ምንድን ነው? ስንል ከአስራ አንደኛውና በአስራ ሁለተኛው እርግብግቦችና ከጀርባ መካከል የሚገኝ ሲመን*semen* ነው፣ ይህም ሲመን የተገነባው ከሙቶ፦
1% ኮውፐር ግላንድ*Cowper gland*
2% ከቴስቲክል*Testicle*
22% ከፕሮስቴት*Prostate*
75% ከሰሚናል ቬሲክል*Seminal vesicle* ነው፣
ትልቁን የሲመን እመርታ የያዘው ሰሚናል ቬሲክል ሲሆን ይህም ፈሳሽ የሚወጣው ከጀርባ እና ከእርግብግቦች መካከል ነው፣ ዛሬ የስነ-ምርምር ጥናት ተመራማሪዎች ይህን ስነ-ህይወት Biology፣ የወንድ ጾታ ጥናት Andrology፣ የሴት ጾታ ጥናት gynaecology መርምረው አይተዋል፣ ይህን ቁርአን በወረደበት ጊዜ የማይታሰብ ነው፣ ነገር ግን አላህ በራሶቻቸውም ያሉትን ታምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን ታውቁታላችሁ ብሎ ቃል በገባው መሰረት ዛሬ በዘመናችን አውቀንማል፣ አይተንማል፦

41.53 እርሱም ቁርአን እውነት መሆኑ ለነርሱ እስከሚገለጽላቸው ድረስ፣ በአጽናፎቹ ውስጥና *በራሶቻቸውም* ውስጥ ያሉትን ታምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን፤

27:93 ምስጋና ለአላህ ነው፤ ታምራቶቹን ወደፊት ያሳያችኋል፤ ታውቂታላችሁ በላቸው፤

ነጥብ ሁለት
መካከል
بَيْن
በመቀጠል ሲተቹ፡- ቁርአን የወንድ የዘር ሴል*sperm-drop* ከጀርባ እና ከእርግብግብቶች ይወጣል ይላሉ፣ አይልም፣ አውቀው በይን بَيْن መካከል የሚለው መስተዋድድ ይዘሏታል፣ መካከል የሚለው ቃል በጣም ሊሰመርበት ይገባል፣ ለምሳሌ፡-
16:66 ለናንተም በግመል፣ በከብት፣ በፍየል፣ በእርግጥ መገምገሚያ አልላችሁ፤ በሆዶቹ ውስጥ ካለው ከፈርስና ከደም መካከል بَيْنِ ጥሩ ወተትን ለጠጪዎች ተዋጭ ሲሆን እናጠጣችኋለን።

ወተት ከፈርስና ከደም መካከል ይገኛል ማለትና ወተት ከፈርስና ከደም ይገኛል ማለት ሁለት የተለያየ ትርጉም እንዳለው ሁሉ በተመሳሳይ መልኩ ተስፈንጣሪ ውሃ ከጀርባ እና ከእርግብግብቶች መካከል ይወጣል ማለትና ተስፈንጣሪ ውሃ ከጀርባ እና ከእርግብግብቶች ይወጣል ማለት ሁለት የተለያየ ትርጉም አለው፣ ሱልብ صُّلْبِ ጀርባ*backbone*sacrum* ማለት ሲሆን ተራኢብ تَّرَآئِبِ ደግሞ እርግብግብቶች*pelvis or ribs* ማለት ነው፣ ይህ ነው እንግዲህ የቁርአን እውነታው፡-

21:18 በእርግጥ እውነትን በውሸት بِٱلْبَاطِلِ ላይ እንጥላለን፤ አንጎሉን ያፈርሰዋልም፤
34:49 እውነቱ መጣ፤ ውሸትም بِٱلْبَاطِلُ መነሻም መድረሻም የለውም ተወገደ በላቸው።
17:81 በልም፡-እውነት መጣ፣ ውሸትም بِٱلْبَاطِلُ ተወገደ፤ እነሆ ውሸት بِٱلْبَاطِلَ ተወጋጅ ነውና፣

ኢንሻላህ በከፍል ሁለት የወንድ የዘር ሴል በባይብል ያለውን እሳቤ እንመለከታለን፣ በስፐርምና በሲመን ዙሪዋ ዋቢ መጽሐፍትን ይመልከቱ፡-
1. Guyton, Arthur C. (1991). Textbook of Medical Physiology (8th ed.). Philadelphia: W.B. Saunders. pp. 890–891
2. Rosenthal, Sara. The Gynecological Sourcebook, McGraw-Hill Professional, 2003, p151

ሳይንስ የሚጻረረው ቁርአንን ወይስ ባይብልን?

ክፍል ሁለት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው::.

2. የወንድን የዘር ህዋስ በባይብል
ባይብል ምንም እንኳን የሰው ቃል ቢኖርበትም የመለኮት ቅሪት በውስጡ ያቀፈ መጽሐፍ ነው፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከቁርአን ጋር ተጓዳኝ የሆኑ እሳቤዎች አሉት፣ ከነዚህም መካከል ሰው ከጭቃ መፈጠሩ፣ ከፍትወት ፈሳሽ እንደ ወተት መፍሰሱ፣ ከብለድ ክሎት እንደ እርጎ መርጋቱ የመሳሰሉት ናቸው፡-
ኢዮብ 10፥9 እንደ ጭቃ አድርገህ እንደ ለወስኸኝ አስብ፤ ወደ ትቢያም ትመልሰኛለህን?
ኢዮብ 33፥6 እኔ ደግሞ ከጭቃ የተፈጠርሁ ነኝ።
ኢሳይያስ 64፥8 እኛ ጭቃ ነን አንተም ሠሪያችን ነህ፥ እኛም ሁላችን የእጅህ ሥራ ነን።
ኢዮብ 10፥10-11 በውኑ እንደ ወተት አላፈሰስኸኝምን? እንደ እርጎስ አላረጋኸኝምን? ቁርበትና ሥጋ አለበስኸኝ፥ በአጥንትና በጅማትም አጠንክርኸኝ።

ነገር ግን በተቃራኒው የሰው እጅ እንደገባበት ከሚያስታውቅበት አንዱ በቀጥታ ከስነ-አካል ጥናት*Physiology* ጋር መጻረሩ ነው፣ እነዚህን መጻረራት እስቲ እንመልከት፡-

መጻረር አንድ

ስፐርም የሚለው የእንግሊዚኛው ቃል ስፐርማ σπέρμα ከሚለው ግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ ዘር ማለት ነው፣ ይህም ቃል የወንድን የዘር ህዋስ ለመጠቀም የምንጠቀምበት ቃል ነው፣ በግሪክ ስፐቱአጀንት ባይብል ላይ የሰፈረው ቃል ይሁ ስፐርማ σπέρμα ነው፣ ባይብል ይህ ስፐር የሚወጣው ከወገብህ ነው ይለናል፡-

ሳሙኤል ካልዕ 7፥12 *ከወገብህ* የሚወጣውን *ዘርህን* σπέρμα ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ፥ መንግሥቱንም አጸናለሁ።

ነገሥት ቀዳማዊ 8፥19 ነገር ግን *ከወገብህ* የሚወጣው *ልጅህ* እርሱ ለስሜ ቤት ይሠራል፣

መዝሙረ ዳዊት 132፥11 *ከሆድህ ፍሬ* በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ።

ሐዋርያት ሥራ 2፥30 ነቢይ ስለ ሆነ፥ *ከወገቡም ፍሬ* በዙፋኑ ያስቀምጥ ዘንድ እግዚአብሔር መሐላ እንደ ማለለት ስለ አወቀ፥

እውን የወንድ ዘር ህዋስ የሚወጣው ከወገብ አሊያም ከሆድ ወይስ ከዘር-ቀረጢት*Testicle*? ባይብል ከስነ-አካል ጥናት*Physiology* በተቃራኒው ከወገብ ነው ይለናል፣ ሌላ ቦታ ደግሞ ከጉልበት ነው የሚወጣው ይላል፣ ይህ ታዲያ አይጣረስምን?

ዘፍጥረት 15፥4 ይህ አይወርስህም፤ ነገር ግን *ከጉልበትህ* የሚወጣው ይወርስሃል።

ዘጸአት 1፥5 ከያቆብ *ጉልበት* የወጡት ሰዎች ሁሉ ሰባ ነፍሶች ነበሩ፤ ዮሴፍም አስቀድሞ በግብፅ ነበረ።

መጻረር ሁለት

የዕብራይስጥ እደ-ክታባት ማለትም የሙት ባህር ጥቅል፣ ማሶሬቲክ፣ ሰማሪያት ወዘተ ደሃራይ ሲሆኑ ከግሪክ ስፐቱአጀንትን አይቀድሙም፣ ስፐቱአጀንት የተተረጎመበት ዕብራይስጡ የለም፣ ስፐቱአጀንት ቀዳማይ እደ-ክታብ ነው፣ በዚህ ባይብል ላይ ሴት ስፐርም σπέρμα አላት ይላል፣ ዛሬ የምናያቸው የኢንግሊሽ ሆነ የአምሃሪክ ባይብል ትርጉም መሰረቱ ስፐቱአጀንት እደ-ክታብ ነው፣ በዚህ ስፐቱአጀንት ላይ ኢጋርና ርብቃ ስፐርም σπέρμα እንዳላቸው ይናገራል፡-

ዘፍጥረት 16፥10 የእግዚአብሔር መልአክም፦ *ዘርሽን* σπέρμα እጅግ አበዛለሁ፥ ከብዛቱም የተነሣ አይቆጠርም አላት።

ዘፍጥረት 24፥60 ርብቃንም መረቁአትና፦ አንቺ እኅታችን፥ እልፍ አእላፋት ሁኚ *ዘርሽም* σπέρμα የጠላቶችን ደጅ ይውረስ አሉአት።

እውን ሴት እንቁላል ሴል እንጂ የዘር ህዋስ σπέρμα አላትን? ባይብል ከስነ-አካል ጥናት*Physiology* በተቃራኒው *ዘርሽን* σπέρμα ይለናል፣ ይህ ታዲያ አይጣረስምን?

መጻረር ሶስት

የሴት ጡት በግሪክ ማስቶስ μαστοῖς ይባላል፣ ይህም በኢንግሊሽ pap*female breast* ይባላል፣ ማስቶስ μαστοῖς ለሴቶች ብቻ የምንጠቀምበት ቃላት ነው፡-

ሉቃ11:27 ይህንም ሲናገር፥ ከሕዝቡ አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ። የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው *ጡቶች* μαστοὶ ብፁዓን ናቸው አለችው።

ሉቃ23:28-29 መካኖችና ያልወለዱ ማኅፀኖች ያላጠቡ *ጡቶችም* μαστοὶ ብፁዓን ናቸው የሚሉበት ጊዜ እነሆ ይመጣልና ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ።

የወንድ ደረት ደግሞ በግሪክ ስቴቶስ στῆθος ይባላል፣ ይህም በኢንግሊሽ chest*male breast* ይባላል፣ ስቴቶስ στῆθος ለለወንዶች ብቻ የምንጠቀምበት ቃላት ነው፡-

ሉቃ18:13 ቀራጩ ግን በሩቅ ቆሞ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሣ እንኳ አልወደደም፥ ነገር ግን። አምላክ ሆይ፥ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ እያለ *ደረቱን* στῆθος ይደቃ ነበር።

ዮሐ 13:25 እርሱም በኢየሱስ *ደረት* στῆθος እንዲህ ተጠግቶ። ጌታ ሆይ፥ ማን ነው? አለው።

ታዲያ ምን ልትለን ነው ደግሞ? ትሉ ይሆናል፣ ኢየሱስ የወንድ ደረት*ስቴቶስ* እንዳለው በወንጌል ላይ ቢሰፍርም የሴት ጡት*ማስቶስ* እንዳለው ደግሞ በራዕይ ላይ ሰፍሯል፣ ይንን አሳፋሪ ቃላት በኢንግሊሹ ሆነ በአምሃሪኩ ደረት እያሉ ቢደብቁትም በግሪኩ ግን የሴት ጡት ማስቶስ μαστοῖς ብሎ ይገልጸዋል፣ እውን ኢየሱስ ጡት አለውን?
ራእ 1:13 በመቅረዞቹም መካከል የሰው ልጅ የሚመስለውን አየሁ፥ እርሱም እስከ እግሩ ድረስ ልብስ የለበሰው *ደረቱንም* μαστοῖς በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ ነበር።

በሰፈሩት ቁና መሰፈር ይሉሃል ይሄ ነው፣ የባይብሉ እያረረባቸው የቁርአኑን ሲያማስሉ ምን ይሉታ

ቁርአን እና ታሪክ

ክፍል አንድ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡

መግቢያ
1. “ታሪክ”
“ታሪክ”history” ያለፈውን ክስተት የሚተርክ የምርምር ጥናት”study” እና አሰሳ”investigation” ነው፤ በታሪክ ጥናት ውስጥ ለታሪክ ምንጭ የሚሆኑ ሁለት መረጃዎች አሉ፣ አንደኛው ትውፊት”tradition” ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የስነ-ቅርስ ጥናት”archology” ነው፤ “ትውፊት” ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚተላለፍ ቅብብል ሲሆን “ስነ-ቅርስ ጥናት” ደግሞ በተለያየ ቁስ ላይ የተፃፉትን ፅሁፎች አስሶና ቆፍሮ የሚያቀርብ የታሪክ ምንጭ ነው፤ ትውፊት ሆነ ስነ-ቅርስ ባህል”culture” ላይ እና ስልጣኔ”civilization” ላይ መሰረት ያደረጉ ግምት”speculation” ናቸው፤ ይህን ግምት የታሪክ ምሁራን በስድስት ከፍለው ያስቀምጡታል፤ እነዚህም፡- 1. መቼ ተገኘ”date” 2. የት ተገኘ”localization” 3. ማን ደረሰው”authorship” 4. ቅድመ-ትንታኔ”analysis” 5. ስምምነት”integrity” 6. ዋጋነት”credibility” ናቸው።

መቼ ተገኘ፣ የት ተገኘ፣ ማን ደረሰው እና ቅድመ-ትንታኔ እነዚህ አራቱ ግምቶች ከፍተኛ ሂስ”higher criticism” ሲሆኑ አምስተኛው ግምት ስምምነት ደግሞ ዝቅተኛ ሂስ”lower criticism” እና ውጫዊ ሂስ”external criticism” ነው፤ በመቀጠል ስድስተኛው ግምት ዋጋነት ውስጣዊ ሂስ”internal criticism” ነው።

የታሪክ ምሁራን”Historians” እንደሚያስተነትኑት ታሪክ ታማኒነት”authenticity” ቢኖረውም እውነታነት”accuracy” ግን ላይኖረው ይችላል፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈው ቅብብል ሆነ በፅሁፍ የሰፈረው ነገር በትክክል ተላልፎና ሰፍሮ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ያ የተላለፈውና የሰፈረው ነገር ቅጥፈትም ሊሆን ይችላል፤ ለምሳሌ ኢየሱስ ከመቅደላዊት ማርያም ጋር ጋብቻ ፈፅሞ ሳራ የምትባል ልጅ እንደተወለደች በአራተኛ ክፍለ-ዘመን በፅሁፍ የተገኘ መረጃ”information” ቢሆንም የተፃፈው ነገር ግን እውነት ለመሆኑ ማስረጃ”evidence” ሊሆን አይችልም፤ ፀሃፊያን ቀጥፈውስ ቢሆን? ስለዚህ ጥንታዊያን መፅሐፍት ጥናት”Paleography” ያቀረበውን ፅሁፍ ሁሉ እንደ መረጃ ሊቀርብ ይችላል እንጂ እንደ ማስረጃ ሊሆን አይችልም፤ ሲጀመር ሊጤን የሚገባው ነገር ከኃላችን ያሉት ነገሮች ከፊታችን ካሉት ነገሮች ጋር በተመሳሳይ መልኩ ከአምስቱ የስሜት ህዋሳት ከመስማት፣ ከማየት፣ ከማሽተት፣ ከመቅመስ ባሻገር የሆኑ ነገሮች ናቸው፤ ሲቀጥል ከኃላችን ያሉት ነገሮች ሁሉ በትውፊት አልተላለፉም በፅሁፍም አልሰፈሩም፤ ታሪክ ጉዳዩን በትውፊት ሆነ በስነ-ቅርስ ጥናት አልደረሰበትም ማለት ጉዳዩ አልተፈፀመም ማለት አይደለም፤ ለምሳሌ ሙሳ ሰላም በእርሱ ላይ ይሁን ባህሩን በበትር ሲመታው እንደ ጋራ መቆሙና የእስራኤል ልጆች እንደተሻገሩ በዘፀአት እና በቁርአን ላይ ሰፍሮ ቢገኝም በታሪክ ግን ይህ ዘገባ አልተገኘም፤ ያ ማለት ዘፀአት እና ቁርአን ትክክል አይደሉም ማለት ሳይሆን ታሪክ ሁሉን አዋቂ እንዳልሆነ እና ታሪክ የሚያገኛቸው ምንጮች ከፊል እውቀት እንደሆነ እንረዳለን፤ ቅዱሳን መፅሐፍት ይቅርና ታሪክም እራሱ በታሪክ አይለካም፣ ምክንያቱን ታሪካውያን ያሰፈሩት ማህደር ከህዋሳቸው ባሻገር ያገኙት እንጂ የራሳቸው ስላልሆነ፤ ቅዱሳን መፅሐፍት ግን በእምነት የምንቀበላቸው የእምነት ማስረጃዎች ናቸው። ስለ ታሪክ ታሪካዊ ዳራ እነዚህን ዋቢ መፃህፍት ይመልከቱ፡-

1. Michael C. Lemon (1995). The Discipline of History and the History of Thought. Routledge. Page 201.
2. Michael J. Salevouris. The Methods and Skills of History: A Practical Guide (2010)

2. “ቁርአን”
“ቁርአን” የዓለማቱ ጌታ የአላህ ንግግር ነው፤ በቁርአን ከኃላችን እኛ ባልነበርንበት ቦታና ጊዜ የተከሰቱ ድርጊቶች፣ ከህዋሳችን ባሻገር ያሉት ነገሮች ሆኑ ወደ ፊት የሚከሰቱ ነገሮች “ገይብ” غَيْب “የሩቅ ነገር ምስጢር” ይባላል፤ “ገይብ” ሁለት ደረጃ አለው አንዱ አላህ ብቻ የሚያውቀው ሲሆን “ገይበል ሙጥለቅ” الغيب المطلق ሲባል፣ ሁለተኛው ደግሞ አላህ ለሚልከው ነብይ ሲያሳውቅ ያ የሚያሳውቀው የሩቅ ነገር ምስጢር “ገይቡን ኒስቢይ” الغيب النسبي ይባላል፡-
1. “ገይበል ሙጥለቅ”
አላህ ብቻ የሰማያትንንና የምድርን የሩቅ ነገር ምስጢር ያውቃል፤ አላህ ሩቆችን ሁሉ አዋቂ ነው፤ ከእርሱ በቀር ማንም አያውቃቸውም፡-
56:59 “የሩቅ ነገርም መክፈቻዎች” እርሱ ዘንድ ናቸው፤ “ከእርሱ በቀር ማንም አያውቃቸውም”::
16:77 በሰማያትና በምድርም ያለው “ሩቅ ምስጢር” የአላህ ነው፤
64:18 “ሩቁን ሚስጢር” ግልጹንም ሁሉ ዐዋቂው አሸናፊው ጥበበኛው ነው።
49:18 አላህ የሰማያትንንና የምድርን “ሩቅ ምስጢር” ያውቃል።
35:38 አላህ “የሰማያትንና የምድርን ምስጢር” በእርግጥ ዐዋቂ ነው፤
9:78 አላህም “ሩቆችን ሁሉ” በጣም ዐዋቂ መሆኑን አያዉቁምን?

2. “ገይቡን ኒስቢይ”
ለምሳሌ አላህ ለነቢያች በቁርአን የሩቅ ነገር ምስጢር አውርዷል፡-
72:26-27 እርሱ “ሩቁን ሚስጢር” ዐዋቂ ነው፣ “በሚስጢሩ” ላይ አንድንም አያሳውቅም። “ከመልክተኛ ለወደደው” ቢሆን እንጅ ለሌላ “አይገልጽም”፤
3:179 አላህም “ሩቁን ነገር የሚያሳውቃችሁ” አይደለም፤ ግን አላህ “ከመልክተኞቹ የሚሻዉን ይመርጣል”፤
34:48 ፡-ጌታዬ እውነትን “ያወርዳል”፤ “ሩቅ የኾኑትን ሚስጢሮች ሁሉ ዐዋቂ” ነው በላቸው።

“ነበእ” نَبَإ ِየሚለው ቃል “የሩቅ ወሬ” ማለት ሲሆን ይህም ወሬ ከህዋስ ባሻገር ያለውን ያለፈውን፣ ያሁኑንና የወፊቱን የሩቅ ነገር ሚስጥር የያዘ ዜና ነው፤ ይህንን ያለፈውን የሩቅ ወሬ በነቢያችን ላይ አላህ በመተረክ አውርዶታል፡-

ነጥብ አንድ
“እንተርካለን”
“ቀሰስ” قَصَص፡። የሚለው ቃል “ቀሰሰ” قصص “ተረከ” ከሚል ቃል የመጣችሲሆን “ትረካ” ማለት ነው፤ አላህ ሁሉን የሚያይ፣ ሁሉን የሚሰማና ሁሉን የሚያውቅ ስለሆነ ያለፈውን ክስተት “ነቁስሱ አለይከ” نَقُصُّ عَلَيْكَ“እንተርክልሃለን” በማለት ይናገራል፡-
40:78 ከአንተ በፊትም መልክተኞችን በእርግጥ ልከናል፤ ከእነርሱ በአንተ ላይ “የተረክንልህ አልለ”፤ ከእነርሱም በአንተ ላይ “ያልተረክነው አልለ” وَمِنْهُمْ مَنْ لَمْ نَقْصُصْ عَلَيْكَ ۚ مَنْ قَصَصْنَا عَلَيْكَ

አላህ ነብያችን ከመላካቸው በፊት የነበሩትን ነቢያት በስም ኢድሪስ፣ ኑህ፣ ኢብራሂም እያለ 24 ነቢያትን ለነቢያችን ተርኳል፣ ነገር ግን በነብያችን ያልተተረኩ ምናልባትም ቡድሃ፣ ክሪሽና፣ ኮንፊሽስ፣ ታኦ፣ ማህቢራ ነብያት ሊሆኑ ይችላሉ፤ አላህ እውቅና ስላልሰጣቸው ግን ነቢያት ናቸው አንልም፤ በተመሳሳይም አይደሉም አንልም። አላህ የተረካቸውን ነቢያት ማንነታቸው ምን ነበርና ምን አስተምረው ነበር የሚለውን አስፈላጊ ትምህርት በነብያችን ላይ ተርኮታል፡-
11:120 ከመልክተኞቹም “ወሬዎች” ተፈላጊውን ሁሉንም ልብህን በርሱ የምናረካበትን “እንተርክልሃለን” نَّقُصُّ عَلَيْكَ ۚ
11:100 ይህ የተነገረው ከከተሞቹ “ወሬዎች” ነው፤ ባንተ ላይ “እንተርክዋለን” نَقُصُّهُ ۚ

7:101 እነዚያ ከተሞች “ከወሬዎቻቸው” በአንተ ላይ “እንተርካለን” نَقُصُّ عَلَيْكَ.
20:99 እንደዚሁ በእርግጥ ካለፉት ወሬዎች በአንተ ላይ “እንተርካለን” نَقُصُّ عَلَيْكَ
12:3 እኛ ይህንን ቁርአን ወደ አንተ በማውረዳችን በጣም መልካም ዜናዎችን በአንተ ላይ “እንተርክልሃለን” نَقُصُّ عَلَيْكَ

ቁርአንና ታሪክ

ክፍል ሁለት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡

ነጥብ ሁለት
“እናወርዳለን”
“ወህይ” وَحْي የሚለው ቃል “አውሃ” أَوْحَى “ገለጠ” አሊያም “አወረደ” ከሚል ግስ የመጣ ሲሆን ትርጉሙ “ግልጠት” አሊያም “ግህደት” የሚል ፍቺ አለው፣ አምላካችን አላህ ለነቢያችን እሳቸው ባልነበሩበት ጊዜ የተከሰተውን የሩቅ ሚስጥር “ኑሒሂ ኢለይከ” نُوحِيهِ إِلَيْكَ “ወደ አንተ እናወርዳለን” በማለት ይተርካል፡-
11:49 ይህቺ “ከሩቅ ወሬዎች ናት”፤ ወደ አንተ “እናወርዳታለን” نُوحِيهَا፤
12:102 ይህ “ወደ አንተ የምናወርደው” نُوحِيهِ إِلَيْكَ ሲሆን ከሩቅ ወሬዎች ነው፤ አንተም እነርሱ በዩሱፍ የሚመኩሩ ሆነው፣ ነገራቸውን በቆረጡ ጊዜ “እነርሱ ዘንድ አልነበርክም”።
3:44 ይኽ “ወደ አንተ የምናወርደዉ” نُوحِيهِ إِلَيْكَ የሆነ “ከሩቅ ወሬዎች” ነዉ፤ መርየምንም ማን እንደሚያሳድግ ብርዖቻቸዉን ለዕጣ በጣሉ ጊዜ እነሱ ዘንድ “አልነበርክም”፤ በሚከራከሩም ጊዜ እነሱ ዘንድ “አልነበርክም”።
19:52 ከጡር ቀኝ ጎን በኩልም “ጠራነው” نَاجَيْنَاهُ ሲኾን አቀረብነው።
28:46 “በጠራነውም ጊዜ” በጡር ጎን “አልነበርክም”፤

ቁርአን የእምነት መፅሐፍ እንጂ የታሪክ መፅሐፍ አይደለም፤ ለምሳሌ የዋሻውና የሰሌዳው ባለቤቶች ያለፈ ከስተት ታሪክ ላይ አልተመዘገበም፤ የዙልቀርነይንም ጉዞ አልተመዘገበም፤ ነገር ግን አምላካችን አላህ ሰዎች የተናገሩትን ሁሉ የሚሰማ፣ ሰዎች ያደረጉትን ሁሉን የሚያይ፣ ሰዎች ያሳለፉትን ሁሉ የሚያውቅ ስለሆነ ይህን የዋሻውና የሰሌዳው ባለቤቶች እና የዙልቀርነይንም ጉዞ ለነቢያችን በማውረድ ተርኮታል፡-
18:9 “የዋሻውና የሰሌዳው ባለቤቶች”፥ ከታምራቶቻችን ሲሆኑ ግሩም መሆናቸውን አሰብከን?
18:13 እኛ “ወሬያቸውን በአንተ ላይ በውነት እንተርካለን” نَقُصُّ عَلَيْكَ፤ እነሱ በጌታቸው ያመኑ ጎበዞች ናቸው፤ መመራትንም ጨመርንላቸው።
18:26-27 አላህ የቆዩትን ልክ “ዐዋቂ” ነው በላቸው፤ “የሰማያትና የምድር ምስጢር የሱ ብቻ” ነው፤ እርሱ “ምንኛ ያይ! ምንኛ ይሰማም”! ለነርሱ ከርሱ በቀር ምንም ረዳት የላቸውም፤ በፍርዱም አንድንም አያጋራም። ከጌታህም መጽሐፍ ወደ አንተ “የተወረደውን” አንብብ፤
18:83-84 ከዙልቀርነይንም ይጠይቁሃል፤ በናንተ ላይ ከርሱ “ወሬን” አነባለሁ” በላቸው። እኛ ለርሱ በምድር አስመቸነው፤ ከነገሩም ሁሉ መዳረሻ መንገድን “ሰጠነው”።

ነጥብ ሶስት
“በቅተንሃል”
ሚሽነሪዎች መፅሐፍ ቅዱስ ላይ የሌለ ጉዳይ ቁርአን ላይ ሲያዩ ታሪክ ላይ የት አለ? ብለው ይጠይቃሉ፤ ቀጥሎ ከመፅሐፍ ቅዱስ ጋር የሚመሳሰል ትረካ ሲያዩ ኩረጃ ይላሉ፤ እኔ ምለው አንድ የሚኮርጅ ሰው ሲኮርጅ ትክክሉን ከስህተቱ ጋር ከሆነ ምነው የመፅሐፍ ቅዱስ ስህተቶች ቁርአን ውስጥ አልተገኙም? ሚሽነሪዎች ይህ ጥያቄ የሚጠይቁት ሲጨንቃቸውና የፈጣሪን ቃል በምን እናጠልሽው ነው፤ ይህን የኩረጃ ክስ በነቢያችን ዘመን የነበሩ ሰዎችም ሲያነሱን ነበር፤ ለዚህ መሳለቅ ሁሉ አላህ “ከፈይናከ” كَفَيْنَاكَ“በቅተንሃል” በማለት እራሱ ምላሽ ይሰጣል፡-
15:94 “የታዘዝከበትንም ነገር በይፋ ግለጽ”። አጋሪዎችንም ተዋቸው። “ተሳላቂዎችን” ሁሉ እኛ “በቅተንሃል” كَفَيْنَاكَ ።

ቁርአን በወረደበት ወቅት ናድርና ሰራዊቱ ቁርአንን፡- “የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ተረቶች ነው፤ ጢትና ማታ በማንበብ ሌሎች ሕዝቦች ያግዙታል” ብለው ላስተባበሉበት ማስተባበያ አላህ ነቢያችንን ፡-”በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለን ምስጢር የሚያውቀው፣ አወረደው” በላቸው በማለት ለተሳላቂዎች መልስ ይሰጣል፡-
25:4-26 እነዚያም የካዱት፣ የቀጠፈው፣ በርሱም ላይ “ሌሎች ሕዝቦች ያገዙት” የሆነ ውሸት እንጂ ሌላ አይደለም አሉ፤ በእርግጥም በደልንና እብለትን ሠሩ።
አልሉም፡- “የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ተረቶች ናት”፤ አስጣፋት፤ እርሷም በርሱ ላይ “ጢትና ማታ ትነበብለታለች”። “ያ በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለን ምስጢር የሚያውቀው፣ አወረደው፤ እርሱ መሐሪ አዛኝ ነውና፤ በላቸው”።

በመኮረጅ ያግዙታል ብለው የሚያስጠጓቸው ሮማዊ ወይም ፋርሳዊ አሊያም ዕብራዊ ሰዎች ሲሆኑ የእነርሱ ቋንቋ “ዐጀም” ማለትም ባእድ”foreigner” ሲሆን ቁርአን ግን ግልፅ አረቢኛ ቋንቋ መሆኑን አምላካችን አላህ ተናግሯል፡-
16:103 እነሱም እርሱን ቁርአን የሚያስተምረው ሰው ብቻ ነው፣ ማለታቸውን በእርግጥ “እናውቃለን”፤ የዚያ ወደ እርሱ የሚያስጠጉበት ሰው ቋንቋ ዐጀም ነው፤ ይህ ቁርአን ግን “ግልጽ ዐረብኛ ቋንቋ” ነው።

ነቢያችን ለመኮረጅ የሚያስችል ማንበብና መፃፍ የማይችሉ መሆናቸው አላህ መስክሯል፤ ከዛም ባሻገር ወደ እርሱ ምንም ያልተወረደለት ሲኾን «ወደ እኔ ተወረደልኝ» ያለ ሰው እና መጽሐፉን በእጆቻቸው ፅፈው «ይህ ከአላህ ዘንድ ነው» ለሚሉ ወዮላቸው በማለት አጥፊዎቹ የሚጠራጠሩበትን ትችት ድባቅ አስገብቷል፡-
29:48 ከርሱ በፊትም “መጽሐፍን የምታነብ በቀኝህም የምትጽፈው” አልነበርክም፤ ያን ጊዜ አጥፊዎቹ በእርግጥ በተጠራጠሩ ነበር።
2:79 ለነዚያም መጽሐፉን በእጆቻቸው ለሚጽፉና ከዚያም በርሱ ጥቂትን ዋጋ ሊገዙበት «ይህ ከአላህ ዘንድ ነው» ለሚሉ ወዮላቸው፡፡
6:93 በአላህም ላይ እብለትን ከቀጣጠፈ ወይም ወደርሱ ምንም ያልተወረደለት ሲኾን «ወደ እኔ ተወረደልኝ» ካለና፡- «አላህም ያወረደውን ብጤ በእርግጥ አወርዳለሁ» ካለ ሰው ይበልጥ በዳይ ማን ነው?

መደምደሚያ
ቁርአን በግምት ከትውፊት ላይ ወይም ከሆነ ፅሁፍ ላይ ምንጭ ተደርጎ የተወሰደ ሳይሆን የዓለማቱ ጌታ ንግግር ነው፤ የቁርአን ተናጋሪ ፈጣሪያችን አላህ ሁሉን አዋቂ፤ ሁሉን ሰሚና ሁሉን ተመልካች መሆኑን ካመንን እርሱ የሚናገረው ንግግር ትክክለኛ ምስክርነት ነው፤ ምስክርነትም በእርሱ በቃ፡-

6:19 «በምስክርነት ከነገሩ ሁሉ ይበልጥ ታላቅ ማነው» በላቸው፡፡ሌላ መልስ የለምና «አላህ ነው፡፡ በእኔና በእናንተ መካከል “መስካሪ” ነው شَهِيدٌ بَيْنِي وَبَيْنَكُم ۚ ፡፡ ይህም ቁርኣን እናንተንና የደረሰውን ሰው ሁሉ በርሱ ላስጠነቅቅበት ወደኔ ተወረደ፡፡
46:8 እርሱ ያንን በርሱ የምትቀባጅሩበትን ዐዋቂ ነው፤ በእኔና በእናንተ መካከል “መስካሪ በእርሱ በቃ” كَفَىٰ بِهِ شَهِيدًا بَيْنِي وَبَيْنَكُمْ ۚ ፡፡ እርሱም መሐሪው አዛኙ ነው በላቸው ፡፡

ፈጣሪ ንግግሩ ትክክል ነው ወይም አይደለም ምስክር አያስፈልገውም፤ ቅድሚያና ዋናው የቁርአን ተናጋሪ አላህ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፤ ከዚያ አላህ በነገሩ ሁሉ መስካሪ መሆኑ በቂ ነው፡-
34:47 አላህ እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ መስካሪ ነው شَهِيدٌ ۚ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ ፤ በላቸው።

41:53 ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ መስካሪ መሆኑ አይበቃቸውምን? أَوَلَمْ يَكْفِ بِرَبِّكَ أَنَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ شَهِيدٌ።
59:22 እርሱ አላህ ነው፤ያ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ “ሩቁንና ቅርቡን አዋቂ የሆነው፤ እርሱ እጅግ በጣም ርኅሩኅ በጣም አዛኝ ነው።

የፀሐይ መጥለቂያና መውጪያ

ክፍል አንድ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

መግቢያ
ፀሐይ የፕላኔታችን ስርዓተ-ብርሃን”Solar System” እምብርትና ከህልቆ መሳፍርት ከዋክብት አንዷ የንጋት ኮከብ ስትሆን፣ ቁርአን የምትወጣበትን እና የምትገባበትን የስነ-ምርምር ጥናት ሳያትት ቀድሞ በመናገር ፋና ወጊና ፈር ቀዳጅ ነው፣ ቁርአን ፀሐይ የምትወጣበትንና የምትገባበትን በተለያየ ፈርጅና ደርዝ ያስቀምጠዋል፡-

ፈርጅ አንድ
“ምስራቅና “የምዕራብ”
“መሸሪቅ” مَشْرِق የሚለው የአረቢኛው :አሸረቀ” أَشْرَق
”አበራ” ወይም “ገለጠ” ከሚል ግስ የመጣ ሲሆን “ገላጭ” ወይም “ምስራቅ” የሚል ፍቺ አለው፣ ይህ ቃል በቁርአን በነጠላ 11 ጊዜ ተወስቷል።
“መግሪብ” مَغْرِب የሚለው ቃል ደግሞ “ገረበ” غَرَبَ“ገባ” ወይም “ተደበቀ” አሊያም “ተሰወረ” ከሚል ግስ የመጣ ሲሆን “ገቢ” ተደባቂ፣ “ምዕራብ” የሚል ፍቺ አለው፣ ይህ ቃል በቁርአን በነጠላ 10 ጊዜ ተወስቷል፤ ፀሐይ ለአይናች የምትጠልቅበትና የምትወጣበት ነገር እኛ ሊገባን በሚችለው መረዳት ከእኛ አንጻር ተነገረን እንጂ ከመነሻው አትገባም አትወጣ፤ የፀሐይን መውጣትና መግባት ሰው ቤቱ ገባና ወጣ ስንል ቤቱ ቃሚ ሰውዬው ተንቀሳቃሽ በሚል ሂሳብ አንረዳውም፣ የእኛን እይታን ታሳቢና ዋቢ ያደረገ ነው፤ ምስራቅና ምዕራብ አንጻራዊና ጥቅላዊ ነው፡-
73:9 እርሱም “የምስራቅ” الْمَشْرِقِ እና “የምዕራብ” وَالْمَغْرِبِ ጌታ ነው፤ ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም፤ መጠጊያ አድርገህም ያዘው።

ዋቢ የምርምር ጥናት፡-
1.Gregory, S. A. (1998). Introductory Astronomy & Astrophysics
2.Phillips, K. J. H. (1995). Guide to the Sun. Cambridge University Press. p. 73.
3.Zirker, J. B. (2002). Journey from the Center of the Sun. Princeton University Press. pp. 15–34

ፈርጅ ሁለት
“ሁለቱ ምሥራቆችና ሁለቱ ምዕራቦችም”
“መሸሪቀይኒ” الْمَشْرِقَيْنِ“የመሸሪቅ ሙተና”dual” ሲሆን ፀሐይ በበጋ ጊዜ በሰሜን ንፍቀ-ክበብ”north pole” ስትወጣ በክረምት ጊዜ ደግሞ በደቡብ ንፍቀ-ክበብ”south pole” መውጣቷን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው።
“መግሪበይኒ” الْمَغْرِبَيْنِ የመግሪብ ሙተና”dual” ሲሆን ፀሐይ በበጋ ጊዜ በሰሜን ንፍቀ-ክበብ”north pole” ስትገባ በክረምት ጊዜ ደግሞ በደቡብ ንፍቀ-ክበብ”south pole” ትገባለች፣ ይህንን ቁርአን ያስተነተነው በአንጻራዊና በተናጥሎአዊ ነው፡-

55:17 “የሁለቱ ምሥራቆች” رَبُّ الْمَشْرِقَيْنِ “የሁለቱ ምዕራቦችም” وَرَبُّ الْمَغْرِبَيْنِ ነው።

ዋቢ የምርምር ጥናት፡-
1.Marina A. (2 November 2012). “The Absolute Chronology and Thermal Processing of Solids in the Solar Protoplanetary Disk”
2. Tobias, S. M. (2005). “The solar tachocline: Formation, stability and its role in the solar dynamo”. CRC Press. pp. 193–235
3.Wang, Y.-M.; Sheeley, N. R. (2003). “Modeling the Sun’s Large-Scale Magnetic Field during the Maunder Minimum”.

ፈርጅፈርጅ ሶስት
“ምስራቆችና ምዕራቦችም”
70:40 በምስራቆችና ምዕራቦችም بِرَبِّ الْمَشَارِقِ وَالْمَغَارِبِ እምላለሁ፤ እኛ በርግጥ ቻዮች ነን፤

“መሻሪቅ” الْمَشَارِقِ የመሸሪቅ ጀመእ”plural” ሲሆን “መጋሪብ” وَالْمَغَارِبِ ደግሞ የመግሪብ ብዙዮሽ ቁጥር ነው፤ የእኛ የንጋት ኮከብ ፀሐይ ለእኛ ስርዓተ-ብርሃን መውጣትና መግባት እንዳላት ሁሉ እያንዳንዳቸው ከዋክብትም በራሳቸው ስርዓተ-ብርሃን ላይ መውጣትና መግባት አላቸው፡-
56:75 በከዋክብትም መጥለቂያዎች بِمَوَاقِعِ እምላለሁ።
52:49 ከሌሊቱም አወድሰው፤ በከዋክብት መደበቂያ وَإِدْبَارَ ጊዜም አወድሰው ።
81:15 ተመላሾችም بِالْخُنَّسِ በሆኑት እምላለሁ። ኪያጆች الْكُنَّسِ ገቢዎች الْجَوَارِ በሆኑት ከዋክብት።

ዋቢ የምርምር ጥናት፡-
1.Schutz, B. F. (2003). Gravity from the ground up. Cambridge University Press. pp. 98–99.
2. Reid, M.J. (1993). “The distance to the center of the Galaxy”.
3.Gillman, M.; Erenler, H. (2008). “The galactic cycle of extinction”.

እንግዲህ ከላይ ያየናቸው የፀሐይ መጥለቂያ ከዘመናዊ ጥናት ምርምር ጋር አንዳች ተፋልሶ የሌለበት ሆኖ ሳለ ባይብላቸው ውስጥ ያለውን ፍጭት ከዘመናዊ ጥናት ምርምር ጋር ማካሄድ ሲያቅታቸው የፕሮቴስታንት አቃቤ-እምነት ሳም ሻሙስና ዴቪድ ሁድ *ቁርአን የፀሐይ መጥለቂያ ጥቁር ጭቃ ነው* ብለው ከዘመናዊ ጥናት ምርምር ጋር ለማላተም ሲዳዱና ሲቃጡ ይታያሉ፣ እስቲ ጥቅሱን በሰከነ ቀልብ እንመልከተው፡-
18:86 ወደ ፀሐይ መግቢያም በደረሰ ጊዜ ጥቁር ጭቃ ባላት ምንጭ ውስጥ ስትጠልቅ “አገኛት” حَتَّىٰ إِذَا بَلَغَ مَغْرِبَ الشَّمْسِ وَجَدَهَا تَغْرُبُ فِي عَيْنٍ حَمِئَةٍ وَوَجَدَ عِندَهَا قَوْمًا ۗ قُلْنَا يَا ذَا الْقَرْنَيْنِ إِمَّا أَن تُعَذِّبَ وَإِمَّا أَن تَتَّخِذَ فِيهِمْ حُسْنًا ﴿٨٦﴾ ::

“ወጀደሃ” وَجَدَهَا የሚለው የአረቢኛው ቃል የሁለት ቃላት ጥምረት ነው፤ “ወጀደ” وَجَدَ ማለት “አገኘ” ወይም “አየ” ማለት ሲሆን “ሃ” هَا ደግሞ ሶስተኛ መደብ ተሳቢ ነጠላ አንስታይ ተውላጠ-ስም ነው፣ አላህ ዙልቀርነይን አያት አለ እንጂ የፀሐይ መጥለቂያ ጥቁር ጭቃ ነው አላለም የአረፍተነገሩ ግስ ዙልቀርነይን እንጂ አላህ አይደለም ፣ ሲያያት ለአይኑ በደቡብ-ምስራቅ አውሮፓና በምዕራብ ኤዢያ በምትገኘው ጥቁር ባህር ስትጠልቅ ይሁን እንጂ አይደለም በጥቁር ጭቃ ይቅርና መጥለቅና መውጣትስ ቀድሞውኑ ይታሰባል እንዴ?አራት ማዕዘን ቁስ ሲሸከረከር ስናይ ክብ አይደለምን ያ አንጻራዊ ወይስ ነባራዊ ክስተት? የዙልቀርነይን እይታ በፀሐይ ወጋገን አድማስ በዚህ ቀመር ማየት ነው፤ “ወጀደሃ” وَجَدَهَا እይታን እንደሚያመለክት

ሌሎች ጥቅሶች ተመልከት፡-
72:8 እኛም ሰማይን ለመድረስ ፈለግን፤ ብርቱ ጠባቂዎችንና ችቦዎችንም ተሞልታ “አገኘናት” فَوَجَدْنَاهَا ::
12:65 ዕቃቸውንም በከፈቱ ጊዜ ሸቀጣቸውን ወደነርሱ ተመልሳ “አገኙ” وَجَدُوا :-
7:44 የገነትም ሰዎች የእሳትን ሰዎች ጌታችን ቃል የገባልንን እውነት ሆኖ “አገኘን” وَجَدْتُم ۚ፤

አውዱ ላይ ስንመለከተው ዙልቀርነይን ፀሐይ ስትጠልቅ ያያት በጥቁር ጭቃ እንደሆነ ሁሉ ስትወጣም ያያት በሕዝቦች ላይ ነበር፣ ታዲያ ያ ማለት ቁርአን ፀሐይ የምትወጣው በሕዝቦች ላይ ነው ብሏልን? ይህ የዙልቀርነይን አስተያየት እንጂ የአላህ አስተያየት አይደለም፤ በጥቁር ጭቃ እና በሕዝቦች ላይ ቃል በቃል እንደ አላህ አስተያየት ከተወሰደ መውጣትና መግባትስ ምን ሊሆን ነው ? የሰው አንጻራዊ እይታ ወይስ ነባራዊ እውነታ?፡-
18:90 ወደ ፀሐይ መውጫ በደረሰም ጊዜ፥ ለነሱ ከበታችዋ መከለያን ባላደረግንላቸው ሕዝቦች ላይ ስትወጣ “”አገኛት”” ﴿حَتَّىٰ إِذَا بَلَغَ مَطْلِعَ الشَّمْسِ وَجَدَهَا تَطْلُعُ عَلَىٰ قَوْمٍ لَّمْ نَجْعَل لَّهُم مِّن دُونِهَا سِتْرًا ٩٠﴾ ።

መደምደሚያ
ከላይ ያለውን አንቀፅ ሲተቹ ባይብሉን በቅጡ ያዩት አይመስለኝም፤ ባይብል ፀሐይ መግቢያና መውጫ አላት ይላል፡-
ሚልክያስ 1፥11 ከፀሐይ #መውጫ ጀምሮ እስከ #መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና፡፡
መዝሙረ ዳዊት 50፥1 ከፀሓይም #መውጫ ጀምሮ እስከ #መግቢያዋ ድረስ ምድርን ጠራት።
መዝሙረ ዳዊት 113፥3 ከፀሐይ #መውጫ ጀምሮ እስከ #መግቢያው ድረስ የእግዚአብሔር ስም ይመስገን።

የፀሐይ መግባትና መውጣት ሰው ገባና ወጣ በተባለበት ሂሳብ ነው የቀረበው፡-
ሳሙኤል ካልዕ 3፥25 የኔር ልጅ አበኔር ያታልልህ ዘንድ፥ *#መውጫህንና #መግቢያህንም* ያውቅ ዘንድ፥ የምታደርገውንም ነገር ሁሉ ያስተውል ዘንድ እንደ መጣ አታውቅምን? አለው።
ነገሥት ቀዳማዊ 3፥7 አሁንም፥ አቤቱ አምላኬ ሆይ፥ እኔን ባሪያህን በአባቴ በዳዊት ፋንታ አንግሠኸኛል እኔም *#መውጫንና #መግቢያን* የማላውቅ ታናሽ ብላቴና ነኝ።

የፀሐይ መግባትና መውጣት ሰው ገባና ወጣ በተባለበት ሂሳብ መሆኑን የምናቅበት ምድር ቋሚ ሆና ፀሐይ ከእንቅስቃሴ መቋረጧ ነው፡-
ኢያሱ 10፥13 ሕዝቡም ጠላቶቻቸውን እስኪበቀሉ ድረስ #ፀሐይ #ቆመ፥ ጨረቃም ዘገየ።
ዕንባቆም 3፥11 #ፀሐይና ጨረቃ በመኖሪያቸው #ቆሙ።
ኢዮብ 9፥7 ፀሐይን #ያዝዛታል፥ #አትወጣምም
አሞጽ 8፥9 በዚያም ቀን ፀሐይ በቀትር #እንድትገባ አደርጋለሁ፥

ጥያቄ ፀሐይ የምትጠልቀው የት ነው?
1.በታላቁ ባሕር?
ኢያሱ 1፥4 ከምድረ በዳው ከዚህም ከሊባኖስ ጀምሮ እስከ ታላቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ድረስ የኬጢያውያን ምድር ሁሉ *እስከ ፀሐይ #መግቢያ እስከ #ታላቁ #ባሕር * ድረስ ዳርቻችሁ ይሆናል።

2.በዮርዳኖስ ማዶ?
ዘዳግም 11፥30 እነርሱም *#በዮርዳኖስ #ማዶ፥ ከፀሐይ #መግቢያ ካለችው መንገድ* በኋላ፥

3.በነቢያት ላይ?
ሚክያስ 3፥6 #ፀሐይም *#በነቢያት ላይ* #ትገባለች፥

4. በሰራዊቱ መካከል? ሽ1ኛ ነገሥት 22:36 በሠራዊቱም መካከል ፀሐይ ስትገባ። ንጉሡ ሞቶአልና እያንዳንዱ ወደ ከተማው፥ እያንዳንዱም ወደ አገሩ ይሂድ የሚል ጩኸት ሆነ።
የቱ ነው ትክክል? ኢንሻላህ በከፍል ሁለት በሐዲስ ላይ የተተቸውን እንመለከታለን።

የፀሐይ መጥለቂያና መውጪያ

ክፍል ሁለት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡

መግቢያ
ባለፈው በክፍል አንድ የፀሐይ መጥለቂያና መውጫ ከእርሱ ጋር ተያይዞ የተነሳውን ትችት ደርዝና ፈርጅ ባለው መልኩ ስንመለከት ነበር፣ ዛሬ ደግሞ ኢንሻላህ ሁለተኛውን ትችት የለበጣ ትችት እንደሆነ እና ምንተ-አፍረታቸው በሰከነ ልብ እናያለን።

የስነ-ፈለክ ጥናት ታሪክን ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት “ምድር” የስርዓተ-ፈለክ እምብርት”Geocentric” ናት ተብሎ በጥንት ይታመን ነበር፣ ነገር ግን በ1533 AD ኒክላስ ኮፐርኒኮስ ምድር ሳትሆን ፀሐይ የስርዓተ-ፈለክ እምብርት”Heliocentric” ናት ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ለዓለማችን አበረከተ፣ ያ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ፀሐይ ቋሚ እምብርት”stationary” እንጂ ትንቀሳቀሳለች ተብሎ አይታሰብም ነበር፣ ነገር ግን በ1783 AD ዊሊያም ሃርቸል ፀሐይ በሰከንድ 16.5 ኪሎ ሜትር ትጓዛለች ብሎ ግኝት አመጣ ይህ ግኝት “ሶላር አፔክስ”solar apex” ይባላል፣ የምትሄድበትን ቦታ ምሁራን “local standard of rest”(LSR) አሊያም “Galactic Center” ይሉታል፣ በመቀጠል ከሄደችበት ስትመለስ የሚኖራት የጊዜ ፍጥነት በሰከንድ 19.7 ኪሎ ሜትር ነው ተብሎ ይዘከራል፣ ይህም ግኝት “ሶላር አንታፔክስ”solar antapex” ይባላል።

ዋቢ የስነ-ፈለክ ጥናት፡-
1. North, John (1995). The Norton History of Astronomy and Cosmology. New York and London: W.W. Norton & Company. pp. 30–31.
2. Grasshoff, Gerd (1990). The history of Ptolemy’s star catalogue. Springer. pp. 1–5
3.Smith, Michael David (2004). The Origin of Stars. Imperial College Press. pp. 57–68

እንግዲህ ከላይ ያየናቸው የስነ-ፈለክ ጥናት ዋቢና ታሳቢ ባደረገ መልኩ ስንመለከት ቁርአን ከዚህ ምርምር ጥናት በፊት ፀሐይ ለርሷ ወደሆነው መርጊያ እንደምትጓዝ ነግሮናል፡-
36:38 ፀሐይም ለርሷ ወደሆነው መርጊያ ትሮጣለች ይህ የአሸናፊው የዐዋቂው አምላክ ውሳኔ ነው።

ታዲያ ትችቱ የት አለ? ይባል ይሆናል፣ በሐዲስ ላይ ፀሐይ በምንጭ ውሃ ትገባለች ይላል፣ ይህም ሐዲስ ከመነሻው ደይፍ ማለትም ደካማ ቢሆን የተቺዎችን ትችት ውሃ የሚያስነሳ ሙግት ሳይሆን ድባቅ የሚያስገባ ነው፡-
ኢማም አቢ ዳውድ መጽሐፍ 32, ሐዲስ 34
አቢ ዘር እንደተረከው፤ ከአላህ መልክተኛ”ﷺ” አጠገብ ተቀምጬ፤ እንዲሁ በአህያ ላይ እየጋለበ በተመሳሳይ ፀሐይ ጠለቀች፤ ፀሐይ የት እንደምትሔድ ታውቃለህን? ብለው ጠየቁኝ፤ እኔም አላህና መልእክተኛው የተሻለውን ያውቃሉ ብዬ መለስኩኝ፤ ፀሐይ በምንጭ ውሃ ትገባለች አሉኝ።
قَالَ كُنْتُ رَدِيفَ رَسُولِ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم وَهُوَ عَلَى حِمَارٍ وَالشَّمْسُ عِنْدَ غُرُوبِهَا فَقَالَ ” هَلْ تَدْرِي أَيْنَ تَغْرُبُ هَذِهِ . قُلْتُ اللَّهُ وَرَسُولُهُ أَعْلَمُ . قَالَ ” فَإِنَّهَا تَغْرُبُ فِي عَيْنِ حَامِيَةٍ ”

ይህንን ሐዲስ ተቺዎች ከዙልቀርነይን እይታ ጋር ሊያምታቱ ይሞክራሉ፤ ከነብያች”ﷺ” ሰማው ብሎ የሚተርክልንን ሙሃጅር የነበረው አቢ ዘርን ሙሉ ንግግር መመልከት ያሻል፣ ይህንን ሙሉ ንግግሩን አህመድ ኢብኑ ሃንበልና ኢማም ቡሃሪም ዘግበውታል፡-

Musnad Ahmad, Hadith 21459
Abu Dharr narrated, “Once I was with the Prophet riding a donkey on which there was a saddle or a velvet. That was at sunset. He said to me, ‘O Abu Dharr, do you know where this sets?’ I said, ‘Allah and His Messenger know better.’ He said, ‘It sets in #a #spring #of #water then it goes and prostrates before its Lord, the Exalted in Might and the Ever-Majestic, #under the #Throne. And when it is time to go out, Allah allows it to go out and thus it rises. But, when He wants to make it rise where it sets, He locks it up. The sun will then say, “O my Lord, I have a long distance to run.” Allah will say, “Rise where you have set.” ’”

Sahih Bukhari Volume 4, Book 54, Number 421:
Narrated Abu Dhar:
The Prophet asked me at sunset, “Do you know where the sun goes?” I replied, “Allah and His Apostle know better.” He said, “It goes till it prostrates Itself #underneath #the #Throne and takes the permission to rise again, and it is permitted and then it will be about to prostrate itself but its prostration will not be accepted, and it will ask permission to go on its course but it will not be permitted, but it will be ordered to return whence it has come and so it will #rise in the #west.and that is what Allah, may He be glorified, refers to in the verse (interpretation of the meaning): “And the sun runs on its fixed course for a term (appointed). That is the Decree of the All-Mighty, the All-Knowing” [Yaa-Seen 36:38].

ሁሉም ጋር ማለትም አቢ ዳውድ ሱለይማን፣ አህመድ ኢብኑ ሃንበል፣ ኢማም ቡሃሪም በዘገቡት ላይ ተራኪው አቢ ዘር ሲሆን ነብያችን”ﷺ” የተናገሩት ፀሐይ ላይ በምንጭ ውሃ ትገባለች፣ በጉዞዋ ወደ አላህ ዙፋን ስር ለአላህ ትሰግድና በገባችበት ትመለሳለች ነው፣ ታዲያ የአላህ ዙፋን በውሃ ላይ አይደለምን? ከሰባተኛ ሰማይ በላይ ውሃ አለ፤ በውሃው ላይ ታላቁ ዙፋን አለ፤ ይህንን ነው አውዱ በምንጭ ውሃ የሚለው፡-
11:7 እርሱም ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀኖች የፈጠረው ነው፤ #ዐርሹም #በውሃ ላይ ነበር፤
Sahih al-Bukhari, Volume 4, Book 54, Number 414
Narrated Imran bin Husain: …. He said, “First of all, there was nothing but Allah, and His #throne was over #the #water,
Jami` at-Tirmidhi Book 44 Number 3320
Ahnaf bin Wais narrated :Then the Messenger of Allah said: ‘Above the seventh heaven is #a #water,

ፀሐይ በሰከንድ 16.5 ኪሎ ሜትር ትጓዛለች፤ ይህን ጉዞ ዊሊያም ሃርቸል “ሶላር አፔክስ”solar apex” ሲለው ነብያችን ደግሞ የአላህ ዙፋን ያለበት ውሃ ብለውታል፤ ከዚህ ቦታ በቂያማ ቀን ስትመለስ ዊሊያም ሃርቸል “ሶላር አንታፔክስ”solar antapex” ሲለው ሐዲሱ ደግሞ በጠለቀችበት በምዕራብ ትወጣለች ይለናል፤ ይህ የመጨረሻው ቀን ምልክት ነው፡-
Sahih Bukhari Volume 5, Book 60, Number 159:
Narrated Abu Huraira: Allah’s Apostle said, “The Hour will not be established until the #sun #rises from the #West: and when the people see it,

ነቢያችን በንግግራቸው ላይ የቁርአን አንቀጽ ይጠቅሳሉ፡-
36:38 ፀሐይም ለርሷ ወደሆነው መርጊያ ትሮጣለች ይህ የአሸናፊው የዐዋቂው አምላክ ውሳኔ ነው።

ይህ የአውድ ሙግት ታሳቢና ዋቢ ያደረገ ነው።

መመምደሚያ

ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ መስገጂ ጥያቄ ጭሮ ማለፉ ስለማይቀር ስለ ስግደት ላጠቃልል፣ “ሱጁድ” سُجود የሚለው ቃል “ሰጀደ” سَجَدَ“ተገዛ” ወይም “ሰገደ” አሊያም “ታዘዘ” ከሚል ግስ የተገኘ ሲሆን መታዘዝን፣ መገዛትን፣ መንበርከክን ያሳያል፤ ስግደት መታዘዝ በሚል ይመጣል፡-
13:15 በሰማያትና በምድርም ያሉት ሁሉ በውድም ሆነ በግድ ለአላህ #ይሰግዳሉ፤ ጥላዎቻቸውም በጧቶችና በሠርኮች #ይሰግዳሉ ።
22:18 አላህ፣ በሰማያት ያለው ሁሉ፣ በምድርም ያለው ሁሉ ፀሐይና ጨረቃም፣ ክዋክብትም፣ ተራራዎችም፣ ዛፎችም፣ ተንቀሳቃሾችም፣ ከሰዎች ብዙዎችም ለእርሱ #የሚሰግዱለት መኾኑን አታውቁምን?
16:48 ወደዚያ ከማንኛውም ነገር አላህ ወደ ፈጠረው ጥላዎቹ እነርሱ የተዋረዱ ሲሆኑ ለአላህ #ሰጋጆች ሆነው ከቀኝና ከግራዎች ወደሚዛወሩት አላዩምን?
55:6 ሐረግና ዛፍም ለእርሱ #ይሰግዳሉ።

በሰማያት ያለው ሁሉ፣ ፀሐይና ጨረቃም፣ ክዋክብትም፣ በምድርም ያለው ሁሉ ተራራዎችም፣ ዛፎችም፣ ተንቀሳቃሾችም፣ ሐረግና ዛፍም እና ጥላዎቻቸውም አላህ በተፈጥሮ ላስቀመጠው ህግ ይገዛሉ ይታዘዛሉ፤ ይህ ስግደት ነው፤ እንዴት እንደሚሰግዱ ባናውቅም ግን ይሰግዳሉ፤ የግድ ሶላት ላይ እንደምንሰግደው ሰላት አይነት እንዴት አልሰገዱም ሸርጥ አይሆንም።

አላህ ሳጂዱን ከሚላቸው ባሮቹ ያድርገን አሚን።

ጨረቃ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

መግቢያ
ጸሐይ እና ጨረቃም በቁርአን ከምናስተነትናቸው ታምራቶች ናቸው፤ እነርሱም ከአላህ ምልክቶች እንጂ አይመለኩ አይሰገድላቸውም፤ ነገር ግን የሚመለከውና የሚሰገድለት እነርሱን የፈጠረ አላህ ብቻ ነው፤ ስለ ፀሐይ አርስታችን ስላልሆነ ወደ ጎን ትተን ስለ ጨረቃ እስቲ እናስተንትን፤ ቁርአንን ለሚያስተነትኑ ሰዎች በጨረቃ ውስጥ ታምር እንደአለበት አላህ ይነግረናል፡-
16:12 ለእናንተም ሌሊትንና ቀንን ፀሐይን እና *ጨረቃንም” ገራላችሁ፤ ከዋክብትም በፈቃዱ የተገሩ ናቸው፤ “በዚህ” “ውስጥ” ለሚያውቁ ሕዝቦች በእርግጥ “ታምራቶች” አሉ።
41:37 ሌሊትና ቀንም፣ ጸሐይ እና “ጨረቃም”፣ “”ከምልክቶቹ”” ናቸው፤ ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ፤ ለዚያም ለፈጠራቸው ለአላህ ስገዱ፤ እርሱን ብቻ የምታመልኩ እንደሆናችሁ ለሌላ አትስገዱ።

ይህም ታምር በሁለት መልኩ ማየት ይቻላል፤ አንደኛ ጊዜን ሲሆን ሁለተኛ ምህዋር ነው፡-

ነጥብ አንድ
“ጊዜ”
ጨረቃ የዓመታትን ጊዜ ቁጥርና ሒሳብን ማወቂያ ምልክት ነው፡-
10:5 እርሱ ያ ፀሐይን አንጸባራቂ ጨረቃንም አብሪ ያደረገ ነው፡፡ የዓመታትን “ቁጥርና ሒሳብን” ታውቁ ዘንድም ለእርሱ መስፈሪያዎችን የለካ ነው።
6:96 እርሱም ንህን ከሌሊት ጨለማ ፈልቃቂ ሌሊትንም ማረፊያ ፀሐይንና ጨረቃንም ለጊዜ “መቁጠሪያ” አድራጊ ነው፡፡ ይህ የአሸናፊው የዐዋቂው አላህ ችሎታ ነው፡፡
2:189 ከለጋ ጨረቃዎች ይጠየቁሃል፡፡ እነርሱ ለሰዎች ጥቅም ለሐጅም ማወቂያ ጊዜያቶች ምልክቶች ናቸው በላቸው፡፡

ነጥብ ሁለት
“ምህዋር”
“ፈለክ” فَلَك የሚለው ቃል “ምህዋር”orbit” ማለት ሲሆን አምላካችን አላህ በተከበረው ከሊማ ጨረቃ በራስዋ ምህዋር እንደምትሮጥ የዘመኑ የሥነ-ፈለክ ጥናት”astronomy” ምሁር የሆኑት አይዛክ ኒውተን ከመናገሩ በፊት ተናግሯል፡-
14:33 ፀሐይን እና “ጨረቃንም” ዘወትር “ኼያጆች” ሲሆኑ ለእናንተ የገራ ሌሊትና ቀንንም ለእናንተ የገራላችሁ ነው።
55:5 ፀሐይና ጨረቃ በተወሰነ ልክ ይኼዳሉ፤
35:13 ሌሊትን በቀን ውስጥ ያስገባል፤ ቀንንም በሌሊት ውስጥ ያስገባል፤ ፀሐይን እና “ጨረቃንም” ገራ፤ ሁሉም እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ “ይሮጣሉ”፤ ይሃችሁ ጌታችሁ አላህ ነው፤
39:5 ሰማያትንና ምድርን በእውነት ፈጠረ፤ ሌሊትንም በቀን ላይ ይጠቀልላል፤ ፀሐይን እና “ጨረቃንም” ገራ፤ ሁሉም ለተወሰነ ጊዜ “ይሮጣሉ”፤ ንቁ እርሱ አሸናፊው መሐሪው ነው።
21:33 እርሱም ሌሊትና ቀንን ፀሐይንና ጨረቃንም፣ የፈጠረ ነው፤ ሁሉም በፈለካቸው ውስጥ ይዋኛሉ።
36:40 ፀሐይ ጨረቃን ልትደርስበት አይገባትም፤ ሌሊትም ቀንን ያለጊዜው ቀዳሚ አይሆንም፤ ሁሉም “በመዞርያቸው” ውስጥ “ይዋኛሉ”።

ይህንን መጣጥፍ የሚያነብ አንድ አንባቢ፡- “በዚህ ቢያበቃ ታምርነቱ ያን ያህል የጎላ አይደለም” ይል ይሆናል፤ አዋ ዋናው ነጥባችን እርሱ ብቻ አይደለም፤ የዘመናችን የሥነ-ፈለክ ጥናት የጨረቃ ፈለክ ምድራችንን በ 384,408 km በሆነ ኡደት”Revolution” ለመዞር የሚወስድባት ጊዜ 27 ቀናት ነው፤ አምላካችን አላህም በቁርአን “ቀመር” قَمَر ማለትም “ጨረቃ” የሚለውን ቃል የተጠቀመው “27” ጊዜ ብቻ ነው፤ ጨረቃ ፕላኔታችንን በምእራባዊ አቅጣጭ 360 ድግሪ ለመዞር 19 ዓመት ይፈጅባታል፤ የሚያስደምመው ነገር “ዓመት” የሚለው ቃል “ሚኒን” سِنِين ወይም “ሠነት” سَنَة ሲሆን በቁርአን የተጠቀሰው “19” ጊዜ ብቻ ነው፤ ይህ የሆነበት ምክንያት የዓለማቱ ጌታ ነገርን ሁሉ በቁጥር ያጠቃለለ ስለሆነ ነው፡-
72:28 እነርሱ ዘንድ ባለው ነገር እውቀቱ የከበበ እና “”ነገሩንም ሁሉ “በቁጥር” ያጠቃለለ”” ሲሆን፣ የጌታቸውን መልክቶች ያደረሱ መሆናቸውን ያውቅ ዘንድ ጠባቂ ያደርጋል።

ይህ ብሩክ መጽሐፍ ያለምክንያት ከዓለማቱ ጌታ ከአላህ ወደ ነብያችን አልወረደም፤ ባይሆን የአእምሮዎች ባለቤቶች አንቀጾቹን እንዲያስተነትኑ እና እንዲገሰጹ ቢሆን እንጂ፡-
38:29 ይህ ወደ አንተ ያወረድነው ብሩክ መጽሐፍ ነው፤ አንቀጾቹን እንዲያስተነትኑ እና የአእምሮዎች ባለቤቶችም እንዲገሰጹ አወረድነው።

ሰንበት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

“ሠብት” سَّبْتَ የሚለው ቃል “ሰንበት” ማለት ሲሆን ትርጉሙ “ሠባት” سُبَات ማለትም “እረፍት” ማለት ነው፡-
78:9 እንቅልፋችሁንም *ዕረፍት* سُبَاتًا አደረግን።
25:47 እርሱም ያ ለናንተ ሌሊትን ልብስ፣ እንቅልፍንም *ዕረፍት* سُبَاتًا ያደረገ፤ ቀንንም መበተኛ ያደረገላችሁ ነው።

“ሠብት” سَّبَ ማለትም “ሰንበት” የሚለው ቃል በቁርአን የተወሳው 7 ጊዜ ነው፡-
7:163 ከዚያችም በባሕሩ ዳርቻ ከነበረችው ከተማ፣ *በሰንበት* السَّبْتِ ቀን ወሰን ባለፉ ጊዜ፣ *በሰንበታቸው* سَبْتِهِمْ ቀን ዐሣዎቻቸው የተከማቹ ኾነው በሚመጡላቸው ጊዜ፣ የኾነውን ጠይቃቸው፤ *ሰንበትንም* يَسْبِتُونَ በማያከብሩበት በሌላው ቀን፣ አይመጡላቸውም፤ እንደዚሁ ያምጡበት በነበሩት ምክንያት እንሞክራቸዋለን።
2:65 እነዚያንም ከእናንተ ውስጥ *በሰንበት* السَّبْتِ ቀን ዐሣን በማጥመድ ወሰን ያለፉትንና ለእነሱ «ወራዳዎች ስትኾኑ ዝንጀሮዎች ኹኑ» ያልናቸውን በእርግጥ ዐወቃችሁ::

4:47 እላንተ መጽሐፉ የተሰጣችሁ ሆይ! ፊቶችን ሳናብስና በጀርባዎች ላይ ሳንመልሳቸው፣ ወይም *የሰንበትን* ٱلسَّبْتِ ባለቤቶች ያፈረሱትን እንደረገምን ሳንረግማቸው በፊት ከእናንተ ጋር ያለውን የሚያረጋግጥ ኾኖ ባወረድነው እመኑ፣ የአላህም ትዕዛዝ ተፈፃሚ ነው።
4:154 በቃል ኪዳናቸውም ምክንያት የጡርን ተራራ ከበላያቸው አነሳን፤ ለነሱም ደጃፎች አጎንባሾች ሆናችሁ ግቡ አልን፤ ለነሱም *በሰንበት* ٱلسَّبْتِ ቀን ትእዛዝን አትተላለፉ አልን፤ ከእነሱም ከባድን ቃል ኪዳንን ያዝን።
16:124 *ሰንበት* ٱلسَّبْتُ ክልክል የተደረገው፣ በነዚያ በእርሱ በተለያዩበት ሰዎች ላይ ብቻ ነው፤ ጌታህም በትንሣኤ ቀን ይለያዩበት በነበሩት ነገር በመካከላቸው በእርግጥ ይፈርዳል።

አላህ ሰንበት የሚለው ቃል “7” ጊዜ ማውሳቱ ሰንበት 7ኛው ቀን መሆኑን እና አንድ ሳምንት 7 ቀናት መሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፤ ከ 7 ጋር በተያያዘ መልኩ በቁርአን የተለገለፁት ሰማያት 7 ሲሆኑ አላህ “ሰባት ሰማያት” ብሎ የተናገረው 7 ጊዜ ብቻ ነው፦
71:15 አላህ “ሰባትን ሰማያት” سَبْعَ سَمَاوَاتٍ አንዱ ካንዱ በላይ ሲሆን እንዴት እንደፈጠረ አታዩምን?
65:11አላህ ያ “ሰባትን ሰማያት” سَبْعَ سَمَاوَاتٍ የፈጠረ ነው፤ከምድርም መሰላቸውን ፈጥሮአል፤
41:12 በሁለት ቀኖችም ውስጥ “ሰባት ሰማያት” سَبْعَ سَمَاوَاتٍ አደርጋቸው፤ በሰማያቱም ሁሉ ነገሯን አዘጋጀ፤
2:29 እርሱ ያ በምድር ያለውን ሁሉ ለእናንተ የፈጠረ ነው፡፡ ከዚያም ወደ ሰማይ አሰበ፤ “ሰባት ሰማያትም” سَبْعَ سَمَاوَاتٍ አደረጋቸው፡፡ እርሱም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው፡፡
23:86 «”የሰባቱ ሰማያት” ٱلسَّبْعِ وَرَبُّ ጌታ እና የታላቁ ዐርሽ ጌታ ማን ነው» በላቸው፡፡
67:3 ያ “ሰባትን ሰማያት” سَبْعَ سَمَاوَاتٍ የተነባበሩ ሆነው የፈጠረ ነው።
17:44 “ሰባቱ ሰማያት” ٱلسَّبْعُ وَالْأَرْضُ እና ምድርም በውስጣቸውም ያለው ሁሉ ለእርሱ ያጠራሉ፣

የመጀመሪያይቱ ሰማይ የቅርቢቱ ሰማይ ናት። “ዱንያ” ٱلدُّنْيَا ማለት “ቅርቢይቱ” ማለት ሲሆን የከዋክብት ረጨት የያዘች እና እኛ የምንኖርባት የቅርቢቱ ዓለም ናት፦
67:5 “ቅርቢቱን ሰማይም” لسَّمَاءَ الدُّنْيَا በእርግጥ በመብራቶች አጌጥናት፤
37:6 እኛ “ቅርቢቱን ሰማይ” لسَّمَاءَ الدُّنْيَا በከዋክብት ጌጥ አጌጥናት።

ሰባተኛይቱ ሰማይ የመጨረሻይቱም አገር ናት። “አኺራ” ٱلْآخِرَةَ ማለት “መጨረሻይቱ” ማለት ሲሆን ይህቺ የመጨረሻይቱም አገር ጀነት ስትሆን ማረፊያ ናት፤ ሰንበት ማለት ትርጉሙ “ዕረፍት” ማለት መሆኑን እና 7ኛ መሆኑ ልብ ላለው ለእዕምሮ ባለቤት ታምር ነው፦
29፥64 ይህችም የቅርቢቱ ሕይወት መታለያና ጨዋታ እንጂ ሌላ አይደለችም፡፡ “የመጨረሻይቱም አገር” ٱلْآخِرَةَ ٱلدَّارَ እርሷ በእርግጥ የዘላለም ሕይወት አገር ናት፡፡
25:24 የገነት ሰዎች በዚያ ቀን “በመርጊያ” مَقِيلًا የተሻሉ፣ “በማረፊያም” በጣም ያማሩ ናቸው።
18:31 እነዚያ ለእነርሱ የመኖሪያ ገነቶች፣ ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው አሏቸው፤ … ምንዳቸው ምን ያምር! “ማረፊያይቱም” مُرْتَفَقًا ምንኛ አማረች!

መደምደሚያ
ይህ የሆነበት ምክንያት የዓለማቱ ጌታ ነገርን ሁሉ በቁጥር ያጠቃለለ ስለሆነ ነው፦
72:28 እነርሱ ዘንድ ባለው ነገር እውቀቱ የከበበ እና “”ነገሩንም ሁሉ *በቁጥር* ያጠቃለለ”” ሲሆን፣ የጌታቸውን መልክቶች ያደረሱ መሆናቸውን ያውቅ ዘንድ ጠባቂ ያደርጋል።

ይህ ብሩክ መጽሐፍ ያለምክንያት ከዓለማቱ ጌታ ከአላህ ወደ ነብያችን አልወረደም፤ ባይሆን የአእምሮዎች ባለቤቶች አንቀጾቹን እንዲያስተነትኑ እና እንዲገሰጹ ቢሆን እንጂ፦
38:29 ይህ ወደ አንተ ያወረድነው ብሩክ መጽሐፍ ነው፤ አንቀጾቹን *እንዲያስተነትኑ* እና *የአእምሮዎች* *ባለቤቶችም* *እንዲገሰጹ* አወረድነው፡፡

ሥነ-ፈለክ

ክፍል አንድ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

27:93 ምስጋና ለአላህ ነው፤ ታምራቶቹን ወደፊት ያሳያችኋል፤ ታውቁታላችሁ በላቸው።

መግቢያ
“አስትሮኖሚ”Astronomy” ማለት “ሥነ-ፈለክ ጥናት” ሲሆን ከመሬት ከባቢ አየር ውጪ የሚገኙ ክስተቶችን የሚያጠና የምርምር ዘርፍ ነው። አላህ የዛሬ 1400 ዓመት በተከበረው ቃሉ በቁርአን “በአጽናፎቹ ውስጥ ያሉትን ታምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን” ብሎ ቃል ገብቶ ነበር፡-
41፥53 እርሱም ቁርአን እውነት መሆኑ ለነርሱ እስከሚገለጽላቸው ድረስ፣ #በአጽናፎቹ #ውስጥ እና በራሶቻቸውም ውስጥ #ያሉትን #ታምራቶቻችንን በእርግጥ #እናሳያቸዋለን፤ ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ መሆኑ አይበቃቸውምን?

በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂው አላህ በአጽናፎች ያሉትን ፈለኮች፣ ፕላኔቶች፣ ምህዳሮች፣ ፍኖተ-ሃሊብ፣ ክላስተሮች፣ እና ኡድማሳትን በዘመናችን ለሥነ-ፈለክ ተመራማሪዎች አሳይቷቸዋል፤ በአጽናፎች ያሉትን ነገሮች አላህ የሰራቸው የአላህ ታምራት ሲሆኑ እነዚህ ታምራት ወደፊት በማሳየት እንደሚያሳውቀን ተናግሮ ነበር፡-
27:93 ምስጋና ለአላህ ነው፤ #ታምራቶቹን ወደፊት #ያሳያችኋል፤ #ታውቁታላችሁ በላቸው።

እነዚህ አላህ የሰራቸው ታምራት ለማሳያነት በወፍ በረር ለቅምሻ ያክል እንመልከት፡-

ማሳያ አንድ
“አዞን”
የመሬት ከባቢ አየር በመሬት ዙሪያ የሚገኝ የጋዝ ክምችት ሲሆን ይህም ከባቢ አየር በውስጡ 78% ናይትሮጅን፣ 21% አክስጅን፣ 0.93% አርገን፣ 0.038% ካርቦን ዳይኦክሳይድ የተባሉ ንጥረ ነገሮችን በውስጡ ይዟል፤ የከባቢ አየር የላይኛው ክፍል ማለትም ስትራቶስፌር ወደ ምድር ከሚመጣው አልትራቫዮሌት ጨረር ውስጥ 99% የሚሆነውን ውጦ የሚያስቀረውን “አዞን”ozone (O3) የተባለ የኦክስጅን ቅንብር ይዟል፤ በመሆኑም ይህ የአዞን ሽፋን ሰዎችንና ፕላንክተን የሚባሉትን በባሕር ውስጥ የሚገኙ ጥቃቅን እጽዋትንና እንስሳትን ጨምሮ ሕይወት ያላቸውን ነገሮች በሙሉ ከጠፈር ከሚመጣ አደገኛ ጨረር ይከላከላል፤ ይህም የአዞን ሽፋን ለምድር አስደናቂና አስተማማኝ ከለላ እንዲሆናት አስችሏል፤ ከዚህም በተጨማሪ ይህ አዞን በየዕለቱ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሚቲሮይድስ በተባሉ ከህዋ ከሚመጡ ተወርዋሪ አካላት እንዳንደበደብ ይከላከልልናል፤ እነዚህ ሚቲሮይድስ ከትንሽ ቅንጣት እስከ ትልቅ ድንጋይ የሚደርስ መጠን አላቸው፤ ደግነቱ ከእነዚህ ሚትሮይድስ መካከል አብዛኞቹ በከባቢ አየር ውስጥ ተቃጥለው ይጠፋሉ፤ በዚህ ጊዜ ኃይለኛ ብርሃን ስለሚፈጥሩ ሚቲዮር ወይም ተወርዋሪ ኮከቦች ተብለው ይጠራሉ፤ ይህን አዞን ለፕላኔታችን ይህንን ሁሉ የሚከላከል ጣራያ ነው፤ ሁሉን አዋቂ አላህ የህዋ ተመራማሪዎች በዘመናችን ከማወቃቸው በፊት በተከበረው ቃል የአዞንን ሰማይ ለእኛ “ቢናእ” بِنَاء የሆነ መከላከያ እንደሆነ ነግሮናል፤ “ቢናእ” ማለት “ጣሪያ” ማለት ነው ፡-

40:64 አላህ ያ ምድርን መርጊያ #ሰማይንም #ጣሪያ ءبِنَاءً ያደረገላችሁ ነው፤
21:32 #ሰማይንም #የተጠበቀ #ጣራያ سَقْفًا ደረግን፤ እነርሱም #ከታምራቶቿ ዘንጊዎች ናቸው።
2:22 እርሱ ያ ለእናንተ ምድርን ምንጣፍ #ሰማይንም #ጣራያ ءبِنَاءً ያደረገ ነው፤ ከሰማይም ውሃን ያወረደ በእርሱም ከፍሬዎች ለእናንተ ሲሳይን ያወጣ ነው።።
52፥5 ከፍ በተደረገው #ጣሪያ ع وَٱلسَّقْفِ ٱلْمَرْفُو ::

በሰማይ አየር ውስጥ ወፎች እንዳይወድቁ የሚይዛቸው አላህ “ኤሮዳይናሚክ”Aerodynamics” በሚባል ህግ ነው፤ ይህንን ህግ በ 1799 AD የንስር ወፍ ንድፍ ታይቶ አይሮፕላን የተሰራ ሲሆን ይህም አላህ “በአጽናፎቹ ውስጥ ያሉትን ታምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን” ብሎ በተናገረው ቃል መሰረት እኛም መንገደኛ ሆነን በመንገደኞች ባለቤት በሆነችው ሰማይ ላይ አይሮፕላን እንደ ንስር ሲበር በዘመናችን አይተናል፦
16:79 ወደ #በራሪዎች #በሰማይ #አየር #ውስጥ ለመብረር የተገሩ ሲሆኑ ከመውደቅ አላህ እንጂ ሌላ የማይዛቸው ኾነው አይመለከቱምን? በዚህ ውስጥ ለሚያምኑ ሕዝቦች በእርግጥ #ታምራቶች አሉ።
51፥7 #የመንገዶች #ባለቤት በሆነችው #ሰማይ እምላለሁ።

ታዲያ በበረሃ ግመል ገፊ ነው ተብሎ በሚነገርላቸው ላይ ይህ ሁሉ እውቀት እንዴት ተሸጎደጎደ? ስንል፤ ይህንን እውቀት የዛሬ 1407 ዓመት ያ በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለውን ምስጢር የሚያውቀው አወረደው ይሆናል መልሱ፦
25:6 ያ በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለውን ምስጢር የሚያውቀው አወረደው፤ እርሱ መሐሪ አዛኝ ነውና፤ በላቸው።

ሥነ-ፈለክ

ክፍል ሁለት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

27:93 ምስጋና ለአላህ ነው፤ ታምራቶቹን ወደፊት ያሳያችኋል፤ ታውቁታላችሁ በላቸው።

ማሳያ ሁለት
“ከዋክብት”
አላህ የዓለማት ጌታ ነው፤ “ዓለሚን” عٰلَمِين ማለት “ዓለማት” ማለት ሲሆን የዘመናችን የሥነ-ፈለክ አስተንታኞች “መልቲ-ቨርስ”multi-verse” ይሉታል፤ ይህም ህልቆ-መሳፍት የሆነውን አድማስና አፅናፍ ለማመልከት ይጠቀሙበታል፤ “አዕለም” أَعْلَم የዐለሚን ነጠላ ሲሆን ‘ዐልለመ” عَلَّم “አሳወቀ” ከሚለው ግስ የመጣ ሲሆን “ዓለም” ወይም “የታወቀ” ማለት ነው፤ አላህ በእኛ ዘመን ባሉት ያሳወቀው እኛ ያለንባት አንድ ዓለም “ዩኒ-ቨርስ”uni-verse” ነው፤ የእኛ ዓለም ከ 170 billion እስከ 200 billion “ረጨት”galaxy” ይዟል፤ “ረጨት” ማለት የከዋክብት ስብስብ ሲሆን የእኛ ረጨት “ፍኖተ-ሃሊብ”Milky Way” ረጨት ይባላል፤ ይህ ረጨት ውፍረቱ 1000 የብርሃን አመት ይገመታል፤ ከአንዱ ጫፍ እስከሌላኛው ጫፍ ያለው ርቀት በዲያሜትር ሲለካ ደግሞ 100,000 የብርሃን ዓመት ይሆናል፤ በውስጡ ከ100 እስከ 400 ቢልዮን ከዋክብቶች እንደያዘ ይገመታል።
ይህንን የከዋክብት ረጨት”constellation” አምላካችን አላህ የዛሬ 1407 ዓመት በቁርአን “ቡሩጅ” ج بُرُو ይለዋል፦

85:1 #የቡርጆች ج ٱلْبُرُو ባለቤት በሆነችው ሰማይ እምላለሁ፤

25:61 ያ በሰማይ #ቡርጆችን بُرُوجًا ያደረገና በርሷም አንጸባራቂን ፀሐይ አብሪ ጨረቃንም ያደረገ ጌታ ክብሩ በጣም ላቀ።

15:16 በሰማይም ላይ #ቡርጆችን بُرُوجًا በእርግጥ አድርገናል።፤ ለተመልካቾችም አጊጠናታል።።

በፍኖተ-ሃሊብ ረጨት ውስጥ “ጻሕል”disk” መስለው በምህዋር”axis” እና “ሹረት”rotation” የሚታዩን ከዋክብት በቅርቢቱ ሰማይ ላይ የሚበሩ ጌጥ ሆነው ነው፡-
37:6 እኛ ቅርቢቱን ሰማይ #በከዋክብት ጌጥ አጌጥናት።
41:12 ቅርቢቱንም ሰማይ #በመብራቶች አጌጥን፤ መጠበቅንም ጠበቅናት፤
67:5 ቅርቢቱን ሰማይም በእርግጥ #በመብራቶች አጌጥናት፤

አላህ የዛሬ 1400 ዓመት በተከበረው ቃሉ በቁርአን “በአጽናፎቹ ውስጥ ያሉትን ታምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን” ብሎ ቃል ገብቶ ነበር፡-
41፡53 እርሱም ቁርአን እውነት መሆኑ ለነርሱ እስከሚገለጽላቸው ድረስ፣ #በአጽናፎቹ #ውስጥ እና በራሶቻቸውም ውስጥ #ያሉትን #ታምራቶቻችንን በእርግጥ #እናሳያቸዋለን፤ ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ መሆኑ አይበቃቸውምን?

ታዲያ በበረሃ ግመል ገፊ ነው ተብሎ በሚነገርላቸው ላይ ይህ ሁሉ እውቀት እንዴት ተቸርጎደጎደ? ስንል፤ ይህንን እውቀት የዛሬ 1407 ዓመት ያ በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለውን ምስጢር የሚያውቀው አወረደው ይሆናል መልሱ፡-
25:6 ያ በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለውን ምስጢር የሚያውቀው አወረደው፤ እርሱ መሐሪ አዛኝ ነውና፤ በላቸው።

ሥነ-ፈለክ

ክፍል ሶስት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

27:93 ምስጋና ለአላህ ነው፤ ታምራቶቹን ወደፊት ያሳያችኋል፤ ታውቁታላችሁ በላቸው።

ማሳያ ሁለት
“ደመና”
ለህዋ ምርምር መሰረቱ ሥነ-ፈለክ ነው፤ ሰዎች የከዋክብትን ኑባሬ ለማወቅ ያደረጉበት ሂደት ነው ከባቢ አየር እና ደመና ምን እንደሆነ ለማወቅ ያጓጓቸው፤ ደመና ብዙ ዝናብንና በረዶን አስገኚ ነው፤ በቁርአን “ቁራጭ” ተብሎ የተረጎመው ቃል “ኪሰፍ” كِسَف ሲሆን “ቅሪት*fragment* ማለት ነው፣ ይህም ቅሪት ደመና ነው፣ይህን ደመና በረዶ ሆኖ ሲወርድ የሰማይ ቅሪት ይባላል፡-
30:48 አላህ ያ ነፋሶችን የሚልክ ነው፤ ደመናንም ይቀሰቅሳሉ፤ #በሰማይ ላይም እንደሚሻ ይዘረጋዋል፤ #ቁርጥራጮችም كِسَفًا *ያደርገዋል*፤
24:43 አላህ ደመናን የሚነዳ መሆኑን አላየህምን? ከዚያም ከፊሉን ከከፊሉ ያገናኛል፤ ከዚያም የተደራረበ ያደርገዋል፤ ዝናሙንም ከመካከሉ የሚወጣ ሆኖ ታየዋለህ፤ ከሰማይም #ከደመና በውስጧ ካሉት #ጋራዎች #በረዶን ያወርዳል፤

የሚያጅበው ነገር አንድ ሰው ከደመና በላይ ሆኖ በአይሮፕላን ሲጓዝ ደመናውን ሲመለከተው ልክ እንደ ጋራ ነው፤ ይህን ጉዳይ አላህ የዛሬ 1400 ዓመት በተከበረው ቃሉ፡- “ከደመና በውስጧ ካሉት ጋራዎች በረዶን ያወርዳል” ብሎ ሲናገር በዘመኑ ያሉ ሰዎች ይህንን ጉዳይ ላይረዱት ይችላሉ፤ ሁሉን አዋቂው አላህ ከዚህ የደመና ጋራ በረዶን እንደሚያወርድ ዛሬ በአይናችን ላየነው ሰዎች አላህ፡- “በአጽናፎቹ ውስጥ ያሉትን ታምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን” ብሎ የተናገረው የትንቢት ባለቤት ምንኛ ታማኝ ነው? ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዝናብ ከደመና እንደሚመጣ ቅቡል ቢሆንም ይህ ውሃ ተኖ ወደ ሰማይ እንደሚሄድ ቁርአን ይናገራል፤ “ትነተ-ስርገት”Evaporation” ውሃው ወደ ላይ ሰራጊ መሆኑ የተረጋገጠው በኬነቲክ በ 1905 AD ላይ ነው፣ አላህ ግን ሰማይ የመመለስ ባለቤት መሆኗንና እርሱ ይህንን ውሃ እንደሚያወርደው ይናገራል፡-
67:30 አያችሁን? ውሃችሁ #ሰራጊ ቢሆን #ፈሳሺን ውሃ #የሚያመጣላችሁ ማን ነው? በላቸው።
86:11 #የመመለስ #ባለቤት በሆነችው #ሰማይም እምላለሁ።
56:68-69 ያንንም #የምትጠጡትን #ውሃ አያችሁን? እናንተ #ከደመና #አወረዳችሁትን? ወይስ እኛ አውራጆቹ ነን?

“ነብበአ” نَبَّأَ የሚለው ቃል ትርጉሙ “ትንቢት” ወይም “የሩቅ ወሬ” ማለት ሲሆን ይህን የሩቅ ነገር “በአጽናፎቹ ውስጥ ያሉትን ታምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን”፣ “ታምራቶቹን #ወደፊት ያሳያችኋል ታውቁታላችሁ” ” ትንቢቱን ወደፊትም ከጊዜ በኋላ ታውቁታላችሁ” ብሎ ቃል በገባልን ትንቢት መሰረት ዛሬ በዘመናችን አሳይቶናል አሳውቆናል፣ ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ምስጋና ሁሉ ይሁን፡-
6፤67 “#ለትንቢት” نَبَإٍ ሁሉ የሚደርስበት መርጊያ አለው፡፡ #ወደፊትም #ታውቁታላችሁ፡፡
38፥88 #ትንቢቱንም” ۥنَبَأَهُ #ከጊዜ #በኋላ በእርግጥ #ታውቁታላችሁ፡፡»

ምድር

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

30:22 ሰማያትንና “ምድርንም” መፍጠሩ፥ የቋንቋዎቻችሁና የመልኮቻችሁም መለያየት “ከአስደናቂ “ታምራቶቹ” ءَايَاتِهِۦ ነው፤ በእዚህ ውስጥ ለአዋቂዎች “ታምራቶች” ءَايَاتٍ ለአሉበት።

መግቢያ
ሥነ-ምድር ጥናት “ጂኦ-ሎጂ”Geo-logy” ሲባል በግሪክ “ጂኦ” γῆ, ማለት “ምድር” ማለት ሲሆን ” ሎጂአ” λογία ደግሞ “ጥናት” ነው፤ አምላካችን አላህ በተከበረው ከሊማ “አርድ”أَرْض ብሎ የሚናገረው “ምድር” ወይም “መሬት” አሊያም “አገርንም” ማለት ነው፤ ይህንን ማየት ይቻላል፡-

1. “ፕላኔት”

አላህ “አርድ” እያለ ከሰማይ ጋር በተያያዘ መልኩ አብዛኛውን የሚገልፀው የምንኖርባትን ፕላኔት ነው፡-
32:4 አላህ ያ ሰማያትንና “ምድርን” وَالْأَرْض በመካከላቸውም ያለውን ሁሉ በስድስት ቀናት ውስጥ የፈጠረ፣ ከዚያም በዐርሹ ላይ የተደላደላ ነው፤
11:7 እርሱም ያ ሰማያትንና “ምድርን” وَالْأَرْض በስድስት ቀኖች የፈጠረው ነው፤
7:54 ጌታችሁ ያ ሰማያትንና “ምድርን” وَالْأَرْض በስድስትቀናት ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው፤
50:38 ሰማያትንና “ምድርን” وَالْأَرْض በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ በስድስት ቀናት ውስጥ በእርግጥ ፈጠርን፡፡ ድካምም ምንም አልነካንም፡፡

2. “መሬት”

“መሬት” ሰዎች የሚኖሩበት ሲሆን ሰዎች የሚኖሩበትን ይህን የላይኛውን ቅርፊት “አርድ” ይለዋል፡-
16:13 “በምድርም” الْأَرْض ላይ መልኮቹ የተለያዩ ኾኖ ለናንተ የፈጠረላችሁን ሁሉ ገራላችሁ፤ በዚህ ውስጥ ለሚገሠጡ ሕዝቦች በእርግጥ ታምር አለ።
67:24 እርሱ ያ “በምድር” الْأَرْض ላይ የበተናችሁ ነው፤ ወደርሱም ትሰበሰባላችሁ በላቸው።
23:79 እርሱም ያ “በምድር” الْأَرْض ውስጥ የበተናችሁ ነው፤ ወደርሱም ትሰበሰባላችሁ፡፡

3. “አገር”
ሰዎች ተለያይተው የሚኖሩበትን አገር “አርድ” ይለዋል፡-
17:76 “ከምድሪቱም” الْأَرْض ከእርሷ ያወጡህ ዘንድ ሊያሸብሩህ፣ በእርግጥ ተቃረቡ፤ ይአን ጊዜም ከአንተ በኋላ ጥቂትን ጊዜ እንጂ አይቆዩም ነበር።
21:71 እርሱንና ሉጥንም ወደዚያች፤ በውስጧ ለዓለማት በረከትን ወደ አደረግንባት “ምድር” الْأَرْض በመውሰድ አዳን።
21:81ለሱለይማም ነፋስን በኀይል የምትነፍስ በትእዛዙ ወደዚያች በርሷ ውስጥ በረከትን ወደ አደረግንበት “ምድር” الْأَرْض የምትፈስ ስትሆን ገራንለት፤
12:56 እንደዚሁም ለዩሱፍ “በምድር” الْأَرْض ላይ ከእርሷ በፈለገው “ስፍራ የሚሰፍር” ሲሆን አስመቸነው፤

ይህንን እሳቤ ይዘን ስለ ምድር ያለንን ግንዛቤ በቀላሉ መረዳት ይቻላል፤ የምድርን ሹረት፣ ቅርፅና ንጣፍ ነጥብ በነጥብ እንመልከት፡-

ነጥብ አንድ
“የምድር ሹረት”
የስነ-ፈለክ ጥናት ታሪክን ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት “ምድር” የስርዓተ-ፈለክ እምብርት”Geocentric” ናት ተብሎ በጥንት ይታመን ነበር፣ ነገር ግን በ1533 AD ኒክላስ ኮፐርኒኮስ ምድር ሳትሆን ፀሐይ የስርዓተ-ፈለክ እምብርት”Heliocentric” ናት ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ለዓለማችን አበረከተ፣ የመሬት ሹረት የሚባለው ምድር በደቡብና በሰሜን በሚገኙት ዋልታዎ”Poles” ከምዕራብ ወደ ምስራቅ በራሷ ዛቢያ በ 360 ድግሪ ስትሽከረከር መአልት እና ሌሊት ይፈራረቃል፤ ይህ ሂደት በአማካኝ 24 ሰአት ይፈጃል፤ ይህን ሂደት የሥነ-ፈለክ ምሁራን “ሹረት”Rotation” ይሉታል፤ እውነት ነው ምድር ጠፍጣፍ ብትሆን ኖሮ ሌሊት ሲሆን ሁሉም የምድር ይዞታ ላይ ጨለማ እና መአልት ሲሆን ደግሞ ሁሉም የምድር ይዞታ ላይ ብርሃን ይሆን ነበር፤ ነገር ግን ምድር በራሷ ዛቢያ ስለምትሽከረከር መአልትና ሌሊት በአንድ ጊዜ እየተደራረቡ ይፈራረቃሉ፤ ለምሳሌ ኢትዮጵያ ብርሃን ሲሆን አሜሪካ ጨለማ መሆኑ ማለት ነው፤ ይህንን ሁኔታ ኮፐርኒከስ ከመናገሩ በፊት በሰማይና ምድር ላይ ያለውን ክስተት ሁሉ የሚያውቀው አምላክ በተከበረ ቃሉ ተናግሯል፡-

39:5 ሌሊትን በቀን ላይ “ይጠቀልላል” يُكَوِّرُ ቀንንም በሌሊት ላይ “ይጠቀልላል” يُكَوِّرُ ።

በዚህኛው አንቀጽ “ኩውወረት” تَكْوِيرَ የሚለውን ቃል “መጠቅለል” ወይም “መደራረብ”Overlap” ማለት ነው፤ አንድ ሰው ጥምጣም በራሱ ጭንቅላት ላይ እነደሚጠቀልል ማለት ነወ፤ ይህ የሚሆነው ምድር በደቡብና በሰሜን በሚገኙት ዋልታዎ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ በራሷ ዛቢያ በ 360 ድግሪ ስትሽከረከር ብቻ ነው፤ አላህ ሌሊትን በቀን ውስጥ ቀንንም በሌሊት ውስጥ በመተካካት የሚያስገባ መሆኑን በብዙ አንቀፆች ይናገራል፤ በዚህም ውስጥ ለሚያስተነትኑ ባለ አእምሮዎች ታምራቶች አሉበት፡-
35:13 ሌሊትን በቀን ውስጥ #ያስገባል፤ ቀንንም በሌሊት ውስጥ #ያስገባል፤
57:6 ሌሊትን በቀን ውስጥ #ያስገባል፤ ቀንንም በሌሊት ውስጥ #ያስገባል፤ እርሱም በልቦች ውስጥ የተደበቁትን ዐዋቂ ነው።
31:29 አላህ ሌሊትን በቀን ውስጥ #የሚያስገባ ቀንንም በሌሊት ውስጥ #የሚያስገባ፣ ፀሐይንና ጨረቃን የገራ፣ መኾኑን አታይምን?
22:61 አላህ ሌሊትን በቀን ውስጥ #የሚያስገባ፣ ቀንንም በሌሊት ውስጥ #የሚያስገባ ቻይ ነው፣ አላህም ሰሚ ተመልካች በመሆኑ ነው።
3:190 ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር፣ ሌሊትና ቀንም #በመተካካት፥ ለባለ አእምሮዎች በእርግጥ “ታምራቶች” ءَايَٰتٍ አሉ።
13:3 ሌሊትን በቀን #ይሸፍናል፤ በዚህም ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች “ታምራቶች” ءَايَٰتٍ አሉ።

ምድር ሞላላ ከመሆን ፋንታ ልክ እንደ ሳንቲም ጠፍጣፋ ብትሆን ኖሮ ሌሊት ወደ መአልት እንዲሁም መአልት ወደ ሌሊት የሚያደርጉት ለውጥ ዝግመታዊ ሳይሆን ቅፅበታዊ ይሆን ነበር፤ የሚቀጥለው ነጥብ የምድርን ሞላላነትን ይሞግታል፡-

ነጥብ ሁለት
“የምድር ቅርፅ”
በነጥብ አንድ ላይ የመአልትና የሌሊት መፈራረቅ በመተካት መሆኑን እና የዚህ መፈራረቅ መንስኤ ደግሞ የምድር በራሷ ዛቢያ መሽከርከር አይተን ነበር፤ ታዲያ ምድር ያለ ምንም በራሷ ዛቢያ ስትዞር አትወድቅም ወይ? ለሚለው አንዱ በአንዱ ባለው የመሳሳብ ህግ”Gravity” እዳትወድቅ ያረጋታት፤ በዚህ ህግ አርቅቆ የያዛት አላህ ብቻ ነው፤ ይህ በትእዛዙ እንዳትወድቅ መቆሟ ከአስደናቂ ታምራቶቹ አንዱ ነው፡-
35፥41 አላህ ሰማያትንና ምድርን #እንዳይወገዱ #ይይዛቸዋል:: ቢወገዱም ከእርሱ ሌላ አንድም የሚይዛቸው የለም:: እነሆ እርሱ ታጋሽ መሓሪ ነውና::
30፥25 ሰማይና ምድርም ያለምንም #በትዕዛዙ #መቆማቸው وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦٓ أَن تَقُومَ ٱلسَّمَآءُ وَٱلْأَرْضُ بِأَمْرِهِۦ ፤ ከዚያም ከምድር ጥሪን በጠራችሁ ጊዜ እናንተ ወዲያውኑ የምትወጡ መሆናችሁ ከአስደናቂ “ታምራቶቹ” ءَايَٰتِهِۦٓ ነው::

ምድር ሆነ ሰማይ ሰማያዊ አካላት ሁሉ ያለምንም ድጋፍ በአላህ ህግ ሳይወድቁ መቆማቸው ብቻ ሳይሆን በትእዛዙ መንቀሳቀሳቸው ደግሞ ታምር ነው፡-

41፥11 ከዚያም ወደ ሰማይ እርሷ “ጭስ” دُخَانٌ ኾና ሳለች አሰበ፡፡ #ለእርሷም #ለምድርም «ወዳችሁም ኾነ ወይም ጠልታችሁ ኑ» አላቸው፡፡ «#ታዛዦች ኾነን #መጣን» አሉ፡፡

ይህ አንቀፅ ምድርም እንደ ሰማይ ተንቀሳቃሽ መሆኑን ያሳያል፤ ሰማይ “ዱኻን” دُخَان ሆና ሳለች የሚለው ይሰመርበት፤ “ዱኻን” ማለት “ጭስ”gas” ሲሆን ይህም ጋዝ ናይትሮጂን፣ ኦክሲጅንና ሃይድሮጂን ነው፤ እነዚህ የጋዝ ንጥረ-ነገር”element” ያላቸው አካላት ከዋክብት፣ ጨረቃ እና ፀሐይ ሆኑ ምድር ሁሉም በምህዋራቸው ይዞራሉ፡-

35:13 ሌሊትን በቀን ውስጥ ያስገባል፤ ቀንንም በሌሊት ውስጥ ያስገባል፤ ፀሐይን እና “ጨረቃንም” ገራ፤ ሁሉም እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ “ይሮጣሉ”፤ ይሃችሁ ጌታችሁ አላህ ነው፤

39:5 ሰማያትንና ምድርን በእውነት ፈጠረ፤ ሌሊትንም በቀን ላይ ይጠቀልላል፤ ፀሐይን እና “ጨረቃንም” ገራ፤ ሁሉም ለተወሰነ ጊዜ “ይሮጣሉ”፤ ንቁ እርሱ አሸናፊው መሐሪው ነው።

21:33 እርሱም ሌሊትና ቀንን ፀሐይንና ጨረቃንም፣ የፈጠረ ነው፤ ሁሉም በፈለካቸው ውስጥ ይዋኛሉ።

6:40 ፀሐይ ጨረቃን ልትደርስበት አይገባትም፤ ሌሊትም ቀንን ያለጊዜው ቀዳሚ አይሆንም፤ ሁሉም “በመዞርያቸው” ውስጥ “ይዋኛሉ”።

36:40 ፀሐይ ጨረቃን ልትደርስበት አይገባትም፤ ሌሊትም ቀንን ያለጊዜው ቀዳሚ አይሆንም፤ ሁሉም “በመዞርያቸው” ውስጥ “ይዋኛሉ”።

“ኩል” كُلّ“ሁሉ” የሚለው ቃል እና “የስበሁነ” يَسْبَحُون“ይዞራሉ” የሚለው ቃል ሙተና”dual” ሳይሆን ከሁለት በላይ “ጀመዕ”plurar” መሆኑ ፀሐይና ጨረቃ ብቻ ሳይሆን ተንቀሳቃሽ ሁሉ በዙረት ላይ መሆኑ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፤ “ፈለክ” فَلَك የሚለው ቃል “ምህዋር”orbit” ማለት ሲሆን ምድር በፀሐይ ዛቢያ ስትሽከረከር 365 ቀናት ይፈጃል፤ የዚህ ውጤት ከረምት፣ በጋ፣ ፀደይና መከር የተባሉ አራት ወቅቶች ይፈራረቃሉ፤ ይህ ሁሉ የሚሆነው ምድር ሞላላ ሆና ስትገኝ ነው፤ አላህ ምድር ሞላላ መሆኗን ይናገራል፡-

79፡27-30 “ባፈጣጠር እናንተ ይበልጥ የበረታችሁ ናችሁን? ወይስ ሰማይ? አላህ ገነባት፡፡ ከፍታዋን አጓነ ፣ አስተካከላትም፣ ሌሊቷንም አጨለመ ቀኗንም ገለፀ፡፡ ምድርንም ከዚህ በኋላ “ዘረጋት” دَحَاهَا፡፡”

“ዘረጋት” ተብሎ ቃል “ደሓሃ” دَحَاهَا ሲሆን “ደሓ” دَحَى ደግሞ በቁርአን ላይ የመጣው በግስ መደብ እዚህ አንቀፅ ላይ ብቻ ነው፤ “ደሓ” በስም መደብ ሲመጣ “አድ-ደሕያ” الدَّحْيَة ነው፤ ትርጉሙም “የሰጎን እንቁላል” ማለት ነው፤ አላህ ምድርን “የእንቁላል ቅርጽ አደረጋት”He made the earth egg-shaped” የሚል ትርጉም አለው፤ ይህንን አንዳንድ የእንግሊዝኛ ትርጉም ላይ ይገኛል፡-

1.Dr. Kamal Omar Translation

“And the earth, after this stage, He gave it an #oval #form”

2. Ali Unal Translation

“And after that He has spread out the earth in #the #egg-#shape”

3. Shabbir Ahmed Translation

“And after that He made the earth #egg-#shaped.

ስለዚህ ምድር እንደ ሰጎን እንቁላህ ሞላላ”ellipse” መሆኗን ሰዎች በዚህ ዘመን ከማስተንተናቸው በፊት አላህ ቀድሞ በቁርአን ተናግሯል፤ ይህ ሙግት የሥነ-ልሳን ሙግት ታሳቢ ያደረገ ነውና ዋቢ ሙዳየ-ቃላት ይመልከቱ፡-

1. Lisan Al-Arab dictionary , Book 7, Page 456:

2. Lisan Al-Arab dictionary , Book 2, Page 790.

3. Al-Mawrid dictionary Arabic-English section 4, Page 1132.
4. Al-Mawrid dictionary English-Arabic section 4, Page 227.
5. Arabic-English dictionary the Hans Wehr dictionary , Page 928.

ነጥብ ሶስት
“የምድር ንጣፍ”
ምድር ልክ እንደ ሰጎን እንቁላል ቅርፅ እንዳላት ካየን ዘንዳ አሁን ደግሞ የምድርን ንጣፍ ከእንቁላል ጋር የሚያመሳስላትን ነገር እናያለን፤ የምድር መዋቅር ልክ እንደ እንቁላል ሶስት ክፍል አለው፤ እርሱም፡-
1ኛ. የላይኛው ቅርፊት “ክረስት”crust” ይባላል፣በአብዛኛው ከተለያዩ የቋጥኝ አይነቶች የተገነባ ሲሆን ህይወት ያላቸው ነገሮች በሙሉ የሚኖሩት በዚህኛው የመሬት ክፍል ላይ ነው፤ ይህ ክፍል ውፍረቱ በውቅያኖሶች ስር ያለው ውፍረት 5000 ሜትር እስከ 10000 ሜትር ሲሆን በአህጉሮች ላይ ደግሞ 30 ኪሎ ሜትር እስከ 50 ኪሎ ሜትር ነው፤ ይህም በእንቁላል የላይኛው ቅርፊት ጋር ይመሳሰላል።

2ኛ. የመካከለኛው ፈሳሽ ክፍል “ማንትል”mantle” ይባላል፤ ፈሳሽ የሆነ “ቅልጥ አለት”Magma” በከፍተኛ የሙቀት መጠን የቀለጠ አለት ነው፤ ይህም በእንቁላል የመካከለኛው ነጭ ፈሳሽ ጋር ይመሳሰላል።

3ኛ. የውስጠኛው አስኳል ክፍል “ኮር”core” ይባላል፤ይህ ክፍል እጅግ በጣም ሞቃት ሲሆን የፀሐይን የውጨኛ ክፍል መጠነ ሙቀት ይኖርዋል፤ ይህ ክፍል መጠኑ አነስተኛ ሲሆን በራዲየስ እስከ 1220 ኪሎ ሜትር ነው፤ በእንቁላል የውስጠኛው አስኳል ጋር ይመሳሰላል።

ይህንን ግንዛቤ ይዘን ለሰዎች መኖሪያ የሆነው የላይኛው የምድር ቅርፊት አላህ ለእኛ ዝግር አድርጎ ፈጥሯል፤ መዘርጋት ከእኛ እይታ አንጻር ነው፤ ለዛ ነው ብዙ አናቅፅ ላይ አላህ “ለኩም” لَكُم “ለእናንተ” የሚለው ሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስም የሚጠቀመው፡-
2፥22 እርሱ ያ *ለእናንተ* لَكُمُ’ምድርን ምንጣፍ ሰማይንም ጣራ ያደረገ ነው፤
20፥53 እርሱ ያ ምድርን *ለእናንተ* لَكُمُ’ምንጣፍ ያደረገላችሁ፣
43፥10 እርሱ ያ ምድርን *ለእናንተ* لَكُمُ’ምንጣፍ ያደረገላችሁ፣
71፥19 አላህም ምድርን *ለእናንተ* لَكُمُ’ምንጣፍ አደረጋት።

አላህም ምድርን ለእኛ ምንጣፍ ያደረገበት ምክንያት “ከእርሷ ሰፋፊዎችን መንገዶች ትገቡ ዘንድ” ነው ይለናል፤ መኪና ስንነዳ መንገዶች ሁሉ ለእኛ ዝርግ ናቸው፡-
71፡19-20 አላህም ምድርን *ለእናንተ* لَكُمُ’ምንጣፍ አደረጋት፤ ከእርሷ ሰፋፊዎችን “”መንገዶች ትገቡ ዘንድ””።
43፥10 እርሱ ያ ምድርን *ለእናንተ* لَكُمُ’ምንጣፍ ያደረገላችሁ፣በእርሷም ውስጥ ትመሩ ዘንድ “”ለእናንተ መንገዶችን”” ያደረገላችሁ ነው።

በእርግጥ አላህ የፈጠረውን ምድር ታምር ነው፤ለሚያስተነትኑ አዋቂዎች ታምር አለበት፤ ወደፊት ይህንን ታምር ያሳያችኋል፤ ታውቁታላችሁ ብሎ ቃል በገባልን ኪዳን በዘመናችን አሳይቶናል ፡-
30:22 ሰማያትንና “ምድርንም” መፍጠሩ፥ የቋንቋዎቻችሁና የመልኮቻችሁም መለያየት “ከአስደናቂ “ታምራቶቹ” ءَايَٰتِهِۦ ነው፤ በእዚህ ውስጥ ለአዋቂዎች “ታምራቶች” لِّلۡعَٰلِمِينَ አሉበት።
27:93 ምስጋና ለአላህ ነው፤ #ታምራቶቹን ወደፊት ያሳያችኋል፤ ታውቁታላችሁ በላቸው።

ሥነ-ፅንስ

ክፍል አንድ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

31:34 አላህ የሰዓቲቱ እውቀት እርሱ ዘንድ ብቻ ነው፤ ዝናምንም ያወርዳል፤ #በማሕፀኖችም #ውስጥ #ያለን #ሁሉ #ያውቃል፤

መግቢያ
ሥነ-ፅንስ ጥናት ኢምብሪዮሎጂይ”Embryology” ሲባል “ኢምብሮ” ἔμβρυον “ያልተወለደ” እና “ሎጂአ” λογία, “ጥናት” ከሚል ሁለት የግሪክ ቃል የተዋቀረ ነው፤ ይህንን ፅንስ እናቱ ማህፀን ውስጥ በሚፈልገው መልኩ የሚቀርፀው አንዱ አምላክ አላህ ነው፡-
3:6 እርሱ ያ “በማሕፀኖች” ዉስጥ እንደሚሻ አድርጎ “የሚቀርጻችሁ” ነዉ፤ ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤

ይህ ፅንስ ማህፀን ውስጥ እንዴት እንደሚፈጠር ሙሉ እውቀት ያለው የዓለማቱ ጌታ አላህ ብቻ ነው፡-
31:34 አላህ የሰዓቲቱ ዕውቀት እርሱ ዘንድ ብቻ ነው፤ ዝናምንም ያወርዳል፤ “በማሕፀኖችም ውስጥ ያለን ሁሉ ያውቃል”፤
53:32 ከምድር በፈጠራችሁ ጊዜ እናንተም በእናቶቻችሁ “ማሕፀኖች” ውስጥ ሽሎች በሆናችሁ ጊዜ እርሱ በእናንተ ሁኔታ “አዋቂ” ነው።
13:8 አላህ ሴት ሁሉ የምታረግዘውን ያውቃል፤ “ማሕፀኖችም የሚያጐድሉትን የሚጨምሩትንም፥ ያውቃል”፤ ነገሩም ሁሉ እርሱ ዘንድ በልክ የተወሰነ ነው።

በማሕፀኖችም ውስጥ ያለውን ሁሉ የሚያውቀ አምላክ የሥነ-ፅንስ እውቀት ወደፊት እንደሚያሳየና እንደሚያሳውቀን ለማመልከት፡- “በራሶቻችሁ ውስጥ ያሉትም ታምራት ወደፊት ያሳያችኋል፤ ታውቁታላችሁ” በማለት ቃል ገብቷል፡-
41፥53 እርሱም ቁርአን እውነት መሆኑ ለነርሱ እስከሚገለጽላቸው ድረስ፣ በአጽናፎቹ ውስጥ እና #በራሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን #ታምራቶቻችንን በእርግጥ #እናሳያቸዋለን፤ ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ መሆኑ አይበቃቸውምን?
27:93 ምስጋና ለአላህ ነው፤ #ታምራቶቹን #ወደፊት #ያሳያችኋል፤ #ታውቁታላችሁ በላቸው።

አላህ ይህንን እውቀት በራሳችን አካላት ከማሳየቱ በፊት በቁርአን አንድ ሽል በማህፀን ውስጥ እንዴት የተለያየ ደረጃዎችን”stages” እንደሚያሳልፍ በተከበረ ቃሉ ይነግረናል፡-
23:12 በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው፤ ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ “የፍትወት ጠብታ” نُّطْفَةً አደረግነው፤ ከዚያም ጠብታዋን “የረጋ ደም” عَلَقَةً አድርገን ፈጠርን፤ የረጋውንም ደም “ቁራጭ ሥጋ” مُضْغَةً አድርገን ፈጠርን፤ ቁራጪንም ሥጋ “አጥንቶች” عِظَامًا አድርገን ፈጠርን፤ አጥንቶቹንም ሥጋን لَحْمًا አለበስናቸው፤ ከዚያም “ሌላ ፍጥረትን” خَلْقًا آخَرَ አድርገን “አስገኘነው” أَنشَأْنَاهُ፤ ከሰዓሊዎችም ሁሉ በላጭ የሆነው አላህ ላቀ።

ደረጃ አንድ
“ኑጥፋህ”
የአንድ ሽል በማህፀን ያለው የመጀመሪያ ደረጃ “ኑጥፋህ” نُّطْفَةً ነው፤ “ኑጥፋህ” ማለት “የፍትወት ጠብታ” ሲሆን ይህም የተባእት ዘር ህዋስ” sperm cell” እና የእንሥት እንቁላል ህዋስ”egg cells” ነው፤ እነዚህ የፍትወት ጠብጣዎች በሥነ-ፅንስ ምሁራን “ፍናፍንት”hermaphroditic” በመባል ይታወቃሉ፤ አላህ ስለዚህ የፍትወት ጠብታ በተከበረ ቃሉ እንዲህ ይለናል፡-
53:45-46 እርሱም ሁለቱን ዓይነቶች ወንድና ሴትን ፈጠረ። “ከፍትወት ጠብታ” نُّطْفَةٍ በማኅፀን ውስጥ በምትፈስ ጊዜ፤

80:19 “ከፍትወት ጠብታ” ٱنُطْفَة ፈጠረው መጠነውም።
16:4 ሰውን “ከፍትወት ጠብታ” ٱنُطْفَة ፈጠረው፤ ከዚያም እርሱ ወዲያውኑ ትንሣኤን በመካድ ግልጽ ተከራካሪ ይሆናል።
35:11 አላህም ከአፈር፣ ከዚያም “ከፍትወት ጠብታ” ٱنُطْفَة ፈጠራችሁ፤
36:77 ሰውየው እኛ “ከፍቶት ጠብታ” የፈጠርነው መሆናችን አላወቀምን?
40:67 እርሱ ያ ከአፈር፣ ከዚያም “ከፍትወት ጠብታ” ٱنُطْفَة ፣ ከዚያም ከረጋ ደም፣ የፈጠራችሁ ነው።

የሴት ልጅ ማህፀን ዘር በሚዘራበት “እርሻ” ሲመሰል፤ የእንሥት ማህፀን ላይ ላይ የሚገናኘው የተባእት ዘር ህዋስ ደግሞ ገበሬ እርሻ ላይ በሚዘራው “ዘር” ተመስሏል፤ ምክንያቱም አንድ ገበሬ እርሻው ላይ ከዘራ በኃላ ዘሩ ዳብሮ ለፍሬ የሚበቃው በእርሻ ውስጥ እንደሆነ ሁሉ አንድ ተባእትም አንድ እንስት ማህፀን ውስጥ ዘሩን ተገናኝ ሆኖ ከዘራ በኃላ ሂደቱ ሁሉ ተከናውኖ ለፍሬ የሚበቃው ማህፀን ውስጥ ነው፡-
2:223 ሴቶቻችሁ ለእናንተ “እርሻ” ናቸው፤ እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ኹኔታ ድረሱ፤ ለነፍሶቻችሁም መልካም ሥራን አስቀድሙ፤ አላህንም ፍሩ፤ እናንተም “”ተገናኝዎቹ”” መኾናችሁን ዕወቁ፡፡
56:57-59 እኛ ፈጠርናችሁ፤ አታምኑምን? “በማኅፀኖች “የምታፈሱትን አያችሁትን”? እናንተ ትፈጥሩታላችሁን? ወይስ እኛ ፈጣሪዎቹ ነን።
56:63-64 “የምትዘሩትንም አያችሁን”? እናንተ ታበቅሉታላችሁን? ወይስ እኛ አብቃዮቹ ነን?
32:7-8 ያ የፈጠረውን ነገር ሁሉ ያሳመረው፣ የሰውንም ፍጥረት ከጭቃ የጀመረው፥ ነው፤ ከዚያም “ዘሮቹን”፣ ከተጣለለ “ከደካማ ውሃ” ያደረገ፣ ነው።
77:20-21 “ከደካማ ውሃ” አልፈጠርናችሁምን? “በተጠበቀ መርጊያ በማሕፀን ውስጥም” አደረግነው፤

አላህ በማህፀን ያለውን የመጀመሪያ ደረጃ ሰው እንዴት የተባእት ዘር ህዋስ እና የእንሥት እንቁላል ህዋስ ፍናፍንት ሆኖ ተቀላቅሎ እንደሚፈጠር ቀድሞውኑ በማሕፀኖችም ውስጥ ያለንውን ሁሉ አዋቂ አምላክ መሆኑን ለእኛ ለማሳየት “አምሻጅ” ٱمْشَاج “ቅልቅል”mixture” በማለት ይናገራል፡-
76:2 እኛ ሰዉን በሕግ ግዳጅ የምንሞክረዉ ስንሆን፥ “ቅልቅሎች” ٱمْشَاج ከሆኑ “የፍትወት ጠብታ” ٱنُطْفَة ፈጠርነዉ፤ ሰሚ ተመልካችም አደረግነዉ።

ሥነ-ፅንስ

ክፍል ሁለት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

31:34 አላህ የሰዓቲቱ እውቀት እርሱ ዘንድ ብቻ ነው፤ ዝናምንም ያወርዳል፤ #በማሕፀኖችም #ውስጥ #ያለን #ሁሉ #ያውቃል፤

“ደረጃ ሁለት”
“ዐለቃ”
“ዐለቃ” عَلَقَة አንስታይ ሲሆን “ዐለቅ” عَلَق ደግሞ ተባእታይ ነው፤ ትርጉሙም “አልቅት”leech” ወይም “የረጋ ደም”blood-clot” ማለት ነው፤ ይህን የፅንስ ሁለተኛው ደረጃ ከሚታይ አልቅት ከሚባል የባህር ትል”insect” እና ከረጋ ደም ጋር ስለሚመሳሰል ነው፤ ወደዚህ ሂደት ለመምጣት በህዋሳት ውህደት ወቅት “ክሮሞሶም”Chromosomes” ከአንዱ ለጋሽ ወላጅ ወደሌላው ለጋሽ ወላጅ ይተላለፋል፤ እያንዳንዱ ተሣታፊ ህዋስ የለጋሾችን ግማሽ ክሮሞሶም ይይዛል፤ የአባት ክሮሞሶም ግማሽ 23% የእናት ክሮሞሶም 23% ተገናኝተው 46% ይዋሃዳሉ ማለት ነው፤ ተወራሽ የዘር ምልክቶች በምፃረ-ቃል “ዲ-ኤን-ኤ”(DNA) ወይም በዝርዝር “ዲኦክሲሪቦ ኒውክሊክ አሲድ”(deoxyribonucleic acid) በመባል በሚታወቀው በክሮሞሶሞች ውስጥ የሚገኝ ንጥረ-ነገር ውስጥ ሰፍረው ይገኛሉ።

ክሮሞሶሞች “በጥንድ” ሆነው በሚገኙበት ጊዜ “ዳይፕሎይድ”(diploid) ይባላሉ፤ ክሮሞሶሞች በነጠላ ግዜ “ሃፕሎይድ”(haploid) ይባላሉ፤ በዚህ ሂደት አንድ ሴል የነበረው የወንድ የዘር ህዋስ ከሴት የእንቁላል ህዋስ ጋር ከተዋሐደ በኃላ 2, 4, 8, 16, 32, 64 እያለ በቲሪልየን ብዜት በ 21 ቀን የረጋ ደም”blood-clot” የሚለው ደረጃ ይጀምራል፤ ይህንን ደረጃ አምላካችን አላህ እንዲህ ይለናል፡-
22:5 እላንተ ሰዎች ሆይ! ከመቀስቀስ፣ በመጠራጠር ዉስጥ እንደ ሆናችሁ አፈጣጠራችሁን ተመልከቱ፤ እኛም ከአፈር ፈጠርናችሁ ከዚያም ከፍቶት ጠብታ፣ ከዚያም “ከረጋ ደም” عَلَقَةٍ ፣ ከዚያም ከቁራጭ፣ ስጋ ፍጥረትዋ ሙሉ ከኾነችና ሙሉ ካልሆነች ችሎታችንን ለእናንተ ልንገልጽላችሁ ፈጠርናችሁ፤
40:67 እርሱ ያ ከአፈር፣ ከዚያም ከፍትወት ጠብታ፣ ከዚያም “ከረጋ ደም” عَلَقَةٍ፤ የፈጠራችሁ ነው።
96:1-2 አንብብ በዚያ ሁሉን በፈጠረው ጌታህ ስም፤ ሰውን “ከረጋ ደም” عَلَقٍ በፈጠረው ጌታህ ስም።

ከፍትወት ህዋስ ወደ የረጋ ደም የሚሄድበት ሂደት እና ደረጃ ለማመልከት “ሱምመ” ثُمَّ“ከዚያም” የሚል መስተፃምር ይጠቀማል፤ ከዚህ ከተቀላቀለው የፍትወት ህዋስ ሁለት ዓይነቶችን ወንድና ሴትን ይመጣል፡-
75፥36-39 ሰው ስድ ሆኖ መትተውን ይጠረጥራልን? የሚፈስስ ከሆነ የፍትወት ጠብታ አልነበረምን? “ከዚያም” ثُمَّ“የረጋ ደም” عَلَقَةً ሆነ፤ ሰው አድርጎ ፈጠረውም፤ አስተካከለውም። “ከእርሱም” ሁለት ዓይነቶችን “ወንድና ሴትን” አደረገ።

“የዘረ-መል ጥናት”(Genetic) እንደሚያስተነትነው የተባእት ክሮሞሶም ‘XY’ ሲሆን የእንስት ክሮሞሶም ደግሞ ‘XX’ ነው፤ ከወንድ ‘Y” መጥቶ ከሴት ‘X’ ከመጣ ሽሉ የአባቱን ፆታ በመያዝ ወንድ ይሆናል፤ ከወንድ ‘X” መጥቶ ከሴት ‘X’ ከመጣ ሽሉ የእናቱን ፆታ በመያዝ ሴት ይሆናል፤ ልብ አድርግ የወንድ ክሮሞሶም ‘XY’ ሲሆን የሴት ክሮሞሶም ደግሞ ‘XX’ መሆኑ ማለቴ ነው፤ የዘረ-መል ጥናት ይህንን ከማወቁ በፊት አላህ ለመልእክተኛው ይህንን የሩቅ ነገር ሚስጥር አሳውቋል፡-
ኢማም ቡሃሪ መጽሐፍ 60 , ቁጥር 4 :
وَأَمَّا الشَّبَهُ فِي الْوَلَدِ فَإِنَّ الرَّجُلَ إِذَا غَشِيَ الْمَرْأَةَ فَسَبَقَهَا مَاؤُهُ كَانَ الشَّبَهُ لَهُ، وَإِذَا سَبَقَ مَاؤُهَا كَانَ الشَّبَهُ لَهَا ”.
የአላህ መልክተኛ አሉ፡- የልጆች ከወላጆቻቸው መመሳሰል እንዲህ ነው፤ ተባእት ከሚስቱ ጋር ተራክቦ ሲያደርግ የእርሱ ከተለቀቀ ህፃኑ እርሱን ይመስላል፤ የእንስት ከተለቀቀ ደግሞ ህፃኗ እርሷን ትመስላለች።

እውነት ነው፤ አላህም ከወንድ ክሮሞሶም ‘XY’ ወንድን እና ከሴት ክሮሞሶም ‘XX’ ደግሞ ሴትን በምድር ላይ ፈጥሮ የበተነ ነው፤ ይህም የሁለቱ አስተዋእዖ የአባት ክሮሞሶም ግማሽ 23% የእናት ክሮሞሶም 23% ተገናኝተው 46% ሲሆኑ ነው፡-
4:1 እላንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ(ከአዳም) የፈጠራችሁን፣ ከእርስዋም መቀናጆዋን(ሔዋንን) የፈጠረውን፣ #ከእነርሱም ብዙ “ወንዶችን” እና “ሴቶችን” የበተነውን፣ ጌታችሁን ፍሩ።
49፥13 እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ “ከወንድ እና ከሴት ፈጠርናችሁ”።

[ሥነ-ፅንስ]

ክፍል ሶስት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

31:34 አላህ የሰዓቲቱ እውቀት እርሱ ዘንድ ብቻ ነው፤ ዝናምንም ያወርዳል፤ #በማሕፀኖችም #ውስጥ #ያለን #ሁሉ #ያውቃል፤

ደረጃ ሶስት
“ሙድጋ”
“ሙድጋ” مُضْغَة ማለት “ቁራጭ ስጋ”embryonic lump” ወይም “የታኘከ ስጋ”chewed gum” ማለት ሲሆን ልክ ጥርስ እንዳረፈበት ስጋ የሚመስልበት የፅንስ ደረጃ ነው፤ ይህን ደረጃ ለማመልከት “ሱምሙ” ثُمَّ“ከዚያም” የሚል መስተፃምር ከመጠቀም ይልቅ “ፈ” فَ“ም” የሚል ቅፅበታዊ መስተፃምር ይጠቀማል፤ ምክንያቱም 21-24 ቀናት የረጋ ደም ጊዜ ሲሆን

24ኛ ቀን ላይ በቅፅፊት የታኘከ ስጋ ቅርፅ ይጀምራል፤ በዚህ ጊዜ “”ፍጥረትዋ ሙሉ ካልሆነች”” ጅማት፣ አንጀት፣ ስስ ጡንቻ፣ ስስ የደም ስር ወዘተ ስለሚፈጠሩ ነው፡-

:5 እላንተ ሰዎች ሆይ! ከመቀስቀስ፣ በመጠራጠር ዉስጥ እንደ ሆናችሁ አፈጣጠራችሁን ተመልከቱ፤ እኛም ከአፈር ፈጠርናችሁ ከዚያም ከፍቶት ጠብታ፣ ከዚያም ከረጋ ደም፣ ከዚያም ከቁራጭ ስጋ مُضْغَةٍ “”ፍጥረትዋ ሙሉ ከኾነችና ሙሉ ካልሆነች”” ችሎታችንን ለእናንተ ልንገልጽላችሁ ፈጠርናችሁ፤
23:12 በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው፤ ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ “የፍትወት ጠብታ” አደረግነው፤ ከዚያም ጠብታዋን “የረጋ ደም” አድርገን ፈጠርን፤ የረጋውን”ም” ደም “ቁራጭ ሥጋ” مُضْغَةً አድርገን ፈጠርን፤

“ፍጥረትዋ ሙሉ የሆነች” ቁራጭ ሥጋ በአምተኛው ደረጃ ላይ ይመጣል፤ ይህንን ለማመልከት “ከመፍጠር በኋላ ሙሉ መፍጠርን ይፈጥራችኋል” ይላል፡-
39:6 በእናቶቻችሁ ማህፀኖች ውስጥ፣ በሦስት ጨለማዎች ውስጥ፣ “ከመፍጠር በኋላ ሙሉ መፍጠርን ይፈጥራችኋል”፤

ሶስት ጨለማ የተባሉት፡- ሆድ፣ ማህፀንና የእንግዴ ልጅ ናቸው።

ደረጃ አራት
“ዐዝም”
“ዐዝም” عَظْم በነጠላ ሲሆን “ዒዛም” عِظَام ደግሞ በብዜት ነው፤ ትርጉሙም “አፅም”skeleton” ወይም “አጥንት”bone” ማለት ነው፤ ከ 24-35 ቀናት የቁራጭ ስጋ ሂደት ሲሆን ከመቅፅበት 35ኛው ቀን የደም ዝውርውር፣ የነርቭ ሥርዓት፣ አፅም ወዘተ የሚፈጠርበት ሂደት ነው፤ ይህን አጭር ጊዜ ለማመልከት “ፈ” ف“ም” የሚል ቅፅበታዊ መስተፃምር ይጠቀማል፡-
23:12 በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው፤ ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ “የፍትወት ጠብታ” አደረግነው፤ ከዚያም ጠብታዋን “የረጋ ደም” አድርገን ፈጠርን፤ የረጋውንም ደም “ቁራጭ ሥጋ” አድርገን ፈጠርን፤ ቁራጫን”ም” ሥጋ “አጥንቶች” عِظَامًا አድርገን ፈጠርን፤

ደረጃ አምስት
“ለህም”
“ለህም” لَحْم ማለት “ስጋ” ማለት ሲሆን ይህ ስጋ ጠንካራ ጡንቻ ያለው ስጋ ነው፤ ከ 35-38 ቀናት የአጥንት ሂደት ሲሆን ከመቅፅበት በ 38ኛው ቀን ልብ፣ አንጎል፣ ቆዳ፣አይን፣ አፍንጫ ወዘተ የሚፈጠርበት ሂደት ነው፡-
23:12 አጥንቶቹንም “ሥጋን” لَحْمًا አለበስናቸው፤

በዚህ ጊዜ ሩህ ይነፋል፡-
ኢማም ሙስሊም መጽሐፍ 46, ሐዲስ 1:
ዓብደላህ ኢብን መስዑድ እንዲህ አለ። እውነት ተናጋሪ እና እውነት የተነገራቸው የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡-
إِنَّ أَحَدَكُمْ يُجْمَعُ خَلْقُهُ فِي بَطْنِ أُمِّهِ أَرْبَعِينَ يَوْمًا نُطْفَةً، ثُمَّ يَكُونُ عَلَقَةً مِثْلَ ذلِكَ، ثُمَّ يَكُونُ مُضْغَةً مِثْلَ ذلِكَ، ثُمَّ يُرْسَلُ إِلَيْهِ الْمَلَكُ فَيَنْفُخُ فيهِ الرُّوحَ، وَيُؤمَرُ بأَرْبَعِ كَلِمَاتٍ: بِكَتْبِ رِزْقِهِ وَأَجَلِهِ وَعَمَلِهِ وَشَقِيٌّ أَوْ سَعِيدٌ.
እያንዳንዳቹህ በእናቱ ሆድ ውስጥ ፍጥረቱ ይሰበሰባል፤ አርባ ቀን የፍትወት ጠብታ ይሆናል፤ ከዛም በተመሳሳይ የረጋ ደምን ይሆናል፤ ከዛም በተመሳሳይ የታኘከን ስጋ ይሆናል፤ ከዛም መልአክ ይላክና ሩሕ ይነፋበታል፤ መልአኩም አራት ነገሮች ላይ ይታዘዛል፡- ሲሳዩን፣ ፍጻሜውን፣ ስራውን፣ የተከፋ ወይንም ደስተኛ መሆኑን እንዲጽፍ ይታዘዛል።

ደረጃ ስድስት
“ነሸአ”
“ነሸአ” أَنْشَأَ የሚለው ቃል “አንሸአ” أَنْشَأَ “አስገኘ” ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን “ግኝት”production” ማለት ነው፤ አላህም “አንሸናሁ” أَنْشَأْنَاهُ “አስገኘነው” ይለናል፤ ይህም ፅንስ እስከ መወለድ ጊዜ ያለው ሽልን የሚያመለክት ሲሆን “ሌላ ፍጥረትን” ይለዋል፤ በዚህ ጊዜ ከንፈር፣ ጥፍር፣ ፀጉር ወዘተ የሚገኘበት ጊዜ ነው፤ ይህን እረጅም ደረጃ ለማመልከት “ሱምሙ” ثُمَّ “ከዚያም” የሚል መስተፃምር ይጠቀማል፡-

23፥12 ከዚያም “ሌላ ፍጥረትን” خَلْقًا آخَر አድርገን “አስገኘነው” أَنْشَأْنَاه ፤ ከሰዓሊዎችም ሁሉ በላጭ የሆነው አላህ ላቀ፡፡

መደምደሚያ
አላህ ከራሳችን ጥንድ እንድንረካ መፍጠሩ፣ በመካከላችን መተዛዘንና ፍቅር መኖሩ በመርካትም ማህፀን ውስጥ የሚፈሱት የፍትወት ጠብታ ሰው መሆኑ ለሚያስውሉ ሕዝቦች ከአስደናቂ ታምራቶቹ ተጠቃሽ ነው፡-
30:21 ለእናንተም ከራሳችሁ “ጥንዶችን” أَزْوَاجًا “mates” ወደ እነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፤ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ “ታምራቶቹ” آيَاتِه ነው፤ በዚህ ውስጥ ለሚያስውሉ ሕዝቦች “ታምራቶች” አሉ።

ይህንን ታምር አላህ በሥነ-ፅንስ እውቀት በራሳችን ያሉትን የአላህ ታምራት በዘመናችን አሳይቶናል፤ ከዚህ የሚበልጥ ምን መታደል አለ? ምስጋና ሁሉ ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይሁን፡-
41፥53 እርሱም ቁርአን እውነት መሆኑ ለነርሱ እስከሚገለጽላቸው ድረስ፣ በአጽናፎቹ ውስጥ እና #በራሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን #ታምራቶቻችንን በእርግጥ #እናሳያቸዋለን፤ ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ መሆኑ አይበቃቸውምን?

ዋቢ መጽሐፍት ይመልከቱ፡-
1. The Developing Human (Prof. Keith Moor & Prof. T. Persaud) Edition 6 – 1998
2. Clinical Anatomy . By Richard Snell (3ed edition) published in 1986 – Little, Brown
3. A Scientist’s Interpretation of References to Embryology in the Quran (Prof. Keith Moor) Journal of the Islamic Medical Association, 1986: vol.18, Page 15-16

መጓጓዣ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኛ በሆነው፡፡

16፥8 ፈረሶችንም፣ በቅሎዎችንም፣ አህዮችንም “ልትቀመጡዋቸው” እና ልታጌጡባቸው ፈጠረላችሁ ፤ የማታውቁትንም ድንቅ ነገር ይፈጥራል።

የዘመናችን መጓጓዣ“Trans-port” በሶስት ዋና ዋና ክፍል ሲከፈሉ እነርሱም፡- የአየር መጓጓዣ”Air- port”፣ የየብስ መጓጓዣ”Geo-port” እና የባህር መጓጓዣ”Hydro-port” ናቸው፣ የአየር መጓጓዣ በ 1799 AD የንስር ወፍ ንድፍ ታይቶ አይሮፕላን የተሰራ ሲሆን፣ የየብስ መጓጓዣ በ 1768 AD አውቶ ሞቢል መኪና የፈረስ ንድፍ ታይቶ የተሰራና ሲሆን በተመሳሳይ ባቡርም በ 1550 AD የአባጨጓሬ ንድፍ ታይቶ የተሰራ ነው፣ የባህር መጓጓዣ ባለ ሞተር “engine” መርከብ 1805 AD የዶልፊን አሳ ንድፍ ታይቶ የተሰራ ነው። አምላካችን አላህ ይህ ክስተት ከመከሰቱ በፊት ስለዚህ ክስተት እንዲህ ይለናል፡-
16፥8 ፈረሶችንም፣ በቅሎዎችንም፣ አህዮችንም “ልትቀመጡዋቸው” እና ልታጌጡባቸው ፈጠረላችሁ ፤ የማታውቁትንም ድንቅ ነገር ይፈጥራል።

”ልትቀመጡዋቸው” የሚለው ቃል “ሊተረከቡሃ” رَكِب ሲሆን “ረኪበ رَكِب ማለትም “ጋለበ” አሊያም “ተጓዘ” ከሚል ግስ የመጣ ሲሆን *”ልትጓዙባቸው”* የሚል ፍቺ አለው፡-
40:79 አላህ፣ ያ ለናንተ ግመልን ከብትንና ፍየልን፣ ከርሷ ከፊሏን “ልትጋልቡ” لِتَرْكَبُوا የፈጠረላችሁ ነው፤ ከርሷም ትበላላችሁ።
36:41-42 እኛም የቅድም ትውልዳቸውን በተመላች መርከብ ውስጥ የጫን መሆናችን ለነርሱ ምልክት ነው። ከመሰሉም በርሱ “የሚሳፈሩበትን” يَرْكَبُون ለነርሱ ፈጠርንላቸው።

ቁርአን በወረደበት ጊዜ ባህላዊ መጓጓዣ ፈረሶች፣ በቅሎዎች፣ አህዮች ቢሆኑም አላህ የማታውቁትንም ድንቅ ነገር ይፈጥራል ብሎ ቃል በገባው መሰረት ዛሬ በዘመናችን ቁርአን በወረደበት ጊዜ ያልነበሩትንና የማይታወቁትን የአየር መጓጓዣ አይሮፕላን፣ የየብስ መጓጓዣ አውቶ ሞቢል መኪናና ባቡር፣ የባህር መጓጓዣ ባለ ሞተር “engine” መርከብ ፈጥሯል፣ ታዲያ እነዚህን ሞተረኛ መጓጓዣ የሰራው ሰው አይደለምን? የሚል ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ነው፣ አላህ ሰዎችንና ሰዎች የሰሩትን ስራዎች የፈጠረው እርሱ ነው፣ ስራ አራት ንጥረ ነገር አለው እርሱም፡- ጊዜ፣ ቦታ፣ ፈቃድ፣ የሚሰራበት ጥሬ-ነገር”material”፤ አላህ የእነዚህ ነገሮች ሁሉ ፈጣሪ ነው፡-

37:96 «አላህ እናንተንም የምትሠሩትንም የፈጠረ ሲኾን፡፡»

39:62 አላህ *የነገር ሁሉ* ፈጣሪ ነው። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ አስተናባሪ ነው።

40:62 ይሃችሁ፣ ጌታችሁ አላህ ነው፤ *የነገር ሁሉ* ፈጣሪ ነው፤ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም፤

6:102 ይህ ጌታችሁ አላህ ነው፡፡ ከእርሱ በቀር አምላክ የለም፡፡ *ነገር ሁሉ* ፈጣሪ ነው፡፡ ስለዚህ ተገዙት፡፡

ምነው ኑህ ባህላዊ መርከቡን ሰርቶ ኑህ የሰራውን ባህላዊ መርከብ አላህ ፈጠርንላቸው ብሎ የለምን?

11:37 አላህም በጥበቃችንና በትእዛዛችንም ሆነህ መርከቢቱን *ሥራ*፤ በነዚያም በበደሉት ሰዎች ነገር ኢታናግረኝ እነሱ በእርግጥ የሚሰጠሙ ናቸውና አለው።

36:42 ከመሰሉም በርሱ የሚሳፈሩበትን ለነርሱ *ፈጠርንላቸው*።

ቁርአን በወረደበት ጊዜ ሰማይ የአይሮፕላን፣ የኢልኮፍተር፣ የጀት የመሳሰሉት ባለቤት ነው ተብሎ የማይታሰብ ቢሆንም አላህ ሰማይ የመንገዶች ባለቤት እንደሆነች አስቀድሞ ከ 1200 አመት በፊት ነግሮናል፡-

51.7 የመንገዶች ባለቤት በሆነችው ሰማይ እምላለሁ።

ሰውም በአይሮፕላን ላይ ሆኖ ከደመና በላይ ሲበር የደመናው ግግር ልክ እንደ ተራራ ጋራ የተነባበረ ነው፣ ይህ ቁርአን በወረደበት ጊዜ ማንም ያላየው ጉዳይ ቢሆንም አላህ ወደፊት በአጽናፎቹ ውስጥ ያሉትን ታምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን ብሎ ቃል በገባው መሰረት ዛሬ በዘመናችን አይተነዋል፣ ከደመና በላይ ያለውን እንደ ተራራ ጋራ የተነባበረውን በረዶ ከ 1200 አመት በፊት አላህ ነግሮናል፡-

24.43 ከሰማይም ደመና በውስጧ ካሉት ጋራዎች በረዶን ያወርዳል፤

ታዲያ ይህን የሩቅ ነገር ወሬ ነቢያችን ከየት አመጡት? መልሱ የሰማያትንንና የምድርን ሩቅ ምስጢር አዋቂ ከሆነው ከአላህ ዘንድ ነው፡-

16:77 በሰማያትና በምድርም ያለው ሩቅ ምስጢር የአላህ ነው፤

35:38 አላህ የሰማያትንና የምድርን ምስጢር በእርግጥ ዐዋቂ ነው፤

72:26-27 እርሱ ሩቁን ሚስጢር ዐዋቂ ነው፣ በሚስጢሩ ላይ አንድንም አያሳውቅም። ከመልክተኛ ለወደደው ቢሆን እንጅ ለሌላ አይገልጽም፤

34:48 ፡-ጌታዬ እውነትን ያወርዳል፤ ሩቅ የኾኑትን ሚስጢሮች ሁሉ ዐዋቂ ነው በላቸው።

25:6 ያ በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለን ምስጢር የሚያውቀው፣ አወረደው፤ እርሱ መሐሪ አዛኝ ነውና፤ በላቸው።

ጥበብ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

2፥269 *ለሚሻው ሰው ጥበብን ይሰጣል፤ ጥበብንም የሚሰጠው ሰው ብዙን መልካም ነገር በእርግጥ ተሰጠ*፡፡ የአእምሮዎች ባለቤቶች እንጂ ሌላው አይገሰጽም፡፡ يُؤْتِى ٱلْحِكْمَةَ مَن يَشَآءُ ۚ وَمَن يُؤْتَ ٱلْحِكْمَةَ فَقَدْ أُوتِىَ خَيْرًا كَثِيرًا ۗ وَمَا يَذَّكَّرُ إِلَّآ أُو۟لُوا۟ ٱلْأَلْبَٰبِ

“ሐኪም” حَكِيم ማለት “ጥበበኛ” ማለት ሲሆን “ሓኪም” حُكِمِين ማለት ደግሞ “ፈራጅ” ማለት ነው፤ ሁለቱም “ሐከመ” حَكَمَ ማለትም “ፈረደ” “ተጠበበ” ከሚል ግስ የመጡ ናቸው፤ “ሒክማህ” حِكْمَة ማለት “ጥበብ” ማለት ሲሆን “ሑክም” حُكْم ደግሞ “ፍርድ” ማለት ነው፤ ጥበብ እና ፍርድ የጥበበኛው እና የፈራጁ አላህ ባህርያት ናቸው፤ አላህ እጅግ በጣም ጥበበኛ ነው፡-
28፥9 «ሙሳ ሆይ! እነሆ እኔ አሸናፊው *ጥበበኛው* አላህ ነኝ፡፡ يَٰمُوسَىٰٓ إِنَّهُۥٓ أَنَا ٱللَّهُ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ
3፥6 እርሱ ያ በማሕጸኖች ውስጥ እንደሚሻ አድርጎ የሚቀርጻችሁ ነው፡፡ ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ አሸናፊው *ጥበበኛው* ነው፡፡ هُوَ ٱلَّذِي يُصَوِّرُكُمۡ فِي ٱلۡأَرۡحَامِ كَيۡفَ يَشَآءُۚ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ

አላህ ለሚሻው ሰው ጥበብን ይሰጣል፤ ጥበብን ከአላህ የተሰጠው ሰው ብዙን መልካም ነገር በእርግጥ ተሰጦታል፡-
2፥269 *ለሚሻው ሰው ጥበብን ይሰጣል፤ ጥበብንም የሚሰጠው ሰው ብዙን መልካም ነገር በእርግጥ ተሰጠ*፡፡ የአእምሮዎች ባለቤቶች እንጂ ሌላው አይገሰጽም፡፡ يُؤۡتِي ٱلۡحِكۡمَةَ مَن يَشَآءُۚ وَمَن يُؤۡتَ ٱلۡحِكۡمَةَ فَقَدۡ أُوتِيَ خَيۡرٗا كَثِيرٗاۗ وَمَا يَذَّكَّرُ إِلَّآ أُوْلُواْ ٱلۡأَلۡبَٰبِ

አላህ ጥበብን ለሰው ልጆች በዐቅል እና በነቅል ይሰጣል፤ እነዚህ ሁለት የጥበብ ጭብጦችን ነጥብ በነጥብ እንይ፡-

ነጥብ አንድ
“ዐቅል”
“ዐቅል” عقل ማለት “ግንዛቤ”Metacognition” ማለት ሲሆን አላህ በቁርአን “ለዐለኩም ተዕቂሉን” لَّعَلَّكُمۡ تَعۡقِلُون ይለናል፡-
12:2 በእርግጥ እኛ *ትገነዘቡ ዘንድ* ዐረብኛ ቁርአን ሲሆን አወረድነው። إِنَّآ أَنزَلۡنَٰهُ قُرۡءَٰنًا عَرَبِيّٗا لَّعَلَّكُمۡ تَعۡقِلُونَ
2:242 እንደዚሁ አላህ አንቀጾቹን *ትገነዘቡ ዘንድ* ለእናንተ ያብራራላችኋል፡፡ كَذَٰلِكَ يُبَيِّنُ ٱللَّهُ لَكُمۡ ءَايَٰتِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَعۡقِلُون

“ትገነዘቡ ዘንድ” የሚለው ቃላት በአጽንዖትና በእንክሮት ልናጤነው የሚገባ ሃይለ ቃል ነው፤ የሰው ልጅ “አዕምሮ” እራሱ “ዐቅል” ይባላል፤ ዐቅል የጥበብ ተውህቦ”faculty” ነው፤ የሰው ልጅ በተፈጥሮ ጥበብን ይወዳል፤ “ፊሎሶፍይ” φιλοσοφία የሁለት ቃላት ውቅር ነው፤ “ፊሎስ” φίλος “ፍቅር” እና “ሶፎስ” σοφός “ጥበብ” ሲሆን “የጥበብ ፍቅር” ማለት ነው፤ ይህም ሥነ-ጥበብ በውስጡ፡-
ሥነ-አመክንዮ”logic”፣
ሥነ-ኑባሬ”Ontology”፣
ሥነ-እውነት”metaphysics”፣
ሥነ-ዕውቀት”epistemology”፣
ሥነ-መለኮት”theology”፣
ሥነ-ምግባር”ethics”፣
ሥነ-ውበት”esthetics”፣
ሥነ-መንግሥት”politics”፣
ሥነ-ቋንቋ”Linguistics”
የመሳሰሉት እሳቦት ይዟል። ጥበብ”craft” እራሱ፡- ሥነ-ጥበብ፣ እደ-ጥበብ፣ ኪነ-ጥበብ እና አውደ-ጥበብ ለአሉታዊ ነገር ከተጠቀሙበት ምግባረ-እኩይ”witch-craft” ሲሆን በአውንታዊ ከተጠቀምንበት ምግባረ-ስናይ”art-craft” መማሪያም ነው፤ አላህ፡- “አፈላ ተዕቂሉን” أَفَلَا تَعۡقِلُون ይለናል፡-
21:10 *ክብራችሁ በውሥጡ ያለበትን መጽሐፍ ወደ እናንተ በእርግጥ አወረድንን፤ አትገነዘቡምን*? لَقَدۡ أَنزَلۡنَآ إِلَيۡكُمۡ كِتَٰبٗا فِيهِ ذِكۡرُكُمۡۖ أَفَلَا تَعۡقِلُون

“አትገነዘቡምን?” የሚለው ቃላት በአጽንዖትና በእንክሮት ልናጤነው የሚገባ ሃይለ ቃል ነው፤ ቁርአን ክብራችን በውሥጡ ያለበትን መጽሐፍ ነው፤ አዎ የሰው ልጆች ሊኩበሩበት የሚችሉበት ጥበብ ይዟል።

ነጥብ ሁለት
“ነቅል”
“ነቅል” نقل ማለት “አስተርዮ”epiphany” ማለት ሲሆን “ወሕይ” وَحْى ነው፤ አምላካችን አላህ ወደ ነብያችን””ﷺ”” ጥበብን አውርዷል፡-
4፥113 አላህም በአንተ ላይ መጽሐፍንና *ጥበብን* አወረደ:: *የማታውቀውንም ሁሉ አስተማረህ*:: የአላህም ችሮታ በአንተ ላይ ታላቅ ነው:: وَأَنزَلَ ٱللَّهُ عَلَيْكَ ٱلْكِتَٰبَ وَٱلْحِكْمَةَ وَعَلَّمَكَ مَا لَمْ تَكُن تَعْلَمُ ۚ وَكَانَ فَضْلُ ٱللَّهِ عَلَيْكَ عَظِيمًا

ይህም ጥበብ ክብራችን በውሥጡ ያለበትን መጽሐፍ ቁርአን ነው፤ ቁርአን ጥበብ የተሞላ መጽሐፍ ነው፡-
10፥1 “አሊፍ ላም ራ” ይህቺ *ጥበብ* ከተመላው መጽሐፍ ከቁርአን አንቀጾች ናት:: الٓر ۚ تِلْكَ ءَايَٰتُ ٱلْكِتَٰبِ ٱلْحَكِيمِ
30፥2 ይህች *ጥበብ* ከተመላው መጽሐፍ አንቀጾች ናት:: تِلْكَ ءَايَٰتُ ٱلْكِتَٰبِ ٱلْحَكِيمِ
36፥2 *ጥበብ* በተመላበት ቁርአን እምላለሁ:: وَٱلْقُرْءَانِ ٱلْحَكِيمِ

ስለዚህ ክብራችን በውስጡ ያለበትን ይህንን ጥበብ የተሞላ መጽሐፍ መገንዘብ ግድ ይላል ማለት ነው፤ የእሳት ሰዎች “የምናገናዝብ” በነበርን ኖሮ በነዳጅ እሳት ጓዶች ውስጥ ባልሆን ነበር ብለው ይፀፀታሉ፡-
67:10 የምንሰማ ወይንም *”የምናገናዝብ”* በነበርን ኖሮ በነዳጅ እሳት ጓዶች ውስጥ ባልሆን ነበር ይላሉ። وَقَالُوا۟ لَوْ كُنَّا نَسْمَعُ أَوْ نَعْقِلُ مَا كُنَّا فِىٓ أَصْحَٰبِ ٱلسَّعِيرِ

<u>ሥነ-ፅንስ</u>

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው::

31:34 አላህ የሰዓቲቱ እውቀት እርሱ ዘንድ ብቻ ነው፤ ዝናምንም ያወርዳል፤ #በማሕፀኖችም #ውስጥ #ያለን #ሁሉ #ያውቃል፤

መግቢያ
ሥነ-ፅንስ ጥናት ኢምብሪዮሎጂይ”Embryology” ሲባል “ኢምብሮ” ἔμβρυον “ያልተወለደ” እና “ሎጂአ” λογία, “ጥናት” ከሚል ሁለት የግሪክ ቃል የተዋቀረ ነው፤ ይህንን ፅንስ እናቱ ማህፀን ውስጥ በሚፈልገው መልኩ የሚቀርፀው አንዱ አምላክ አላህ ነው፡-
3:6 እርሱ ያ “በማሕፀኖች” ዉስጥ እንደሚሻ አድርጎ “የሚቀርጻችሁ” ነዉ፤ ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤

ይህ ፅንስ ማህፀን ውስጥ እንዴት እንደሚፈጠር ሙሉ እውቀት ያለው የዓለማቱ ጌታ አላህ ብቻ ነው፡-
31:34 አላህ የሰዓቲቱ ዕውቀት እርሱ ዘንድ ብቻ ነው፤ ዝናምንም ያወርዳል፤ “በማሕፀኖችም ውስጥ ያለን ሁሉ ያውቃል”፤
53:32 ከምድር በፈጠራችሁ ጊዜ እናንተም በእናቶቻችሁ “ማሕፀኖች” ውስጥ ሽሎች በሆናችሁ ጊዜ እርሱ በእናንተ ሁኔታ “አዋቂ” ነው።
13:8 አላህ ሴት ሁሉ የምታረግዘውን ያውቃል፤ “ማሕፀኖችም የሚያጐድሉትን የሚጨምሩትንም፥ ያውቃል”፤ ነገሩም ሁሉ እርሱ ዘንድ በልክ የተወሰነ ነው።

በማሕፀኖችም ውስጥ ያለውን ሁሉ የሚያውቀ አምላክ የሥነ-ፅንስ እውቀት ወደፊት እንደሚያሳየና እንደሚያሳውቀን ለማመልከት፡- “በራሶቻችሁ ውስጥ ያሉትም ታምራት ወደፊት ያሳያችኋል፤ ታውቁታላችሁ” በማለት ቃል ገብቷል፡-
41፥53 እርሱም ቁርአን እውነት መሆኑ ለነርሱ እስከሚገለጽላቸው ድረስ፣ በአጽናፎቹ ውስጥ እና #በራሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን #ታምራቶቻችንን በእርግጥ #እናሳያቸዋለን፤ ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ መሆኑ አይበቃቸውምን?
27:93 ምስጋና ለአላህ ነው፤ #ታምራቶቹን #ወደፊት #ያሳያችኋል፤ #ታውቁታላችሁ በላቸው።

አላህ ይህንን እውቀት በራሳችን አካላት ከማሳየቱ በፊት በቁርአን አንድ ሽል በማህፀን ውስጥ እንዴት የተለያየ ደረጃዎችን”stages” እንደሚያሳልፍ በተከበረ ቃሉ ይነግረናል፡-

23:12 በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው፤ ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ “የፍትወት ጠብታ” ٱلنُّطْفَةَ አደረግነው፤ ከዚያም ጠብታዋን “የረጋ ደም” ٱلْعَلَقَةَ አድርገን ፈጠርን፤ የረጋውንም ደም “ቁራጭ ሥጋ” ٱلْمُضْغَةَ አድርገን ፈጠርን፤ ቁራጪንም ሥጋ “አጥንቶች” عِظَامًا አድርገን ፈጠርን፤ አጥንቶቹንም ሥጋን لَحْمًا አለበስናቸው፤ ከዚያም “ሌላ ፍጥረትን” خَلْقًا آخَرَ አድርገን “አስገኘነው” أَنْشَأْنَاهُ፤ ከሰዓሊዎችም ሁሉ በላጭ የሆነው አላህ ላቀ።

ደረጃ አንድ
“ኑጥፋህ”
የአንድ ሽል በማህፀን ያለው የመጀመሪያ ደረጃ “ኑጥፋህ” ٱلنُّطْفَةَ ነው፤ “ኑጥፋህ” ማለት “የፍትወት ጠብታ” ሲሆን ይህም የተባእት ዘር ህዋስ” sperm cell” እና የእንሥት እንቁላል ህዋስ”egg cells” ነው፤ እነዚህ የፍትወት ጠብጣዎች በሥነ-ፅንስ ምሁራን “ፍናፍንት”hermaphroditic” በመባል ይታወቃሉ፤ አላህ ስለዚህ የፍትወት ጠብታ በተከበረ ቃሉ እንዲህ ይለናል፡-

53:45-46 እርሱም ሁለቱን ዓይነቶች ወንድና ሴትን ፈጠረ። “ከፍትወት ጠብታ” ٱلنُّطْفَةِ በማኅፀን ውስጥ በምትፈስ ጊዜ፤
80:19 “ከፍትወት ጠብታ” ٱلنُّطْفَةِ ፈጠረው መጠነውም።
16:4 ሰውን “ከፍትወት ጠብታ” ٱلنُّطْفَةِ ፈጠረው፤ ከዚያም እርሱ ወዲያውኑ ትንሣኤን በመካድ ግልጽ ተከራካሪ ይሆናል።
35:11 አላህም ከአፈር፣ ከዚያም “ከፍትወት ጠብታ” ٱلنُّطْفَةِ ፈጠራችሁ፤
36:77 ሰውየው እኛ “ከፍቶት ጠብታ” የፈጠርነው መሆናችን አላወቀምን?
40:67 እርሱ ያ ከአፈር፣ ከዚያም “ከፍትወት ጠብታ” ٱلنُّطْفَةِ፣ ከዚያም ከረጋ ደም፣ የፈጠራችሁ ነው።

የሴት ልጅ ማህፀን ዘር በሚዘራበት “እርሻ” ሲመሰል፤ የእንሥት ማህፀን ላይ ላይ የሚገናኘው የተባእት ዘር ህዋስ ደግሞ ገበሬ እርሻ ላይ በሚዘራው “ዘር” ተመስሏል፤ ምክንያቱም አንድ ገበሬ እርሻው ላይ ከዘራ በኃላ ዘሩ ዳብሮ ለፍሬ የሚበቃው በእርሻ ውስጥ እንደሆነ ሁሉ አንድ ተባእትም አንድ እንስት ማህፀን ውስጥ ዘሩን ተገናኝ ሆኖ ከዘራ በኃላ ሂደቱ ሁሉ ተከናውኖ ለፍሬ የሚበቃው ማህፀን ውስጥ ነው፡-
2:223 ሴቶቻችሁ ለእናንተ “እርሻ” ናቸውና፤ እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ኹኔታ ድረሱ፤ ለነፍሶቻችሁም መልካም ሥራን አስቀድሙ፤ አላህንም ፍሩ፤ እናንተም “”ተገናኝዎቹ”” መኾናችሁን ዕወቁ።
56:57-59 እኛ ፈጠርናችሁ፤ አታምኑምን? “በማኅፀኖች “የምታፈሱትን አያችሁትን”? እናንተ ትፈጥሩታላችሁን? ወይስ እኛ ፈጣሪዎቹ ነን።
56:63-64 “የምትዘሩትንም አያችሁን”? እናንተ ታበቅሉታላችሁን? ወይስ እኛ አብቃዮቹ ነን?
32:7-8 ያ የፈጠረውን ነገር ሁሉ ያሳመረው፣ የሰውንም ፍጥረት ከጭቃ የጀመረው፥ ነው፤ ከዚያም “ዘሮቹን”፣ ከተጣለለ “ከደካማ ውሃ” ያደረገ፣ ነው።
77:20-21 “ከደካማ ውሃ” አልፈጠርናችሁምን? “በተጠበቀ መርጊያ በማሕፀን ውስጥም” አደረግነው፤

አላህ በማህፀን ያለውን የመጀመሪያ ደረጃ ሰው እንዴት የተባእት ዘር ህዋስ እና የእንሥት እንቁላል ህዋስ ፍናፍንት ሆኖ ተቀላቅሎ እንደሚፈጠር ቀድሞውኑ በማሕፀኖችም ውስጥ ያለንውን ሁሉ አዋቂ አምላክ መሆኑን ለእኛ ለማሳየት “አምሻጅ” ٱمْشَاجٍ “ቅልቅል”mixture” በማለት ይናገራል፤ ይህ የሚቀላቀለው የተባእት ዘር ህዋስ እና የእንሥት እንቁላል ህዋስ ከወንድ እና ከሴት ስለሚገኝ አላህ፡- ከወንድ እና ከሴት ፈጠርናችሁ” ይላል፡-
76:2 እኛ ሰዉን በሕግ ግዳጅ የምንሞክረዉ ስንሆን፥ “ቅልቅሎች” ٱمْشَاجٍ ከሆኑ “የፍትወት ጠብታ” ٱلنُّطْفَةَ ፈጠርነዉ፤ ሰሚ ተመልካችም አደረግነዉ።
49፥13 እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ “ከወንድ እና ከሴት ፈጠርናችሁ”።

“ደረጃ ሁለት”
“ዐለቃ”
“ዐለቃ” ʿalaqa አንስታይ ሲሆን “ዐለቅ” ʿalaq ደግሞ ተባእታይ ነው፤ ትርጉሙም “አልቅት”leech” ወይም “የረጋ ደም”blood-clot” ማለት ነው፤ ይህን የፅንስ ሁለተኛው ደረጃ ከሚታይ አልቅት ከሚባል የባህር ትል”insect” እና ከረጋ ደም ጋር ስለሚመሳሰል ነው፤ ወደዚህ ሂደት ለመምጣት በህዋሳት ውህደት ወቅት “ክሮሞሶም”Chromosomes” ከአንዱ ለጋሽ ወላጅ ወደሌላው ለጋሽ ወላጅ ይተላለፋል፤ እያንዳንዱ ተሣታፊ ህዋስ የለጋሾችን ግማሽ ክሮሞሶም ይይዛል፤ የአባት ክሮሞሶም ግማሽ 23% የእናት ክሮሞሶም 23% ተገናኝተው 46% ይዋሃዳሉ ማለት ነው፤ ተወራሽ የዘር ምልክቶች በምፃረ-ቃል “ዲ-ኤን-ኤ”(DNA) ወይም በዝርዝር “ዲኦክሲሪቦ ኒውክሊክ አሲድ”(deoxyribonucleic acid) በመባል በሚታወቀው በክሮሞሶሞች ውስጥ የሚገኝ ንጥረ-ነገር ውስጥ ሰፍረው ይገኛሉ። ክሮሞሶሞች “በጥንድ” ሆነው በሚገኙበት ጊዜ “ዳይፕሎይድ”(diploid) ይባላሉ፤ ክሮሞሶሞች በነጠላ ግዜ “ሃፕሎይድ”(haploid) ይባላሉ፤ በዚህ ሂደት አንድ ሴል የነበረው የወንድ የዘር ህዋስ ከሴት የእንቁላል ህዋስ ጋር ከተዋሐደ በኃላ 2, 4, 8, 16, 32, 64 እያለ በቲሪልየን ብዜት በ 21 ቀን የረጋ ደም”blood-clot” የሚለው ደረጃ ይጀምራል፤ ይህንን ደረጃ አምላካችን አላህ እንዲህ ይለናል፡-
22:5 እላንተ ሰዎች ሆይ! ከመቀስቀስ፣ በመጠራጠር ዉስጥ እንደ ሆናችሁ አፈጣጠራችሁን ተመልከቱ፤ እኛም ከአፈር ፈጠርናችሁ ከዚያም ከፍቶት ጠብታ፣ ከዚያም “ከረጋ ደም” ʿalaqa፣ ከዚያም ከቁራጭ፣ ስጋ ፍጥረትዋ ሙሉ ከኾነችና ሙሉ ካልሆነች ችሎታችንን ለእናንተ ልንገልጽላችሁ ፈጠርናችሁ፤
40:67 እርሱ ያ ከአፈር፣ ከዚያም ከፍትወት ጠብታ፣ ከዚያም “ከረጋ ደም” ʿalaqa፤ የፈጠራችሁ ነው።
96:1-2 አንብብ በዚያ ሁሉን በፈጠረው ጌታህ ስም፤ ሰውን “ከረጋ ደም” ʿalaq በፈጠረው ጌታህ ስም።

ከፍትወት ህዋስ ወደ የረጋ ደም የሚሄድበት ሂደት እና ደረጃ ለማመልከት “ሱምመ” ṯumma“ከዚያም” የሚል መስተፃምር ይጠቀማል፤ ከዚህ ከተቀላቀለው የፍትወት ህዋስ ሁለት ዓይነቶችን ወንድና ሴትን ይመጣል፡-
75፥36-39 ሰው ስድ ሆኖ መትተውን ይጠረጥራልን? የሚፈስስ ከሆነ የፍትወት ጠብታ አልነበረምን? “ከዚያም” ṯumma“የረጋ ደም” ʿalaqa ሆነ፤ ሰው አድርጎ ፈጠረውም፤ አስተካከለውም። “ከእርሱም” ሁለት ዓይነቶችን “ወንድና ሴትን” አደረገ።

“የዘረ-መል ጥናት”(Genetic) እንደሚያስተነትነው የተባእት ክሮሞሶም ‘XY’ ሲሆን የእንስት ክሮሞሶም ደግሞ ‘XX’ ነው፤ ከወንድ ‘Y” መጥቶ ከሴት ‘X’ ከመጣ ሽሉ የአባቱን ፆታ በመያዝ ወንድ ይሆናል፤ ከወንድ ‘X” መጥቶ ከሴት ‘X’ ከመጣ ሽሉ የእናቱን ፆታ በመያዝ ሴት ይሆናል፤ ክሮሞሶም ማለት በአማርኛችን “ሐብለ-በራሔ” ይልላል፤ ልብ አድርግ የወንድ ክሮሞሶም ‘XY’ ሲሆን የሴት ክሮሞሶም ደግሞ ‘XX’ መሆኑ ማለቴ ነው፤ የዘረ-መል ጥናት ይህንን ከማወቁ በፊት አላህ ለመልእክተኛው ይህንን የሩቅ ነገር ሚስጥር አሳውቋል፡-
ኢማም ቡኻርይ መጽሐፍ 60 , ቁጥር 4 :
وَأَمَّا الشَّبَهُ فِي الْوَلَدِ فَإِنَّ الرَّجُلَ إِذَا غَشِيَ الْمَرْأَةَ فَسَبَقَهَا مَاؤُهُ كَانَ الشَّبَهُ لَهُ، وَإِذَا سَبَقَ مَاؤُهَا كَانَ الشَّبَهُ لَهَا ".
የአላህ መልክተኛ አሉ፡- የልጆች ከወላጆቻቸው መመሳሰል እንዲህ ነው፤ ተባእት ከሚስቱ ጋር ተራክቦ ሲያደርግ የእርሱ ከተለቀቀ ህፃኑ እርሱን ይመስላል፤ የእንስት ከተለቀቀ ደግሞ ህፃኗ እርሷን ትመስላለች።

እውነት ነው፤ አላህም ከወንድ ክሮሞሶም ‘XY’ ወንድን እና ከሴት ክሮሞሶም ‘XX’ ደግሞ ሴትን በምድር ላይ ፈጥሮ የበተነ ነው፤ ይህም የሁለቱ አስተዋእፆ የአባት ክሮሞሶም ግማሽ 23% የእናት ክሮሞሶም 23% ተገናኝተው 46% ሲሆኑ ነው፡-
4:1 እላንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ(ከአዳም) የፈጠራችሁን፣ ከእርስዋም መቀናጆዋን(ሔዋንን) የፈጠረውን፣ #ከእነርሱም ብዙ “ወንዶችን” እና “ሴቶችን” የበተነውን፣ ጌታችሁን ፍሩ።
49፥13 እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ “ከወንድ እና ከሴት ፈጠርናችሁ”።

ደረጃ ሶስት
“ሙድጋ”
“ሙድጋ” مُضْغَة ማለት “ቁራጭ ስጋ”embryonic lump” ወይም “የታኘከ ስጋ”chewed gum” ማለት ሲሆን ልክ ጥርስ እንዳረፈበት ስጋ የሚመስልበት የፅንስ ደረጃ ነው፤ ይህን ደረጃ ለማመልከት “ሱምሙ” ثُّم“ከዚያም” የሚል መስተፃምር ከመጠቀም ይልቅ “ፈ” ف“ም” የሚል ቅፅበታዊ መስተፃምር ይጠቀማል፤ ምክንያቱም 21-24 ቀናት የረጋ ደም ጊዜ ሲሆን 24ኛ ቀን ላይ በቅፅፈት የታኘከ ስጋ ቅርፅ ይጀምራል፤ በዚህ ጊዜ “”ፍጥረትዋ ሙሉ ካልሆነች”” ጅማት፣ አንጀት፣ ስስ ጡንቻ፣ ስስ የደም ስር ወዘተ ስለሚፈጠሩ ነው፡-
22:5 እላንተ ሰዎች ሆይ! ከመቀስቀስ፣ በመጠራጠር ዉስጥ እንደ ሆናችሁ አፈጣጠራችሁን ተመልከቱ፤ እኛም ከአፈር ፈጠርናችሁ ከዚያም ከፍቶት ጠብታ፣ ከዚያም ከረጋ ደም፣ ከዚያም ከቁራጭ ስጋ مُضْغَةٍ“”ፍጥረትዋ ሙሉ ከኾነችና ሙሉ ካልሆነች”” ችሎታችንን ለእናንተ ልንገልጽላችሁ ፈጠርናችሁ፤
23:12 በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው፤ ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ “የፍትወት ጠብታ” አደረግነው፤ ከዚያም ጠብታዋን “የረጋ ደም” አድርገን ፈጠርን፤ የረጋውን”ም” ደም “ቁራጭ ሥጋ” مُضْغَةً አድርገን ፈጠርን፤

“ፍጥረትዋ ሙሉ የሆነች” ቁራጭ ሥጋ በአምተኛው ደረጃ ላይ ይመጣል፤ ይህንን ለማመልከት “ከመፍጠር በኋላ ሙሉ መፍጠርን ይፈጥራችኋል” ይላል፡-
39:6 በእናቶቻችሁ ማህፀኖች ውስጥ፣ በሦስት ጨለማዎች ውስጥ፣ “ከመፍጠር በኋላ ሙሉ መፍጠርን ይፈጥራችኋል”፤

ሶስት ጨለማ የተባሉት፡- ሆድ፣ ማህፀንና የእንግዴ ልጅ ናቸው።

ደረጃ አራት
“ዐዝም”
“ዐዝም” عَظْم በነጠላ ሲሆን “ዒዛም” عِظَام ደግሞ በብዜት ነው፤ ትርጉሙም “አፅም”skeleton” ወይም “አጥንት”bone” ማለት ነው፤ ከ 24-35 ቀናት የቁራጭ ስጋ ሂደት ሲሆን ከመቅፅበት 35ኛው ቀን የደም ዝውርውር፣ የነርቭ ሥርዓት፣ አፅም ወዘተ የሚፈጠርበት ሂደት ነው፤ ይህን አጭር ጊዜ ለማመልከት “ፈ” ف“ም” የሚል ቅፅበታዊ መስተፃምር ይጠቀማል፡-
23:12 በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው፤ ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ “የፍትወት ጠብታ” አደረግነው፤ ከዚያም ጠብታዋን “የረጋ ደም” አድርገን ፈጠርን፤ የረጋውንም ደም “ቁራጭ ሥጋ” አድርገን ፈጠርን፤ ቁራጯን”ም” ሥጋ “አጥንቶች” عِظَامًا አድርገን ፈጠርን፤

ደረጃ አምስት
“ለህም”
“ለህም” لَحْم ማለት “ስጋ” ማለት ሲሆን ይህ ስጋ ጠንካራ ጡንቻ ያለው ስጋ ነው፤ ከ 35-38 ቀናት የአጥንት ሂደት ሲሆን ከመቅፅበት በ 38ኛው ቀን ልብ፣ አንጎል፣ ቆዳ፣አይን፣ አፍንጫ ወዘተ የሚፈጠርበት ሂደት ነው፡-
23:12 አጥንቶቹንም “ሥጋን” لَحْمًا አለበስናቸውም፤

በዚህ ጊዜ ሩህ ይነፋል፡-
ኢማም ሙስሊም መጽሐፍ 46, ሐዲስ 1:
ዓብደላህ ኢብን መስዑድ እንዲህ አለ። እውነት ተናጋሪ እና እውነት የተነገራቸው የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡-
إِنَّ أَحَدَكُمْ يُجْمَعُ خَلْقُهُ فِي بَطْنِ أُمِّهِ أَرْبَعِينَ يَوْمًا نُطْفَةً، ثُمَّ يَكُونُ عَلَقَةً مِثْلَ ذلِكَ، ثُمَّ يَكُونُ مُضْغَةً مِثْلَ ذلِكَ، ثمَّ يُرْسَلُ إِلَيْهِ الْمَلَكُ فَيَنْفُخُ فيهِ الرُّوحَ، وَيُؤمَرُ بأَرْبَعِ كَلِمَاتٍ: بِكَتْبِ رِزْقِهِ وَأَجَلِهِ وَعَمَلِهِ وَشَقِيٌّ أَوْ سَعِيدٌ.
እያንዳንዳቹህ በእናቱ ሆድ ውስጥ ፍጥረቱ ይሰበሰባል፤ አርባ ቀን የፍትወት ጠብታ ይሆናል፤ ከዛም በተመሳሳይ የረጋ ደምን ይሆናል፤ ከዛም በተመሳሳይ የታኘከን ስጋ ይሆናል፤ ከዛም መልአክ ይላክና ሩሕ ይነፋበታል፤ መልአኩም አራት ነገሮች ላይ ይታዘዛል፡- ሲሳዩን፣ ፍጻሜውን፣ ስራውን፣ የተከፋ ወይንም ደስተኛ መሆኑን እንዲጽፍ ይታዘዛል።

ደረጃ ስድስት
“ነሽአ”
“ነሽአ” ٱنشَأَ የሚለው ቃል “አንሸአ” ٱنشَأَ “አስገኘ” ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን “ግኝት”production” ማለት ነው፤ አላህም “አንሸናሁ” ٱنشَأْنَاهُ “አስገኘነው” ይለናል፤ ይህም ፅንስ እስከ መወለድ ጊዜ ያለው ሽልን የሚያመለክት ሲሆን “ሌላ ፍጥረትን” ይለዋል፤ በዚህ ጊዜ ከንፈር፣ ጥፍር፣ ፀጉር ወዘተ የሚገኘበት ጊዜ ነው፤ ይህን እረጅም ደረጃ ለማመልከት “ሱምመ” ثُمَّ “ከዚያም” የሚል መስተፃምር ይጠቀማል፡-
23፥12 ከዚያም “ሌላ ፍጥረትን” خَلْقًا آخَرَ አድርገን “አስገኘነው” ٱنشَأْنَاهُ፤ ከሰዓሊዎችም ሁሉ በላጭ የሆነው አላህ ላቀ፡፡

መደምደሚያ
አላህ ከራሳችን ጥንድ እንድንረካ መፍጠሩ፣ በመካከላችን መተዛዘንና ፍቅር መኖሩ በመርካትም ማህፀን ውስጥ የሚፈሱት የፍትወት ጠብታ ሰው መሆኑ ለሚያስውሉ ሕዝቦች ከአስደናቂ ታምራቶቹ ተጠቃሽ ነው፡-
30:21 ለእናንተም ከራሳችሁ “ጥንዶችን” أَزْوَاجًا “mates” ወደ እነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፤ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ “ታምራቶቹ” ءَايَاتِهِۦ ነው፤ በዚህ ውስጥ ለሚያስውሉ ሕዝቦች “ታምራቶች” አሉ።

ይህንን ታምር አላህ በሥነ-ፅንስ እውቀት በራሳችን ያሉትን የአላህ ታምራት በዘመናችን አሳይቶናል፤ ከዚህ የሚበልጥ ምን መታደል አለ? ምስጋና ሁሉ ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይሁን፡-
41፥53 እርሱም ቁርአን እውነት መሆኑ ለነርሱ እስከሚገለጽላቸው ድረስ፣ በአጽናፎቹ ውስጥ እና #በራሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን #ታምራቶቻችንን በእርግጥ #እናሳያቸዋለን፤ ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ መሆኑ አይበቃቸውምን?

ዋቢ መጽሐፍት ይመልከቱ፡-
1. The Developing Human (Prof. Keith Moor & Prof. T. Persaud) Edition 6 – 1998
2. Clinical Anatomy . By Richard Snell (3ed edition) published in 1986 – Little, Brown
3. A Scientist’s Interpretation of References to Embryology in the Quran (Prof. Keith Moor) Journal of the Islamic Medical Association, 1986: vol.18, Page 15-16

ቋንቋ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

55፥3-4 ሰውን ፈጠረ፡፡ *መናገርን አስተማረው*፡፡ خَلَقَ ٱلْإِنسَٰنَ عَلَّمَهُ ٱلْبَيَانَ

*መወለድ፣”መሞት፣መብላት፣ መጠጣት፣ ያ የተበላውንና የተጠጣውን ነገር በሌላ መልኩ ከሰውነት ማስወገድ፣ መተኛት፣ ከተቃራኒ ጥንድ ጋር ተራክቦ ማድረግ ሰው ከእንስሳ የሚጋራበት ተፈጥሮ ነው፤ ነገር ግን ሰው ከእንስሳ፣ ከእጽዋት፣ ከማዕድናት በተፈጥሮ ይልቃል፤ አላህ ሰውን ከሌላው ፍጡር አክብሮታል፤ ከፈጠረውም ፍጡሮች በብዙዎቹ ላይ ማብለጥን አብልጦታል፡-
17፥70 *የአደምንም ልጆች በእርግጥ ከሌላው ፍጡር አከበርናቸው*፡፡ በየብስ እና በባህርም አሳፈርናቸው፡፡ ከመልካሞችም ሲሳዮች ሰጠናቸው፡፡ *ከፈጠርናቸውም ፍጡሮች በብዙዎቹ ላይ ማብለጥን አበለጥናቸው*፡፡ وَلَقَدْ كَرَّمْنَا بَنِىٓ ءَادَمَ وَحَمَلْنَٰهُمْ فِى ٱلْبَرِّ وَٱلْبَحْرِ وَرَزَقْنَٰهُم مِّنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَفَضَّلْنَٰهُمْ عَلَىٰ كَثِيرٍ مِّمَّنْ خَلَقْنَا تَفْضِيلًا

አላህ የአደምንም ልጆች ከሌላው ፍጡር ያከበረበት እና ያበለጠበት በሁለት ነገር ነው፤ አንደኛው ዐቅል በመስጠት ነው፤ ዐቅል” عَقل ማለት “ግንዛቤ”Metacognition” ማለት ነው፤ የሰው ልጅ “አዕምሮ” እራሱ “ዐቅል” ይባላል፤ ዐቅል የጥበብ ተውህቦ”faculty” ነው፤ አላህ አደምን ስሞችን ሁሏንም አስተማረው፤ ሰው ያላወቀውን ሁሉ አሳውቆታል፡-
2፥31 *አደምንም ስሞችን ሁሏንም አስተማረው*፡፡ ከዚያም በመላእክት ላይ ተጠሪዎቹን አቀረባቸው፡፡ «እውነተኞችም እንደኾናችሁ የእነዚህን ተጠሪዎች ስሞች ንገሩኝ» አላቸው፡፡ وَعَلَّمَ ءَادَمَ ٱلْأَسْمَآءَ كُلَّهَا ثُمَّ عَرَضَهُمْ عَلَى ٱلْمَلَٰٓئِكَةِ فَقَالَ أَنۢبِـُٔونِى بِأَسْمَآءِ هَٰٓؤُلَآءِ إِن كُنتُمْ صَٰدِقِينَ
96፥4-5 ያ በብርዕ ያስተማረ፡፡ *ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲኾን*፡፡ ٱلَّذِى عَلَّمَ بِٱلْقَلَمِ عَلَّمَ ٱلْإِنسَٰنَ مَا لَمْ يَعْلَمْ

ሁለተኛው ቀውል በመስጠት ነው፤ “ቀውል” لْقَوْ ማለት “አንደበት”articulate speech” ማለት ነው፤ ሰው ስሜቱንና ሃሳቡን የሚገልፅበት ቋንቋ ነው፤ ሰውን መናገር ያስተማረው አላህ ነው፡-
55፥3-4 ሰውን ፈጠረ። *መናገርን አስተማረው*። َخَلَقَ ٱلْإِنسَٰنَ عَلَّمَهُ ٱلْبَيَان

የሥነ-ቋንቋ ጥናት”Linguistics” ምሁራን እንደሚያትቱት የሰው ልጆች የጋራ የሆነ ሰዋስው”grammar” አላቸው፤ በዚህ አንዱ የሌላውን ቋንቋን በመልመድ ይግባባል፤ ሁሉም ቋንቋ ውስጥ ጋር ስም፣ ተውላጠ-ስም፣ ግስ፣ ተውሳከ-ግስ፣ ገላጭ፣ መስተጻምር፣ መስተዋድድ እና ቃል-አጋኖ አለ።
በዓለማችን ላይ ከአምስት ሺ እስከ ስምንት ሺ ቋንቋዎች አሉ፤ እነዚህ ቋንቋዎች የመጡበት የራሳቸው ቤተሰብ አላቸው፤ አፍሮ-አሲያቲክ፣ ኢንዶ-ኢሮፒያን፣ ናይሎ-ሰሃራን፣ አዩስትሮ-አሲያቲክ ወዘተ ይባላሉ። አፍሮ-አሲያቲክ ቤተሰብ ውስጥ ሴሚቲክ፣ አሞቲክ፣ ኩሽቲክ፣ ቻዲክ ወዘተ ናቸው። የሴሜቲክ ዝርያ ውስጥ ዐረማይክ፣ ዕብራይስጥ፣ ዐረቢኛ፣ ግዕዝ፣ ዓካድ ወዘተ ናቸው። ወደድንም ጠላን እነዚህ ሁሉ ቋንቋዎች መሰረታቸው አንድ ቋንቋ ነው፤ ለምሳሌ በዐረቢኛ “አሊፍ” ا በዐረማይክ “አሊፍ” ܐ በዕብራይስጥ “አሌፍ” א በግሪክ “አልፋ” Ἀλφα ነው፤ በዐረቢኛ “ባ” ب በዐረማይክ “ባ” ܒ በዕብራይስጥ “ቤት” ב በግሪክ “ቤታ” βῆτα ነው፤ ይህ መመሳሰል ቋንቋዎች መሰረታቸው አንድ ቋንቋ መሆኑን ያሳያል፤ እያንዳንዱ ፊደላት ትርጉሙ በሁሉም አንድ ነው፤ ለምሳሌ “አሌፍ” ማለት “መጀመሪያ” ወይም “በሬ” ማለት ነው፤ “ባ” ማለት “ቤት” ማለት ነው፤ “ጂም” ማለት “ግመል” ማለት ነው። ይህንን በሌሎች ቋንቋዎች ተመሳሳይ ትርጉም አለው።

ይህ የመጀመሪያው የአደም ቋንቋ ማን ነው? የሚለው ብዙ መላምት ቢኖርም፤ አብላጫውን የቋንቋ ምሁራን መላምት ዐረማይክ የሚል መረጃ ነው ያለው፤ ለማንኛውም የቋንቋዎቻችን መለያየት ከአላህ አስደናቂ ምልክቶቹ ነው፤ በዚህ ውስጥ ለዐዋቂዎች ተዓምራቶች አሉበት፡-
30፥22 ሰማያትንና ምድርንም መፍጠሩ፣ *የቋንቋዎቻችሁና የመልኮቻችሁም መለያየት፣ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው*። በዚህ ውስጥ *ለዐዋቂዎች ተዓምራቶች አሉበት*። وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦ خَلْقُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَٱخْتِلَٰفُ أَلْسِنَتِكُمْ وَأَلْوَٰنِكُمْ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّلْعَٰلِمِين

አላህ ነብያትን ሲልክ በወቅቱ የተወለዱበት ማህበረሰብ ሊግባቡበት በሚችል ቋንቋ ነው፡-
14፥4 ከመልክተኛ ማንኛውንም ለእነርሱ ያብራራላቸው ዘንድ *በህዝቦቹ ቋንቋ እንጂ በሌላ አልላክንም*። وَمَآ أَرْسَلْنَا مِن رَّسُولٍ إِلَّا بِلِسَانِ قَوْمِهِۦ لِيُبَيِّنَ لَهُمْ ۖ فَيُضِلُّ ٱللَّهُ مَن يَشَآءُ وَيَهْدِى مَن يَشَآءُ ۚ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيم

“ቀውም” قَوْم “ህዝብ” በአንድ አካባቢ ተመሳሳይ ባህል፣ ቋንቋ፣ አኗኗር፣ ታሪክ፣ መንግሥት እና ቦታ ያለው ማህበረሰብን ያመለክታል፣ ሙሳ ነብይ ሆኖ በተነሳበት ዘመን አላህ ሙሳን ወደ ህዝቦቹ “በታምራታት” እንደላከው እነዚያም ህዝቦች “ፈሮዖንና ሹማምንቶቹ” የሚጠቀልል መሆኑን ለማመልከት “ወደ ፈሮዖንና ወደ ሹማምንቶቹ በእርግጥ ላክን” በማለት ይናገራል፡-
14:5 ሙሳንም፤ “ሕዝቦችህን” ከጨለማዎች ወደ ብርሃን አውጣ፤ የአላህንም ቀኖች አስገንዝባቸው፤ በማለት *”በታምራታችን” በእርግጥ “ላክነው”*፤ وَلَقَدْ أَرْسَلْنَا مُوسَىٰ بِـَٔايَٰتِنَآ أَنْ أَخْرِجْ قَوْمَكَ مِنَ ٱلظُّلُمَٰتِ إِلَى ٱلنُّورِ وَذَكِّرْهُم بِأَيَّىٰمِ ٱللَّهِ
43:46 ሙሳንም *”በታምራቶቻችን” ወደ ፈሮዖንና ወደ ሹማምንቶቹ በእርግጥ “ላክን”*፤ እኔ የአለማት ጌታ መልክተኛ ነኝ አላቸውም። وَلَقَدْ أَرْسَلْنَا مُوسَىٰ بِـَٔايَٰتِنَآ إِلَىٰ فِرْعَوْنَ وَمَلَإِيْهِۦ فَقَالَ إِنِّى رَسُولُ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِين

በተጨማሪም ኢብኑ ከሲር ነብዩላህ ዩኑስ የተላከው ለነነዌ ሰዎች እንደሆነ የነነዌ ሰዎች ደግሞ መውሲል እንደሆኑ ይናገራል፤ መውሲል ያሁኑ ሰሜናዊ ኢራቅ እንደሆነ የታሪክ ምሁራን ይናገራሉ፤ ኢብኑ ሳድ በኪታቡ ዩኑስ ከቤተ-እስራኤል እንደሆነ ይተርካል፣ ታዲያ ህዝብ ማለት የትውልድ የዘር ሃረግ ቢሆን ኖሮ አላህ የነነዌ ሰዎችን የዩኑስ ህዝብ ብሎ ባልተናገረ ነበር፡-
10:98 *”የዩኑስ ሕዝቦች” ´“ባመኑ ጊዜ” በቅርቢቱ ሕይወት የውርደትን ቅጣት ከእነሱ ላይ አነሳንላቸው። “እስከ ጊዜም ድረስ አጣቀምናቸው”*። فَلَوْلَا كَانَتْ قَرْيَةٌ ءَامَنَتْ فَنَفَعَهَآ إِيمَٰنُهَآ إِلَّا قَوْمَ يُونُسَ لَمَّآ ءَامَنُوا۟ كَشَفْنَا عَنْهُمْ عَذَابَ ٱلْخِزْىِ فِى ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا وَمَتَّعْنَٰهُمْ إِلَىٰ حِينٍ
37:147 *ወደ መቶ ሺሕ ሰዎችም “ላክነው”። ከቶውንም ይጨምራሉ። “አመኑም”። “እስከ ጊዜ ድረስም አጣቀምናቸው”*። ۞وَأَرْسَلْنَٰهُ إِلَىٰ مِاْئَةِ أَلْفٍ أَوْ يَزِيدُونَ فَـَٔامَنُوا۟ فَمَتَّعْنَٰهُمْ إِلَىٰ حِين

ፖለቲካ

ገቢር አንድ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

5፥48 *በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ*፡፡ فَاحْكُم بَيْنَهُم بِمَا أَنزَلَ اللَّه

ኢሥላም አጠቃላይ የሕይወት ዘይቤ ይዟል፤ ይህም ዘይቤ መንፈሳዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ዘይቤ ነው። “ፖለቲካ” πολιτικά የሚለው የግሪክ ቃል “ፖሊቲኮስ” πολιτικός ማለት “ዜግነት”citizen” ከሚል ቃል የመጣ ሲሆን “ፖሊስ” πόλις ማለትም “ከተማ” እና “ፖሊተስ” πολίτης ማለትም “ፖሊስይ” ያቀፈ የአስተዳደር ጥበብ ነው፤ በጥንቷ ሄለናዊ ግሪክ ከተማ የምትመራበት ፖሊሲይ ፖለቲካ ይባል ነበር። በጥቅሉ ፖለቲካ ማለት በፖሊስይ ማለትም በመርሕ ዜጎችም የሚመራ ሥነ-መንግሥት ጥናት ነው፤ ሕገ-መንግሥት”constitution” ማለት ደግሞ የመንግሥት መርሕ፣ ሕግ እና መመሪያ ነው፤ “መንግሥት” አገዛዝ” “ኃይል” “ሥልጣን” በግሪክ “ክራቶስ” κράτος ይባላል፤ “ክራሲ” የሚለው ቃል “ክራቶስ” ከሚለው ግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን የመንግሥት ቅርፅ መዳረሻ ቅጥያ ሆኖ ሲመጣ የተለያየ የመንግሥት እርከን ይሆናል፤ ይህንን ነጥብ በነጥብ እንመልከት፡-

ነጥብ አንድ
“ፕሉቶ-ክራሲ”
“ፕሉቶ-ክራሲ” ማለት “የሃብት አገዛዝ” ማለት ነው፤ “ፕሉቶስ” πλοῦτος ማለት “ሃብት” ማለት ነው፤ ይህ አገዛዝ ሃብት ያላቸው ሃብታሞች ሃብት ስላላቸው በሃብታቸው የሚገዙበት ሥርዓት ነው፤ ይህ እሳቤ በድህረ ዘመነ አብርሆት ውድቅ ሆኗል።

ነጥብ ሁለት
“አርስቶ-ክራሲ”
“አርስቶ-ክራሲ” ማለት “የልዕልና አገዛዝ” ማለት ነው፤ “አርስቶስ” ἄριστος ማለት “ልዕልና” ማለት ነው፤ ይህ አገዛዝ ልዕልና ያላቸው ልዑላን በልዕልናቸው የሚገዙበት ሥርዓት ነው፤ እኛ ምርጥ ዘር ነን የሚል አቋም አላቸው፤ ይህ እሳቤ በድህረ ዘመነ አብርሆት ውድቅ ሆኗል።

ነጥብ ሥስት
“አውቶ-ክራሲ”
“አውቶ-ክራሲ” ማለት “የኃይል አገዛዝ” ማለት ነው፤ “አውቶስ” αὐτός ማለት “ኃይል” ማለት ነው፤ ይህ አገዛዝ ኃይል ያላቸው ኃያላን በኃይላቸው የሚገዙበት ሥርዓት ነው፤ ይህ እሳቤ በተለይ የሞናርኪስም እሳቤ በሳውዲ፣ በዖማን፣ በሲዊዘርላድ፣ በደቡብ ኮርያ ወዘተ ያለ እሳቤ ነው፤ ይህ እሳቤ እየወደቀ ነው፤ ቅርብ ቀን ኢንሻላህ ሙሉ ለሙሉ ይወድቃል።

ነጥብ አራት
“ዲሞ-ክራሲ”
“ዲሞ-ክራሲ” ማለት “የሕዝብ አገዛዝ” ማለት ነው፤ “ዴሞስ” δημο ማለት “ሕዝብ” ማለት ነው፤ ይህ አገዛዝ በሕዝብ ምርጫ በተወካዮች ምክር ቤት ወይም በክልል ምክር ቤት ውስጥ የተመረጠው ሰው የሚገዛበት ሥርዓት ነው፤ ሕገ-መንግሥቱን የሚያረቁት ከአእምሮ አፍልቀው ነው።

ነጥብ አምስት
“ቴክኖ-ክራሲ”
“ቴክኖ-ክራሲ” ማለት “የሙያ አገዛዝ” ማለት ነው፤ “ቴክኖስ” τέχνη ማለት “ሙያ”skill” ወይም “እደ-ሙያ”craft” ማለት ነው፤ ይህ አገዛዝ በእያንዳንዱ ሚኒስትሪ ሚኒስቴ መሆን ያለበት የሙያው ባለቤት ነው የሚል እሳቤ ነው፤ ለምሳሌ በጤና ሚኒስትሪ ሜዲካል ያጠና ዶክተር፤ በትምህርት ሚኒስቴር ፔዳጎጂ ያጠና ሚኒስተር፣ በግብርና ሚኒስትሪ ግብርና ያጠና ሚኒስቴር ወዘተ የሚመራበት እሳቤ ነው። “ሚንስትሪ” ማለት “አገልግሎት” ማለት ሲሆን “ሚንስተር” ማለት “አገልጋይ” ማለት ነው፤ ይህ እሳቤ በአንጻራዊ ተመራጭ ነው።

ፖለቲካ

ገቢር ሁለት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

3፥189 *የሰማያትና የምድር ንግሥና ለአላህ ብቻ ነው*፡፡ አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው፡፡ وَلِلَّهِ مُلْكُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۗ وَاللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِير

ነጥብ ሥድስት
“ቴኦ-ክራሲ”
“ቴኦ-ክራሲ” ማለት “የአምላክ አገዛዝ” ማለት ነው፤ “ቴኦስ” θεός ማለት “አምላክ” ማለት ነው፤ በክፍል አንድ ያየናቸው የአገዛዝ ቅርጽ ምክር ቤት ውስጥ ያሉትን ሕገ-መንግሥት የሚያረቁት ከሰው አእምሮ ነው፤ ነገር ግን በቴኦክራሲ ቅርጽ መመሪያው መለኮታዊ ብቻ ነው። “መጅሊስ” مجلس የሚለው የዐረቢኛ ቃል “ሲኖዶስ” σύνοδος የሚለው የግሪክ ቃል ትርጉማቸው “ምክር ቤት”council” ማለት ነው፤ እዚህ ምክር ቤት ውስጥ ሕገ-መንግሥቱ ሸሪዓህ ነው፤ “ሸሪዓህ” شَرِيعَة የሚለው ቃል “ሺርዓህ” شِرْعَة ማለትም “ሕግ” ከሚለው የስም መደብ የመጣ ሲሆን “ትክክለኛ ሕግ” ማለት ነው፡-
45፥18 *ከዚያም ከነገሩ ከሃይማኖት “በትክክለኛይቱ ሕግ” ላይ አደረግንህ*፡፡ ثُمَّ جَعَلْنَاكَ عَلَىٰ شَرِيعَةٍ مِّنَ الْأَمْرِ
5፥48 *ከእናንተ ለሁሉም ሕግን እና መንገድን አደረግን*፡፡ لِكُلٍّ جَعَلْنَا مِنكُمْ شِرْعَةً وَمِنْهَاجًا

አላህ ለሁሉም መልእክተኞች “ሕግ” እና “መንገድ” አድርጓል፤ “መንገድ” ተብሎ የተቀመጠው ቃል “ሚንሃጅ” مِنْهَاج ማለትም “ፋና” ማለት ሲሆን “መንሃጅ” منهاج የሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ይህ ሕግ የሚዋቀረው ውቅር አራት ሲሆኑ፤ እነርሱም፡-
1ኛ. “ቁርኣን” قرآن ማለትም የአላህ ቃል፣
2ኛ. “ሡናህ” سنة የነብያችን”ﷺ” ሰሒህ ሐዲስ፣
3ኛ. “ቂያሥ” قياس “ማመጣጠን”Analogy”
4ኛ. “ኢጅማዕ” إجماع ማለትም የዐሊሞች ስብስብ ናቸው።

ስለዚህ ፍርድ ከአላህ በወረደው ሕግ ይፈረዳል፡-
5፥48 *በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ*፡፡ فَاحْكُم بَيْنَهُم بِمَا أَنزَلَ اللَّه

“ፍረድ” ለሚለው ቃል የተጠቀመበት “ፈሕኩም” فَاحْكُم ሲሆን “ሑክም” ለሚለው የግስ መደብ ነው፤ “ሑክም” حُكْم የሚለው ቃል”ሐከመ” حَكَم ማለትም “ፈረደ” የመጣ ሲሆን ፍርድ” ወይም “ሕግ” ማለት ነው፤ “አሕካም” أحكام ደግሞ የሑክም ብዙ ቁጥር ነው፤ በኢስላም “ሕጎች” በአምስት ይከፈላሉ፤ እነርሱም፡-
1ኛ. “ፈርድ” فرض ማለትም “የታዘዘ”
2ኛ. “ሙሥተሐብ” مستحب” ማለትም “የተወደደ”
3ኛ. “ሙባሕ” مباح ማለትም “የተፈቀደ”
4ኛ. “መክሩህ” مكروه” ማለትም “የተጠላ”
5ኛ. “ሐራም” حرام” ማለትም “የተከለከለ” ናቸው።

“ፊቅህ” ፏقه ማለት “ጥልቅ መረዳት” ማለት ሲሆን የሥነ-ሕግ ጥናት”the study of law” ነው፤ ሕግ አዋቂ ደግሞ “ፈቂህ” ፏقيه ይባላል፤ “ፊቅህ” ማለት ቋንቋዊ ትርጉሙ “መረዳት” ማለት ነው፡-
6፥98 *”ለሚያወቁ” ሕዝቦች አንቀጾችን በእርግጥ ዘረዘርን*:: قَدْ فَصَّلْنَا الْآيَاتِ لِقَوْمٍ يَفْقَهُون

“ሚያወቁ” ተብሎ የተቀመጠው ቃል “የፍቀሁነ” يَفْقَهُون ሲሆን “ሚረዱ” ማለት ነው። ሙስሊሙ የስልጣን ባለቤቶች ለሆኑት ለአሚሮቻችን ይታዘዛል፤ የሚያወዘግብ ነገር ካለ ወደ አላህ ቁርኣን እና ወደ መልእክተኛው ሐዲስ መረጃ እና ማስረጃ ማግኘት ነው፡-
4፥59 እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገዙ፤ መልክተኛው እና *ከእናንተም የስልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ*:: በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህ እና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትኾኑ *የተከራከራችሁበትን ነገር ወደ አላህ እና ወደ መልክተኛው መልሱት*:: ይህ የተሻለ መጨረሻውም ያማረ ነው:: يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا أَطِيعُوا اللَّهَ وَأَطِيعُوا الرَّسُولَ وَأُولِي الْأَمْرِ مِنكُمْ ۖ فَإِن تَنَازَعْتُمْ فِي شَيْءٍ فَرُدُّوهُ إِلَى اللَّهِ وَالرَّسُولِ إِن كُنتُمْ تُؤْمِنُونَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ ۚ ذَٰلِكَ خَيْرٌ وَأَحْسَنُ تَأْوِيلًا

ቀደምት ሰለፎች የስልጣን ባለቤቶች የሆኑትን ኸሊፋዎች ይታዘዙ ነበር። “ኸሊፋህ” ፏخَلِيفَة ማለት “ምትክ” ማለት ሲሆን “ኺላፋህ” ፏخِلافة ማለት ደግሞ “ተተኪ” ማለት ነው፤ ከ 632–661 ድህረ-ልደት”AD” የነበሩት “አል-ኺላፈቱ አር-ረሺዳህ” ፏاَلْخِلَافَةُ اَلرَّاشِدَة ማለትም “ትክክለኛ ተተኪ” አቡበከር ሲዲቅ፣ ዑመር ኢብኑል ኸጧብ፣ ዑስማን ኢብኑ ዐፋን እና ዐሊይ ኢብኑ አቡ ጧሊብ ናቸው። ስለ እነርሱ ዘመነ-መግቦት ነብያችን”ﷺ” እንዲህ በትንቢት ይናገራሉ፡-
ሱነን አቢ ዳውድ መጽሐፍ 42, ሐዲስ 51
ሠፊናህ እንደተረከው፡- *”የአላህ መልእክተኛም”ﷺ” አሉ፡- “የነብያዊ ኺላፋህነት ሰላሳ ዓመት ነው፤ ከዚያም አላህ መንግሥትን ለሚሻው ይሰጣል፤ ወይም የእርሱን መንግሥት ለሚሻው ያመጣል፤ ሠዒድም ለሠፊናህ እንደተናገረው፡- “የአቡበከር ኸሊፋነት ሁለት ዓመት፣ ዑመር አስር ዓመት፣ ዑስማን አስራ ሁለት ዓመት፣ ዐሊይ እንዲህና እንዲያ(6 ዓመት) አሰላው*። عَنْ سَفِينَةَ، قَالَ قَالَ رَسُولُ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم “ خِلاَفَةُ النُّبُوَّةِ ثَلاَثُونَ سَنَةً ثُمَّ يُؤْتِي اللَّهُ الْمُلْكَ – أَوْ مُلْكَهُ – مَنْ يَشَاءُ ” . قَالَ سَعِيدٌ قَالَ لِي سَفِينَةُ أَمْسِكْ عَلَيْكَ أَبَا بَكْرٍ سَنَتَيْنِ وَعُمَرَ عَشْرًا وَعُثْمَانَ اثْنَتَىْ عَشْرَةَ وَعَلِيٌّ كَذَا .

እንደሚታወቀው የመጨረሻው ዘመን ጥናት”Eschatology” በኢስላም “አል-አኺሩል ዘማን” لَلْآخِر لَلْزَمَان ይባላል፤ የመጨረሻው ዘመን ምልክቶች በሁለት ይከፈላሉ፤ አንዱ ንዑሣን ምልክቶች ሲሆኑ ሁለተኛ ዐበይት ምልክቶች ናቸው፤ የኺላፋህ ሥርዓት ተመልሶ መምጣት ከንዑሳን ምልክቶች አንዱ ሲሆን በነብያችን”ﷺ” ትንቢት ውስጥ እንዲህ ተቀምጧል፡-
ኢማም አሕመድ መጽሐፍ 14, ሐዲስ 163
ሑደይፋህ ኢብኑል-የማን እንደተረከው፡- “የአላህ መልእክተኛ”ﷺ” እንዲህ አሉ፡- *”ነብይነት አላህ እስከፈቀደው ጊዜ ይቆያል፤ ከዚያም በነብይነት ሚንሃጅ ኺላፋህ ይጀመርና አላህ እስከፈቀደው ጊዜ ይቆያል፤ ከዚያም ዘውዳዊ ንግሥና ቦታውን ይይዝና አላህ እስከፈቀደው ጊዜ ይቆያል፤ ከዚያም የአንባገነን ንግሥና ይነሳልና አላህ እስከፈቀደው ጊዜ ይቆያል፤ ከዚያም በስተመጨረሻም በነብይነት ሚንሃጅ ኺላፋህ ከእንደገና ይመጣል*። » :- فَقَالَ حُذَيْفَةُ: قَالَ رَسُولُ اللَّهِ – صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ تَكُونُ النُّبُوَّةُ فِيكُمْ مَا شَاءَ اللَّهُ أَنْ تَكُونَ ثُمَّ يَرْفَعُهَا إِذَا شَاءَ أَنْ يَرْفَعَهَا، ثُمَّ تَكُونُ خِلاَفَةٌ عَلَى مِنْهَاجِ النُّبُوَّةِ فَتَكُونُ مَا شَاءَ اللَّهُ أَنْ تَكُونَ ثُمَّ يَرْفَعُهَا إِذَا شَاءَ اللَّهُ أَنْ يَرْفَعَهَا، ثُمَّ تَكُونُ مُلْكًا عَاضًّا فَيَكُونُ مَا شَاءَ اللَّهُ أَنْ يَكُونَ ثُمَّ يَرْفَعُهَا إِذَا شَاءَ أَنْ يَرْفَعَهَا، ثُمَّ تَكُونُ مُلْكًا جَبْرِيَّةً فَتَكُونُ مَا شَاءَ اللَّهُ أَنْ تَكُونَ ثُمَّ يَرْفَعُهَا إِذَا شَاءَ أَنْ يَرْفَعَهَا، ثُمَّ تَكُونُ خِلاَفَةً عَلَى مِنْهَاجِ النُّبُوَّة

የነብያችን”ﷺ” ነብይነት ቆይታው እንደ ጎርጎሮሳውን አቆጣጠር ከ 610-632 ድህረ-ልደት ነበር፤ ከዚያም በነብያችን”ﷺ” ፋና አል-ኺላፈቱ አር-ረሺዳህ ከ 632-661 ድህረ-ልደት ነበር፤ ከዚያ የበኑ ኡመያድ ሥርወ-መንግሥት እና የበኑ ዐባሥ ሥርወ-መንግሥት ዘውዳዊ ንግሥና ሆኖ ከ 661-1258 ድህረ-ልደት ነበር፤ ከዚያም ከ 1258 ድህረ-ልደት እስከ ዘመናችን የአንባገነኖቹ ነገሥታት ጊዜ ውስጥ ነን፤ ከዚያም ኢንሻላህ በነብያችን”ﷺ” ፋና እንደገና የኺላፋህ ሥርዓት ይመለሳል።

ፓለቲካ

ገቢር ሦስት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው::

25፥26 *እውነተኛው ንግሥና በዚያ ቀን ለአልራሕማን ብቻ ነው*:: በከሓዲዎችም ላይ አስቸጋሪ ቀን ነው:: الْمُلْكُ يَوْمَئِذٍ الْحَقُّ لِلرَّحْمَـٰنِ ۚ وَكَانَ يَوْمًا عَلَى الْكَافِرِينَ عَسِيرًا

የኢስላም ሊሂቃን የመጨረሻው ዘመን ጥናት ዘርፈ ብዙ እና መጠነ ሰፊ እንደሆነ ያትታሉ፤ ከእነዚህ ጥናት አንዱ ቴኦክራሲ በትክክል የሚያመጣው መሪ ነው፤ ይህ መሪ የተጻውዖ ስሙ ሙሐመድ ሲሆን የአባቱ ስም አብደሏህ ነው፡-

ሱነን አቢ ዳውድ መጽሐፍ 38, ሐዲስ 4
ዐብደላህ ኢብኑ መሥዑድ እንደተረከው፡- *"ነብዩም"ﷺ" አሉ፡- "ከቀን በስተቀር ከዱንያህ ምንም ባይቀር(ዛሒዳህ በሐዲሱ እንደተናገረው) አላህ ያንን ቀን እስከ ከእኔ ወይም ከአህለል በይት እስከሚነሳው ሰው ድረስ ያረዝመዋል፤ እርሱም ስሙ የእኔን ስም የአባቱ ስም የአባቴ ስም ይሆናል። ምድር በበደል እንደተሞላች በፍትሕ እና በእኩልነት ያስተዳድራል*። عَنْ عَبْدِ اللَّهِ، عَنِ النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم قَالَ " لَوْ لَمْ يَبْقَ مِنَ الدُّنْيَا إِلاَّ يَوْمٌ " . قَالَ زَائِدَةُ فِي حَدِيثِهِ " لَطَوَّلَ اللَّهُ ذَلِكَ الْيَوْمَ " . ثُمَّ اتَّفَقُوا " حَتَّى يَبْعَثَ فِيهِ رَجُلاً مِنِّي " . أَوْ " مِنْ أَهْلِ بَيْتِي يُوَاطِئُ اسْمُهُ اسْمِي وَاسْمُ أَبِيهِ اسْمَ أَبِي . زَادَ فِي حَدِيثِ فِطْرٍ

ይህ መሪ የማዕረግ ስሙ ደግሞ አል-መህዲ ይባላል፤ "አል-መህዲ" الْمَهْدِيُ ማለት "መሪው"The Guided one" ማለት ነው፤ ይህ መህዲ የሚመጣው ከአህለል በይት ነው። "አህለል በይት" أَهْلَ الْبَيْت ማለት "የነብያችን"ﷺ" ቤተሰብ" ማለት ነው፡-
ሱነን ኢብኑ ማጃህ መጽሐፍ 36, ሐዲስ 160
ዐሊይ እንደተረከው፡- የአላህ መልእክተኛ"ﷺ" እንዲህ አሉ፡- *"አል-መህዲ ከአህለል በይት ነው፤ አላህ በአንድ ሌሊት ያስነሳዋል"*። " عَنْ عَلِيٍّ، قَالَ قَالَ رَسُولُ اللَّهِ ـ صلى الله عليه وسلم ـ " الْمَهْدِيُّ مِنَّا أَهْلَ الْبَيْتِ يُصْلِحُهُ اللَّهُ فِي لَيْلَةٍ
ሱነን አቢ ዳውድ መጽሐፍ 38, ሐዲስ 6
ኡሙ ሠለማህ ከአላህ መልእክተኛ"ﷺ" ሰምታ እንደተረከችው፡- እርሳቸው፡- *"አል-መህዲ ከእኔ ቤተሰብ ነው፤ ከፋጢማህ የዘር-ሃረግ ነው" አሉ*። عَنْ أُمِّ سَلَمَةَ، قَالَتْ سَمِعْتُ رَسُولَ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم يَقُولُ الْمَهْدِيُّ مِنْ عِتْرَتِي مِنْ وَلَدِ فَاطِمَةَ

ይህ መህዲ ከፋጢማህ የዘር-ሃረግ የሚመጣ ሲሆን ጭቆና እና አምናገነንነት አስወግዶ ምድርን በእኩልነት እና በፍትሕ በመሙላት ለሰባት ዓመት ይገዛል፡-
ሱነን አቢ ዳውድ መጽሐፍ 38, ሐዲስ 7
አቢ ሠዒድ አል-ኹድሪይ እንደተረከው፡- *"የአላህ መልእክተኛም"ﷺ" አሉ፡- "አል-መህዲ ከእኔ አብራክ ነው፤ ሰፊ ግንባር የታወቀ አፍንጫ ይኖረዋል፤ ጭቆና እና አምናገነንነት ምድርን እንደተሞላች በእኩልነት እና በፍትሕ ምድርን ይሞላታል፤ ሰባት ዓመት ይገዛል*። عَنْ أَبِي سَعِيدٍ الْخُدْرِيِّ، قَالَ قَالَ رَسُولُ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم " الْمَهْدِيُّ مِنِّي أَجْلَى الْجَبْهَةِ أَقْنَى الأَنْفِ يَمْلأُ الأَرْضَ قِسْطًا وَعَدْلاً كَمَا مُلِئَتْ جَوْرًا وَظُلْمًا يَمْلِكُ سَبْعَ سِنِينَ "

ይህ መሪ የመርየምን ልጅ ዒሣን እንዲያሰግድ ይጋብዘዋል፡-
ኢማም ሙስሊም መጽሐፍ 1, ሐዲስ 302
ጃቢ ኢብኑ ዐብደላህ እንደዘገበው፡- "ነብዩ"ﷺ" እንዲህ ሲሉ ሰምቻለው፡- *"ከእኔ ኡማ የሆኑ በእውነት ቢሆን እንጂ አይታገሉም፤ እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ ያሸንፋሉ። ከዚያም ዒሣ የመርየም ልጅ ይወርዳል፤ መሪያቸውም ዒሣን በሶላት እንዲመራ ይጠይቀዋል፤ ዒሣም፡- "አይሆንም! በመካከላችሁ መሪ አለ" ይላል፤ ይህ ከአላህ ለዚህ ኡማህ ክብር ነው*። أَنَّهُ سَمِعَ جَابِرَ بْنَ عَبْدِ اللَّهِ، يَقُولُ سَمِعْتُ النَّبِيَّ صلى الله عليه وسلم يَقُولُ " لاَ تَزَالُ طَائِفَةٌ مِنْ أُمَّتِي يُقَاتِلُونَ عَلَى الْحَقِّ ظَاهِرِينَ إِلَى يَوْمِ الْقِيَامَةِ – قَالَ – فَيَنْزِلُ عِيسَى ابْنُ مَرْيَمَ صلى الله عليه وسلم فَيَقُولُ أَمِيرُهُمْ تَعَالَ صَلِّ لَنَا . فَيَقُولُ لاَ . إِنَّ بَعْضَكُمْ عَلَى بَعْضٍ أُمَرَاءُ . تَكْرِمَةَ اللَّهِ هَذِهِ الأُمَّةَ "

የመርየምን ልጅ ዒሣም ተመልሶ ሲመጣ የሙስሊሙ መሪ ይሆናል፤ መሪ የሚሆነውም በቁርአን እና በነብያችን"ﷺ" ሱና መመሪያ ነው፡-

ኢማም ሙስሊም መጽሐፍ 1, ሐዲስ 300

አቢ ሁረይራ"ረ.ዐ" እንደተረከው፡- *"የአላህ መልእክተኛም"ﷺ" እንዲህ አሉ፡- "በመካከላችሁ የመርየም ልጅ በወረደ ጊዜ እና ሲመራችሁ ምን ታደርጋላችሁ? "*። قَالَ رَسُولُ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم " كَيْفَ أَنْتُمْ إِذَا نَزَلَ ابْنُ مَرْيَمَ فِيكُمْ وَأَمَّكُمْ

ኢማም ሙስሊም መጽሐፍ 1, ሐዲስ 301

አቢ ሁረይራ"ረ.ዐ" እንደተረከው፡- *"የአላህ መልእክተኛም"ﷺ" እንዲህ አሉ፡- "በመካከላችሁ የመርየም ልጅ በወረደ ጊዜ እና ሲመራችሁ ምን ታደርጋላችሁ? ኢብኑ አቢ ዚዕብም አቢ ሁረይራ የዘገበው መሰረት አድርጎ፡- "ሲመራችሁ ምን ታደርጋላችሁ?" ምን ማለት ነው? አለ፤ እኔም ለእኔ አብራራልኝ አልኩኝ፤ እርሱም አለ፡- "በጌታችሁ ተባረከ ወተዓላ መጽሐፍ እና በመልእክተኛው በነብያችሁ"ﷺ" ፈለግ ይመራችኃል" አለ*። أَنَّ رَسُولَ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم قَالَ " كَيْفَ أَنْتُمْ إِذَا نَزَلَ فِيكُمْ ابْنُ مَرْيَمَ فَأَمَّكُمْ مِنْكُمْ . فَقُلْتُ لِابْنِ أَبِي ذِئْبٍ إِنَّ الأَوْزَاعِيَّ حَدَّثَنَا عَنِ الزُّهْرِيِّ عَنْ نَافِعٍ عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ " وَإِمَامُكُمْ مِنْكُمْ " . قَالَ ابْنُ أَبِي ذِئْبٍ تَدْرِي مَا أَمَّكُمْ مِنْكُمْ قُلْتُ تُخْبِرُنِي . قَالَ فَأَمَّكُمْ بِكِتَابِ رَبِّكُمْ تَبَارَكَ وَتَعَالَى وَسُنَّةِ نَبِيِّكُمْ صلى الله عليه وسلم .

ማንኛውም ንጉሥ፣ ኸሊፋህ ወይም አሚር ሚች ነው፤ አላህ ግን በምንነቱ የማይሞት እውነተኛ ንጉሥ ነው፡-

20፥114 *እውነተኛው ንጉሥ አላህም ከሐዲዎች ከሚሉት ላቀ*። ወደ አንተ መወረዱም ከመፈጸሙ በፊት በማንበብ አትቸኩል። «ጌታዬ ሆይ! ዕውቀትንም ጨምርልኝ» በል። فَتَعَالَى اللَّهُ الْمَلِكُ الْحَقُّ ۗ وَلَا تَعْجَلْ بِالْقُرْآنِ مِن قَبْلِ أَن يُقْضَىٰ إِلَيْكَ وَحْيُهُ ۖ وَقُل رَّبِّ زِدْنِي عِلْمًا

እውነተኛ መንግሥት የአላህ መንግሥት ነው፤ ማንኛው ምድራዊ ንጉሥ ንግሥናው ጅማሬ አለው እንዲሁ ፍጻሜ አለው፤ ግን አላህ ንግሥናው መነሻ የሌለው ቀዳማይ መዳረሻ የሌለው ደኃራይ ነው። "ሙልክ" مُلْك የሚለው ቃል "መሊክ" مَلِك ማለትም "ንጉሥ" ከሚል የስም መደብ የመጣ ሲሆን "ንግሥና" "መንግሥት" ማለት ነው፤ የእርሱ ንግሥና ደግሞ የእርሱ ባህርይ ነው፤ የሰማያትና የምድር ንግሥና ሁሉ በትንሳኤ ቀን እውነተኛ ንጉሥ ለሆነው ለአላህ ብቻ ይሆናል፡-

25፥26 *እውነተኛው ንግሥና በዚያ ቀን ለአልራሕማን ብቻ ነው*። በከሓዲዎችም ላይ አስቸጋሪ ቀን ነው። الْمُلْكُ يَوْمَئِذٍ الْحَقُّ لِلرَّحْمَـٰنِ ۚ وَكَانَ يَوْمًا عَلَى الْكَافِرِينَ عَسِيرًا

እንግዲያውስ እውነተኛ ፓለቲካ ቴአክራሲ ብቻ ነው።

የኩፍር ፓለቲካ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።።

5፥48 *በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ*። فَاحْكُم بَيْنَهُم بِمَا أَنزَلَ اللَّهُ

ኢሥላም አጠቃላይ የሕይወት ዘይቤ ይዟል፤ ይህም ዘይቤ መንፈሳዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፓለቲካዊ ዘይቤ ነው። "ፓለቲካ" πολιτικά የሚለው የግሪክ ቃል "ፓሊቲኮስ" πολιτικός ማለት "ዜግነት"citizen" ከሚል ቃል የመጣ ሲሆን "ፓሊስ" πόλις ማለትም "ከተማ" እና "ፓሊተስ" πολίτης ማለትም "ፓሊስይ" ያቀፈ የአስተዳደር ጥበብ ነው፤ በጥንቷ ሄለናዊ ግሪክ ከተማ የምትመራበት ፓሊሲይ ፓለቲካ ይባል ነበር። በጥቅሉ ፓለቲካ ማለት በፓሊስይ ማለትም በመርሕ ዜጎችም የሚመራ ሥነ-መንግሥት ጥናት ነው፤ ሕገ-መንግሥት"constitution" ማለት ደግሞ የመንግሥት መርሕ፣ ሕግ እና መመሪያ ነው፤ "መንግሥት" አገዛዝ" "ኃይል" "ሥልጣን" በግሪክ "ክራቶስ" κράτος ይባላል፤ "ክራሲ" የሚለው ቃል "ክራቶስ" ከሚለው ግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን የመንግሥት ቅርፅ መዳረሻ ቅጥያ ሆኖ ሲመጣ የተለያየ የመንግሥት እርከን ይሆናል። ይህንን ነጥብ በነጥብ እንመልከት፡-

ነጥብ አንድ
“ፕሉቶ-ክራሲ”
“ፕሉቶ-ክራሲ” ማለት “የሃብት አገዛዝ” ማለት ነው፤ “ፕሉቶስ” πλοῦτος ማለት “ሃብት” ማለት ነው፤ ይህ አገዛዝ ሃብት ያላቸው ሃብታሞች ሃብት ስላላቸው በሃብታቸው የሚገዙበት ሥርዓት ነው፤ ይህ እሳቤ በድህረ ዘመነ አብርሆት ውድቅ ሆኗል።

ነጥብ ሁለት
“አርስቶ-ክራሲ”
“አርስቶ-ክራሲ” ማለት “የልዕልና አገዛዝ” ማለት ነው፤ “አርስቶስ” ἄριστος ማለት “ልዕልና” ማለት ነው፤ ይህ አገዛዝ ልዕልና ያላቸው ልዑላን በልዕልናቸው የሚገዙበት ሥርዓት ነው፤ እኛ ምርጥ ዘር ነን የሚል አቋም አላቸው፤ ይህ እሳቤ በድህረ ዘመነ አብርሆት ውድቅ ሆኗል።

ነጥብ ሥስት
“አውቶ-ክራሲ”
“አውቶ-ክራሲ” ማለት “የኃይል አገዛዝ” ማለት ነው፤ “አውቶስ” αὐτός ማለት “ኃይል” ማለት ነው፤ ይህ አገዛዝ ኃይል ያላቸው ኃያላን በኃይላቸው የሚገዙበት ሥርዓት ነው፤ ይህ እሳቤ በተለይ የሞናርኪስም እሳቤ በሳውዲ፣ በዖማን፣ በሲዊዘርላድ፣ በደቡብ ኮርያ ወዘተ ያለ እሳቤ ነው፤ ይህ እሳቤ እየወደቀ ነው፤ ቅርብ ቀን ኢንሻላህ ሙሉ ለሙሉ ይወድቃል።

ነጥብ አራት
“ዲሞ-ክራሲ”
“ዲሞ-ክራሲ” ማለት “የሕዝብ አገዛዝ” ማለት ነው፤ “ዴሞስ” δημο ማለት “ሕዝብ” ማለት ነው፤ ይህ አገዛዝ በሕዝብ ምርጫ በተወካዮች ምክር ቤት ወይም በክልል ምክር ቤት ውስጥ የተመረጠው ሰው የሚገዛበት ሥርዓት ነው፤ ሕገ-መንግሥቱን የሚያረቁት ከአእምሮ አፍልቀው ነው።

ነጥብ አምስት
“ቴክኖ-ክራሲ”
“ቴክኖ-ክራሲ” ማለት “የሙያ አገዛዝ” ማለት ነው፤ “ቴክኖስ” τέχνη ማለት “ሙያ”skill” ወይም “እደ-ሙያ”craft” ማለት ነው፤ ይህ አገዛዝ በእያንዳንዱ ሚኒስትሪ ሚኒስቴ መሆን ያለበት የሙያው ባለቤት ነው የሚል እሳቤ ነው፤ ለምሳሌ በጤና ሚኒስትሪ ሜዲካል ያጠና ዶክተር፤ በትምህርት ሚኒስቴር ፔዳጎጂ ያጠና ሚኒስተር፣ በግብርና ሚኒስትሪ ግብርና ያጠና ሚኒስቴር ወዘተ የሚመራበት እሳቤ ነው። “ሚንስትሪ” ማለት “አገልግሎት” ማለት ሲሆን “ሚንስተር” ማለት “አገልጋይ” ማለት ነው፤ ይህ እሳቤ በአንጻራዊ ተመራጭ ነው።

ነጥብ ሥድስት
“ቴኦ-ክራሲ”
“ቴኦ-ክራሲ” ማለት “የአምላክ አገዛዝ” ማለት ነው፤ “ቴኦስ” θεός ማለት “አምላክ” ማለት ነው፤ በክፍል አንድ ያየናቸው የአገዛዝ ቅርጽ ምክር ቤት ውስጥ ያሉትን ሕገ-መንግሥት የሚያረቁት ከሰው አእምሮ ነው፤ ነገር ግን በቴኦክራሲ ቅርጽ መመሪያው መለኮታዊ ብቻ ነው። “መጅሊስ” مجلس የሚለው የዐረቢኛ ቃል “ሲኖዶስ” σῦνοδος የሚለው የግሪክ ቃል ትርጉማቸው “ምክር ቤት”council” ማለት ነው፤ እዚህ ምክር ቤት ውስጥ ሕገ-መንግሥቱ ሸሪዓህ ነው፤ “ሸሪዓህ” شَرِيعَة የሚለው ቃል “ሺርዓህ” شِرْعَة ማለትም “ሕግ” ከሚለው የስም መደብ የመጣ ሲሆን “ትክክለኛ ሕግ” ማለት ነው፡-
45፥18 *ከዚያም ከነገሩ ከሃይማኖት “በትክክለኛይቱ ሕግ” ላይ አደረግንህ*፡፡ ثُمَّ جَعَلْنَاكَ عَلَىٰ شَرِيعَةٍ مِّنَ الْأَمْرِ
5፥48 *ከእናንተ ለሁሉም ሕግን እና መንገድን አደረግን*፡፡ لِكُلٍّ جَعَلْنَا مِنكُمْ شِرْعَةً وَمِنْهَاجًا

አላህ ለሁሉም መልእክተኞች “ሕግ” እና “መንገድ” አድርጓል፤ “መንገድ” ተብሎ የተቀመጠው ቃል “ሚንሃጅ” مِنْهَاج ማለትም “ፋና” ማለት ሲሆን “መንሃጅ” منهاج የሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ይህ ሕግ የሚዋቀረው ውቅር አራት ሲሆኑ፤ እነርሱም፡-
1ኛ. “ቁርአን” قرآن ማለትም የአላህ ቃል፣
2ኛ. “ሡናህ” سنة የነብያችን”ﷺ” ሰሒህ ሐዲስ፣

3ኛ. “ቂያሥ” قياس “ማመጣጠን”Analogy”
4ኛ. “ኢጅማዕ” إجماع ማለትም የዐሊሞች ስብስብ ናቸው።
ስለዚህ ፍርድ ከአላህ በወረደው ሕግ ይፈረዳል፦
5፥48 *በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ*:: فَاحْكُم بَيْنَهُم بِمَا أَنزَلَ اللَّه

“ፍረድ” ለሚለው ቃል የተጠቀመበት “ፈሕኩም” مْحُكْفَ ሲሆን “ሑክም” ለሚለው የግስ መደብ ነው፤ “ሑክም” حُكْم የሚለው ቃል”ሐከመ” حَكَمَ ማለትም “ፈረደ” የመጣ ሲሆን ፍርድ” ወይም “ሕግ” ማለት ነው። ለምድራችን የሚያስፈልጋት ዛሬ ቴአክራሲ ነው። የኩፍር ፓለቲካ ውስጥ መግባት ለዐማው ውድቀት እንጂ ልምላሜ የለም። ይህንን ከታሪክ መማር አለብን።

ከምን ጊዜ በላይ ዛሬ በኩፍር ፓለቲካ ስለ ሰላም ተሰብኳል ግን ሰፊ የእርስ በርስ ጦርነት አለ። ከምን ጊዜ በላይ ዛሬ በኩፍር ፓለቲካ ስለ አንድነት ተሰብኳል ግን ሰፊ ልዩነት አለ። ከምን ጊዜ በላይ ዛሬ በኩፍር ፓለቲካ ስለ ይቅርታ ተሰብኳል ግን ሰፊ ቂምና ቁርሾ አለ። ከምን ጊዜ በላይ ዛሬ በኩፍር ፓለቲካ ስለ ፍትሕ ተሰብኳል ግን ሰፊ በደል አለ። ከምን ጊዜ በላይ ዛሬ በኩፍር ፓለቲካ ስለ ሁለንተናዊነት ተሰብኳል ግን ሰፊ ዘረኝነት አለ። ከምን ጊዜ በላይ ዛሬ በኩፍር ፓለቲካ ስለ መዋለ ንዋይ ተሰብኳል ግን ሰፊ ድህነት አለ።
ሰው በጨረቃ ላይ ይሄዳል ግን በጨለማ ያለ ስጋት መሄድ አይችልም። ሰው መዋቅራዊና እና አርክቴክታዊ ንድፍ ያላቸው የተንጣለለ ቤት ውስጥ ይኖራል ግን የቤተሰብና የትዳር መፈራረስ አላስቆመም። ሰው የመገናኛ ብዙሃን መረብ ይጠቀማል ግን መግባባት አይችልም።
በምድሪቱ ላይ ረሃብ ያለው ምግብ ታጥቶ አሊያም ለእህል የሚሆን ተስማሚ የእርሻ ቦታ ታጥቶ ሳይሆን ከፋት፣ ጭካኔ፣ ስግብግብነት፣ ጥላቻ ስላለ ነው። በምድሪቱ ላይ ድህነት ያለው 80% የሚሆነውን የምድራችን ሃብት 20% የሚሆኑ የምድራችም ሃብታሞች በሞኖፓልና በስግብግብነት ስለያዙት ነው። ከኩፍር ፓለቲካ ጀርባ ሆነው ዓለምን እየመሩ ያሉት ቴምፕላርስ፣ ፍሪ ሜሶንና ኢሉሚናቲ ናቸው። እነዚህ ደግሞ ለመሢሑል ደጃል መንገድ የሚጠርጉ ናቸው።
ትክክለኛ ሰላም፣ አንድነት፣ ይቅርባይነት፣ ፍትሕ፣ ሁለንተናዊነት እና መዋለ ንዋይ የሚመጣው በመለኮታዊ ሕግ የሚመራው ቴአክራሲ ሲመጣ ነው። በነቢያችን”ﷺ” ፋና እንደገና የኺላፋህ ሥርዓት ይመለሳል። ያኔ ምድሪቱ ታርፋለች።

ሐዲድ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

57፥25 መልክተኞቻችንን በግልጽ ማስረጃዎች በእርግጥ ላክን:: ሰዎችም በትክክል ቀጥ እንዲሉ መጽሐፎችን እና ሚዛንን ወደ እነርሱ አወረድን፥ *”ብረትንም በውስጡ ብርቱ ኀይልና ለሰዎችም መጠቃቀሚያዎች ያሉበት ሲኾን አወረድን”*:: لَقَدْ أَرْسَلْنَا رُسُلَنَا بِالْبَيِّنَاتِ وَأَنزَلْنَا مَعَهُمُ الْكِتَابَ وَالْمِيزَانَ لِيَقُومَ النَّاسُ بِالْقِسْطِ ۖ وَأَنزَلْنَا الْحَدِيدَ فِيهِ بَأْسٌ شَدِيدٌ وَمَنَافِعُ لِلنَّاس

አምላካችን አላህ”ﷻ” ወደ ነቢያችን”ﷺ” መጽሐፍ እና ሚዛን አውርዷል፦
42፥17 አላህ ያ *”መጽሐፉን በእውነት ያወረደ ነው:: ሚዛንንም እንደዚሁ*”:: ሰዓቲቱ ምንአልባት ቅርብ መኾንዋን ምን ያሳውቅሃል? ٱللَّهُ ٱلَّذِىٓ أَنزَلَ ٱلْكِتَٰبَ بِٱلْحَقِّ وَٱلْمِيزَانَ ۗ وَمَا يُدْرِيكَ لَعَلَّ ٱلسَّاعَةَ قَرِيب

ይህም መጽሐፍ እና ሚዛን ቁርኣን ነው፥ መጽሐፍ እና ሚዛን የቁርኣን ስሞች ናቸው። ለምሳሌ ተውራት መጽሐፍ እና ፉርቃንን ተብሏል፦
2፥53 ሙሳንም *”መጽሐፍን እና ፉርቃንንም”* ትመሩ ዘንድ በሰጠነው ጊዜ አስታውሱ:: وَإِذْ ءَاتَيْنَا مُوسَى ٱلْكِتَٰبَ وَٱلْفُرْقَانَ لَعَلَّكُمْ تَهْتَدُون

“ሚዛን” مِيزَان እውነትን ከሐሰት፣ ትክክለኛውን ከስህተት፣ ሰናዩን ከእኩይ የምንለይበት መመዘኛ ነው። ይህ መመዘኛ አምላካችን አላህ”ﷻ” ወደ መልእክኞቹ አውርዷል፦

57፥25 መልክተኞቻችንን በግልጽ ማስረጃዎች በእርግጥ ላክን፡፡ ሰዎችም በትክክል ቀጥ እንዲሉ *"መጽሐፎችን እና ሚዛንን ወደ እነርሱ አወረድን፥ ብረትንም በውስጡ ብርቱ ኀይልና ለሰዎችም መጠቃቀሚያዎች ያሉበት ሲኾን አወረድን"*፡፡ لَقَدْ أَرْسَلْنَا رُسُلَنَا بِالْبَيِّنَاتِ وَأَنزَلْنَا مَعَهُمُ الْكِتَابَ وَالْمِيزَانَ لِيَقُومَ النَّاسُ بِالْقِسْطِ ۖ وَأَنزَلْنَا الْحَدِيدَ فِيهِ بَأْسٌ شَدِيدٌ وَمَنَافِعُ لِلنَّاس

"ሐዲድ" حَدِيد የሚለው ቃል በቁርኣን 6 ጊዜ የመጣ ሲሆን "ብረት"Iron" ማለት ነው። "ሐዲድ" የ 57ኛው ሱራ ስም ነው፥ ይህ ሱራ ላይ አምላካችን አላህ"ﷻ"፡- "ብረትንም በውስጡ ብርቱ ኀይልና ለሰዎችም መጠቃቀሚያዎች ያሉበት ሲኾን አወረድን" በማለት ይናገራል። ታዲያ ይህ ብረት ከየት ነው የወረደው? ስንል "አንዘልና" أَنزَلْنَا ማለትም "አወረድን" የሚለው ቃል "ገለጥን" ወይም "ሰጠን" በሚል ይመጣል፡-
7፥26 የአዳም ልጆች ሆይ! *"ኀፍረተ ገላችሁን የሚሸሸግን ልብስ ጌጥንም በእርግጥ በእናንተ ላይ አወረድን"*፡፡ አላህን የመፍራትም ልብስ ይህ የተሻለ ነው፡፡ ይህ ከአላህ ታምራቶች ነው፡፡ ይገሠጹ ዘንድ አወረደላቸው፡፡ يَا بَنِي آدَمَ قَدْ أَنزَلْنَا عَلَيْكُمْ لِبَاسًا يُوَارِي سَوْآتِكُمْ وَرِيشًا ۖ وَلِبَاسُ التَّقْوَىٰ ذَٰلِكَ خَيْرٌ ۚ ذَٰلِكَ مِنْ آيَاتِ اللَّهِ لَعَلَّهُمْ يَذَّكَّرُونَ
16፥14 *እርሱም ያ ባሕርን ከእርሱ እርጥብ ስጋን ልትበሉና ከእርሱም "የምትለብሱትን ጌጣጌጥ" ታወጡ ዘንድ የገራ ነው*፡፡ وَهُوَ الَّذِي سَخَّرَ الْبَحْرَ لِتَأْكُلُوا مِنْهُ لَحْمًا طَرِيًّا وَتَسْتَخْرِجُوا مِنْهُ حِلْيَةً تَلْبَسُونَهَا وَتَرَى الْفُلْكَ مَوَاخِرَ فِيهِ وَلِتَبْتَغُوا مِن فَضْلِهِ وَلَعَلَّكُمْ تَشْكُرُون

ልብ አድርግ "ጌጣጌጥ" ከባሕር የሚወጣ ነገር ሲሆን አላህ ለእኛ ስላገራው "አወረድን" ብሎታል እንጂ ከሰማይ መውረድን አያመለክትም፥ እንዲሁ ብረትንም በውስጡ ብርቱ ኀይልና ለሰዎችም መጠቃቀሚያዎች ያሉበት ሲኾን አውርዶታል። የቤት እንስሳ ግመል፣ ከብት፣ ፍየል እና በግ ከእነ ጥንዳቸው ስምንት ሲሆኑ ወርደዋል ይላል፡-
39፥6 ከአንዲት ነፍስ ፈጠራችሁ፡፡ ከዚያም ከእርሷ መቀናጆዋን አደረገ፡፡ *"ለእናንተም ከግመልና ከከብት፣ ከፍየል፣ ከበግ ስምንት ዓይነቶችን ወንድና ሴት "አወረደ"*፡፡ خَلَقَكُم مِّن نَّفْسٍ وَاحِدَةٍ ثُمَّ جَعَلَ مِنْهَا زَوْجَهَا وَأَنزَلَ لَكُم مِّنَ الْأَنْعَامِ ثَمَانِيَةَ أَزْوَاجٍ

"አንዘለ" أَنزَلَ ማለት "አወረደ" ማለት ሲሆን ስምንቱ ጥንድ እንስሳ ወርደዋል ማለት ለሰው ልጆች አገልግሎት ተሰጥተዋል ማለት ከሆነ ብረትም ወረደ ማለት መጠቃቀሚያ ያለበት ሲኾን ለሰው ልጆች አገልግሎት ተሰቷል ማለት ነው። "አንዘለ" أَنزَلَ የሚለው ቃል ደመና ከተሸከመው ሰማይ ዝናብን ለማውረድ ተጠቅሞበታል፡-
6፥99 *"እርሱም ያ ከሰማይ ውኃን ያወረደ ነው፡፡ በእርሱም የነገሩን ሁሉ በቃይ አወጣን*፡፡ وَهُوَ الَّذِي أَنزَلَ مِنَ السَّمَاءِ مَاءً فَأَخْرَجْنَا بِهِ نَبَاتَ كُلِّ شَيْءٍ

"ሠማእ" سَّمَاء ማለትም "ሰማይ" ከላይ ያለውን "ጠፈር"Space" ለማመልከት ከገባ ብረት እራሱ ከጠፈር ሥነ-ፈለካዊ ክስተት"supernova" የመጣ በውስጡ ብርቱ ኀይል እና ለሰዎችም መጠቃቀሚያዎች ያሉበት ነው። የብረት ዑደት"cycle" ከአየር ክልል"atmo-sphere" ወደ ውኃ ክልል"hydro-sphere" ከዚያ ወደ ሕይወት ክልል"bio-sphere" በመቀጠል ወደ ዐለት ክልል"litho-sphere" አርጎ በተለያየ ሁኔታ ያልፋል።
ብርቱ ኀይል እና ለሰዎች መጠቃቀሚያ መባሉ ብረት ካርበን ሲገባበት አስተኔ ብረት"steel" ይሆንና ለመሠረተ-ልማት፣ ለግንባታ፣ ለኤሌትሪክ ወዘተ ይሆናል። በሰውነታችን ውስጥ ፕሮቲንን ለቀይ የደም ሕዋስ የሚያጓጉዘው ይህ የብረት ክምሸት"hemoglobin" ነው፥ በዚህም የአንድ ጎልማሳ አካል 4 ግራም ወይም 0.005% ክብደት ብረት አለው። በሰማያትና በምድር ውስጥ ለምእምናን ሁሉ እርገጠኛ ምልክቶች አሉ፥ ይህንን በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም ውስጥ ያሉትን ምልክቶች ቆመው፣ ተቀምጠውም፣ በጎኖቻቸው ተጋድመውም የሚያስተነትኑ ምንኛ የታደሉ ናቸው? አላህ ከሚያስተነትኑ ባሮቹ ያርገን! አሚን፡-
45፥3 *"በሰማያትና በምድር ውስጥ ለምእምናን ሁሉ እርገጠኛ ምልክቶች አሉ"*፡፡ إِنَّ فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ لَآيَاتٍ لِّلْمُؤْمِنِينَ
3፥19 እነርሱም እነዚያ ቆመው፣ ተቀምጠውም፣ በጎኖቻቸው ተጋድመውም አላህን የሚያወሱ በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያስተነትኑ፡- «ጌታችን ሆይ! ይኸን በከንቱ አልፈጠርከውም፤ ጥራት ይገባህ፤ ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን» የሚሉ ናቸው፡፡ الَّذِينَ يَذْكُرُونَ اللَّهَ قِيَامًا وَقُعُودًا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمْ وَيَتَفَكَّرُونَ فِي خَلْقِ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ رَبَّنَا مَا خَلَقْتَ هَٰذَا بَاطِلًا سُبْحَانَكَ فَقِنَا عَذَابَ النَّارِ

እንስሳት እና ዕፅዋት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኛ በሆነው፡፡

50፥7 *ምድርንም ዘረጋናት፡፡ በእርሷም ውስጥ ጋራዎችን ጣልንባት፡፡ “በውስጧም ከሚያስደስት ጥንድን ሁሉ አበቀልን”*፡፡ وَالْأَرْضَ مَدَدْنَاهَا وَأَلْقَيْنَا فِيهَا رَوَاسِيَ وَأَنبَتْنَا فِيهَا مِن كُلِّ زَوْجٍ بَهِيجٍ

“ዘውጅ” زَوْج የሚለው ቃል “ጥንድ” “ባል” ወይም “ሚስት” ተብሎ ተቀምጧል፡-
58:1 አላህ የዚያችን *በባልዋ* ነገር የምትከራከርህንና ወደአላህ የምታስሙተውን ቃል በእርግጥ ሰማ። قَدْ سَمِعَ ٱللَّهُ قَوْلَ ٱلَّتِى تُجَٰدِلُكَ فِى زَوْجِهَا وَتَشْتَكِىٓ إِلَى ٱللَّهِ وَٱللَّهُ يَسْمَعُ تَحَاوُرَكُمَآ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌۢ بَصِيرٌ
7:19 አዳምም ሆይ! አንተም *ሚስትህም* ከገነት ተቀመጡ፤ وَيَٰٓـَٔادَمُ ٱسْكُنْ أَنتَ وَزَوْجُكَ ٱلْجَنَّةَ فَكُلَا مِنْ حَيْثُ شِئْتُمَا وَلَا تَقْرَبَا هَٰذِهِ ٱلشَّجَرَةَ فَتَكُونَا مِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ
35:11 አላህም ከዐፈር፣ ከዚያም ከፍትወት ጠብታ ፈጠራችሁ፤ *ከዚያም ጥንዶች አደረጋችሁ*፤ وَٱللَّهُ خَلَقَكُم مِّن تُرَابٍۢ ثُمَّ مِن نُّطْفَةٍۢ ثُمَّ جَعَلَكُمْ أَزْوَٰجًا
53:45 እርሱም *ሁለቱን ዓይነቶችን ወንድ እና ሴትን ፈጠረ*። وَأَنَّهُۥ خَلَقَ ٱلزَّوْجَيْنِ ٱلذَّكَرَ وَٱلْأُنثَىٰ

“ዘውጀይኒ” زَّوْجَيْنِ ሙተና ሲሆን ሁለት የወንድ እና የሴት ዓይነቶች በሚል መጥቷል፤ “ባልዋ” ለሚለው ቃል የገባው “ዘውጂሃ” زَوْجِهَا መሆኑ እና “ሚስትህ” ለሚለው ቃል የገባው ደግሞ “ዘውጅከ” زَوْجُكَ መሆኑ አንባቢ ልብ ይለዋል። እዚህ ድረስ ከተግባባን አምላካችን አላህ ለእኛ ከምድር ጥንድ ጥንድ የሆኑ ፍጥረታትን ፈጥሮልናል፡-
50፥7 *ምድርንም ዘረጋናት፡፡ በእርሷም ውስጥ ጋራዎችን ጣልንባት፡፡ “በውስጧም ከሚያስደስት ጥንድን ሁሉ አበቀልን”*፡፡ وَالْأَرْضَ مَدَدْنَاهَا وَأَلْقَيْنَا فِيهَا رَوَاسِيَ وَأَنبَتْنَا فِيهَا مِن كُلِّ زَوْجٍ بَهِيجٍ

እዚህ አንቀጽ ላይ “ዓይነት” ተብሎ የተቀመጠው ቃል “ዘውጅ” زَوْج ሲሆን “ጥንድ” ማለት ነው። ለእኛ የተፈጠሩት እነዚህም ጥንድ ጥንድ የሆኑ ፍጥረታት እንስሳት እና ዕፅዋት ናቸው። እስቲ ይህንን እሳቤ ነጥብ በነጥብ እንመልከት፡-

ነጥብ አንድ
“እንስሳት”
እንስሳት ከምድር የተፈጠሩ መነሻቸው ውኃ የሆኑ ፍጥረታት ናቸው፡-
24፥45 *”አላህም ተንቀሳቃሽን ሁሉ ከውሃ ፈጠረ፡፡ ከእነርሱም በሆዱ ላይ የሚኼድ አለ፤ ከእነሱም በሁለት እግሮች ላይ የሚኼድ አለ፡፡ አላህ የሚሻውን ሁሉ ይፈጥራል”*፡፡ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና፡፡ وَاللَّهُ خَلَقَ كُلَّ دَابَّةٍ مِّن مَّاءٍ ۖ فَمِنْهُم مَّن يَمْشِي عَلَىٰ بَطْنِهِ وَمِنْهُم مَّن يَمْشِي عَلَىٰ رِجْلَيْنِ وَمِنْهُم مَّن يَمْشِي عَلَىٰ أَرْبَعٍ ۚ يَخْلُقُ اللَّهُ مَا يَشَاءُ ۚ إِنَّ اللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ
42፥11 ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ ነው፡፡ ከራሳችሁ ጥንዶችን፣ *ከቤት እንስሳዎችም ጥንዶችን ለእናንተ አደረገላችሁ*፡፡ በእርሱ ያበዛችኋል፡፡ የሚመስለው ምንም ነገር የለም፡፡ እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው፡፡ فَاطِرُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۚ جَعَلَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَاجًا وَمِنَ الْأَنْعَامِ أَزْوَاجًا ۖ يَذْرَؤُكُمْ فِيهِ ۚ لَيْسَ كَمِثْلِهِ شَيْءٌ ۖ وَهُوَ السَّمِيعُ الْبَصِير

“ከቤት እንስሳዎችም ጥንዶችን ለእናንተ አደረገላችሁ” የሚለው ሃይለ-ቃል ይሰመርበት። አሁንም “አዝዋጅ” أَزْوَاج ተብሎ የተቀመጠው ቃል ” ዘውጅ” زَوْج ለሚለው ቃል ብዜት ሲሆን “ጥንዶች” ማለት ነው፤ እንስሳት የጾታ ጥንዶች እንደሆኑም እሙንና ቅቡል ነው። በእነዚህ እንስሳ ላይ ሰው ባለቤት እና ንጉሥ ነው፡-
36፥71 እኛ እጆቻችን ከሠሩት *”ለእነርሱ እንስሳዎችን መፍጠራችንን አያውቁምን? እነርሱም ለእርሷ ባለ መብቶች ናቸው”*፡ أَوَلَمْ يَرَوْا أَنَّا خَلَقْنَا لَهُم مِّمَّا عَمِلَتْ أَيْدِينَا أَنْعَامًا فَهُمْ لَهَا مَالِكُون ፡

“ባለ መብት” ተብሎ የተቀመጠው ቃል “ማሊክ” مَٰلِك ማለትም “ባለቤት”owner” ማለት ሲሆን ሚምን በሁለት ሃረካት ሲሳብ ሚም ፈትሃ አሊፍ ስኩን “ማ” مَا ብሎ ሲቀራው “ባለቤት”owner” ይሆናል፤ እንዲሁ “መሊክ”مَلِيك ብሎ ሚምን ባለ አንድ ሃረካ ተስቦ ሚም ፈትሃ “መ” ብሎ مَ ሲቀራ “ንጉሥ”king” ይሆናል። ወደ ነጥቡ ስንገባ ሰው የእንስሳት “ንጉሥ” “ባለቤት” “ባለመብት” መሆኑን ነው።

ነጥብ ሁለት
“ዕፅዋት”
ዕፅዋትም ከምድር የተፈጠሩ መነሻቸው ውኃ የሆኑ ፍጥረታት ናቸው፡-
50፥9 *”ከሰማይም ብሩክን ውሃ አወረድን፡፡ በእርሱም አትክልቶችንና የሚታጨድን ፍሬ አበቀልን”*፡፡ وَنَزَّلْنَا مِنَ السَّمَاءِ مَاءً مُّبَارَكًا فَأَنبَتْنَا بِهِ جَنَّاتٍ وَحَبَّ الْحَصِيدِ
15፥19 ምድርንም ዘረጋናት፡፡ በውስጧም ኮረብታዎችን ጣልናባት፡፡ *”በውስጧም የተለካን በቃይ ሁሉ አበቀልንባት”*፡፡ وَالْأَرْضَ مَدَدْنَاهَا وَأَلْقَيْنَا فِيهَا رَوَاسِيَ وَأَنبَتْنَا فِيهَا مِن كُلِّ شَيْءٍ مَّوْزُونٍ

ዕፅዋት ልክ እንደ እንስሳት የተባእት እና የእንስት ህዋስ”gamete” ያመነጫሉ። አላህ በዕፅዋት መካከል ጥንድ የሆኑ ተቃራኒ ጸታዎች እንዳሉ ለማመልከት “ዘውጂይኒ” ﺯَوْجَيْنِ በማለት ይናገራል፡-
13፥3 እርሱም ያ ምድርን የዘረጋ በእሷም ተራራዎችን እና ወንዞችን ያደረገ *በውስጧም ከፍሬዎች ሁሉ ሁለት ሁለት ጥንዶችን ያደረገ ነው*፡፡ ሌሊትን በቀን ይሸፍናል፡፡ *በዚህም ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ታምራቶች አሉ*፡፡ وَهُوَ الَّذِي مَدَّ الْأَرْضَ وَجَعَلَ فِيهَا رَوَاسِيَ وَأَنْهَارًا ۖ وَمِن كُلِّ الثَّمَرَاتِ جَعَلَ فِيهَا زَوْجَيْنِ ۖ يُغْشِي اللَّيْلَ النَّهَارَ ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ

“ኩል” ﻛُﻞ ማለትም “ሁሉ” የሚለው ቃል ፍጹማዊ “Absolute” ሆኖ ሲመጣ “ሙጥለቅ” مطلق ሲባል በአንጻራዊ “Relative” ሆኖ ሲመጣ ደግሞ “ቀሪብ” قريب ይባላል። እዚህ አንቀጽ ላይ ቀሪብ ሆኖ የመጣ ነው። ነቢያችን”ﷺ” በተላኩበት ጊዜ ላይ ዕፅዋት ጸታ አላቸው ብሎ ማንም ሰው ዐያውቅም ነበር፥ በዚህ ጊዜ አምላካችን አላህ ሁሉን ዐዋቂ በመሆኑ “ዘውጂይኒ” በማለት ዕፅዋት ጥንዶች እንደሆኑ ነግሮናል። በተጨማሪም ይህንንም እሳቤ ቁርኣን በወረደበት ጊዜ ዐለማወቃችንንም ለማመልከት፡- “ከማያውቁትም ነገር ጥንዶችን ሁሏንም የፈጠረ ጥራት ይገባው” በማለት በሦስተኛ መደብ እራሱ ይናገራል፡-
36፥36 ያ ምድር ከምታበቅለው ከራሶቻቸውም *ከማያውቁትም ነገር ጥንዶችን ሁሏንም የፈጠረ ጥራት ይገባው*፡፡ سُبْحَانَ الَّذِي خَلَقَ الْأَزْوَاجَ كُلَّهَا مِمَّا تُنبِتُ الْأَرْضُ وَمِنْ أَنفُسِهِمْ وَمِمَّا لَا يَعْلَمُونَ

አምላካችን አላህ ጊዜው ሲደርስ በ 19ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ታምራት ይሆን ዘንድ ዕፅዋት ጸታ እንዳላቸው ዐሳውቆናል። “ጋይኒ” γυνή ማለት “ሴቴ” ማለት ሲሆን ይህቺ የዕፅዋት እንቁላል ህዋስ”gynoecious” በሥነ-ሕይወት ጥናት “ካርፔልስ”carpels” ትባላለች፥ “አንድሮ” ἀνήρ ማለት “ወንዴ” ማለት ሲሆን የዕፅዋት የዘር ህዋስ”Androecium” በሥነ-ሕይወት ጥናት “ስቴመንስ”stamens” ይባላል።

እንግዲህ እንስሳት እና ዕፅዋት ከምድር የተፈጠሩ መነሻቸው ውኃ የሆኑ ፍጥረታት መሆናቸውን ካየን ዘንዳ የተፈጠሩበት አላማ ለሰው መደሰቻ ነው፡-
2፥29 *”እርሱ ያ በምድር ያለውን ሁሉ ለእናንተ የፈጠረ ነው”*፡፡ هُوَ الَّذِي خَلَقَ لَكُم مَّا فِي الْأَرْضِ جَمِيعًا
50፥7 *ምድርንም ዘረጋናት፡፡ በእርሷም ውስጥ ጋራዎችን ጣልንባት፡፡ “በውስጧም ከሚያስደስት ጥንድን ሁሉ አበቀልን”*፡፡ وَالْأَرْضَ مَدَدْنَاهَا وَأَلْقَيْنَا فِيهَا رَوَاسِيَ وَأَنبَتْنَا فِيهَا مِن كُلِّ زَوْجٍ بَهِيجٍ

በባይብልም ከሄድን እንስሳት እና ዕፅዋት ከምድር የተፈጠሩ መነሻቸው ውኃ የሆኑ ፍጥረታት መሆናቸውን ይናገራል፡-
ዘፍጥረት 1፥20 እግዚአብሔርም አለ፡- *”ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ፥ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ”*።
ዘፍጥረት 1፥24 እግዚአብሔርም አለ፡- *”ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ፥ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደ ወገኑ፥ ታውጣ! እንዲሁም ሆነ”*።
መክብብ 3፥19-20 *”የሰው ልጆች እና የእንስሳ እድል ፈንታ አንድ ነው”*፤ ድርሻቸውም ትክክል ነው፤ አንዱ እንደሚሞት ሌላውም እንዲሁ ይሞታል፤ የሁሉም እስትንፋስ አንድ ነው፤ ሁሉም ከንቱ ነውና ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም። ሁሉ ወደ አንድ ቦታ ይሄዳል፤ *”ሁሉ ከአፈር ነው ሁሉም ወደ አፈር ይመለሳል”*።

ዘፍጥረት 1፥11 እግዚአብሔርም፦ *"ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል! አለ፤ እንዲሁም ሆነ"*።

የፀሐይ መጥለቂያ

ገቢር አንድ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

18፥86 *"ወደ ፀሐይ መግቢያም በደረሰ ጊዜ ጥቁር ጭቃ ባላት ምንጭ ውስጥ ስትጠልቅ አገኛት"*፡፡ حَتَّىٰ إِذَا بَلَغَ مَغْرِبَ ٱلشَّمْسِ وَجَدَهَا تَغْرُبُ فِي عَيْنٍ حَمِئَةٍ

ቀኝና ግራ፣ ታችና ላይ፣ ፊትና ኃላ፣ ውስጥና ውጪ፣ እዚህና እዚያ አንጻራዊ እውነት እንጂ ፍጹማዊ እውነት አይደም፥ እነዚህን ስምንቱን አመላካች አንጻራዊ ነጥብ ይወስነዋል። እንዲሁ ምስራቅና ምዕራብ፣ ሰሜንና ደቡብ አንጻዊ እውነታ ናቸው፦
18፥86 *"ወደ ፀሐይ መግቢያም በደረሰ ጊዜ ጥቁር ጭቃ ባላት ምንጭ ውስጥ ስትጠልቅ አገኛት"*፡፡ حَتَّىٰ إِذَا بَلَغَ مَغْرِبَ ٱلشَّمْسِ وَجَدَهَا تَغْرُبُ فِي عَيْنٍ حَمِئَةٍ

"መግሪብ" مَغْرِب የሚለው ቃል "ገረበ" غَرَبَ ማለትም "ገባ" "ጠለቀ" "ተሰወረ" ከሚል ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን "መግቢያ" "መጥለቂያ" "መሰወሪያ" ማለት ነው። ከመነሻው ፀሐይ በፍጹማዊ እውነታ መግቢያና መውጫ የላትም፥ ከእኛ እይታ አንጻር የምትገባ እና የምትወጣ ስለሚመስለን ነው። ይህንን ከተረዳን እዚህ አንቀጽ ላይ "ስትጠልቅ" ለሚለው ቃል የገባው "ተግሩቡ" تَغْرُبُ ሲሆን "አል-ሙዷሪዕ" ٱلْمُضَارِع ነው። ስለዚህ ፀሐይ የጠለቀችው ለዙል-ቀርነይን ሲያያት እንጂ ቃል በቃል ፀሐይ አትጠቅም፤ አትወጣም። "ሐሚአህ" حَمِئَة ማለት "ጥቁር ጭቃ" ማለት ሲሆን ዙል-ቀርነይን ባደረገው ጉዞ ሜድትራትንያን ባሕር ውስጥ ስትገባ ታየችው፥ "ወጀደ" وَجَدَ ማለት "አገኘ" ማለት ሲሆን ጥቁር ጭቃ ባላት ምንጭ ውስጥ ስትጠልቅ እንዳያት ሁሉ ሕዝቦች ላይ ስትወጣ አገኛት፦
18፥90 *"ወደ ፀሐይ መውጫ በደረሰም ጊዜ ለእነርሱ ከበታችዋ መከለያን ባላደረግንላቸው ሕዝቦች ላይ ስትወጣ አገኛት"*፡፡ حَتَّىٰ إِذَا بَلَغَ مَطْلِعَ الشَّمْسِ وَجَدَهَا تَطْلُعُ عَلَىٰ قَوْمٍ لَّمْ نَجْعَل لَّهُم مِّن دُونِهَا سِتْرًا

"መጥሊዕ" مَطْلِع የሚለው ቃል "ጠለዐ" طَلَعَ ማለትም "ወጣ" "ተገለጠ" ከሚል ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን "መውጫ" "መገለጫ" ማለት ነው። አሁንም "አገኘ" ለሚለው የተጠቀመበት ቃል "ወጀደ" وَجَدَ እንደሆነ አስተውል። ስትወጣ ለእነርሱ ከበታችዋ መከለያን በተደረገላቸው ሕዝቦች ላይ አንጻራዊ ከሆነ እንግዲያውስ ጥቁር ጭቃ ባላት ምንጭ ውስጥ ስትጠልቅ ማየቱ አንጻራዊ ነው። መውጣቷ ላይ "ዐላ" عَلَىٰ የሚለው መስተዋድድ አንጻራዊነትን እንደሚሳይ ሁሉ መግባቷ ላይም "ፊ" فِي የሚለው መስተዋድድ አንጻራዊነትን ያሳያል። እዚህ አንቀጽ ላይ "ስትወጣ" ለሚለው ቃል የገባው "ተጥሉዑ" تَطْلُعُ ሲሆን "አል-ሙዷሪዕ" ٱلْمُضَارِع ነው። ስለዚህ ፀሐይ የወጣችው ለዙል-ቀርነይን ሲያያት እንጂ ቃል በቃል ፀሐይ እንደማትወጣ ሁሉ ቃል በቃልም አትገባም።
እዚህ ድረስ ከተግባባን ሁለት ናሙና ከባይብል እንይ፦
ኢያሱ 1፥1 እንዲህም ሆነ፤ የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ከሞተ በኋላ *እግዚአብሔር የሙሴን አገልጋይ የነዌን ልጅ ኢያሱን እንዲህ ብሎ ተናገረው*፦
ኢያሱ 1፥4 ከምድረ በዳው ከዚህም ከሊባኖስ ጀምሮ እስከ ታላቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ድረስ የኬጥያውያን ምድር ሁሉ *"እስከ ፀሐይ መግቢያ እስከ ታላቁ ባሕር ድረስ"* ዳርቻችሁ ይሆናል።

እዚህ አንቀጽ ላይ ታላቁ ባሕር የፀሐይ መግቢያ እንደሆነ ይናገራል። ታዲያ የፀሐይ መግቢያ ታላቁ ባሕር ነውን? አይ “ይህ የተናገረው ኢያሱ ነው” እንዳትሉ “እግዚአብሔር የሙሴን አገልጋይ የነዌን ልጅ ኢያሱን እንዲህ ብሎ ተናገረው” በማለት ይህንን የሚናገረው እግዚአብሔር መሆኑን ዐውዱ አስረግጦና ረግጦ ያስረዳል። ይህ ታላቁ ባሕር የሜዲትራኒያን ባሕር ነው፥ ኢያሱ ከነበረበት ከምድረ በዳው ከሊባኖስ አንጻር የተነገረ እንጂ ቃል በቃል ፀሐይ ታላቁ ባሕር ውስጥ በፍጹም አትገባም” ከተባለ እንግዲያውስ ከላይ ያለውን የቁርአን አንቀጽ በዚህ ልክና መልክ ተረዱት፡-
1 ነገሥት 22፥36 *”በሠራዊቱም መካከል ፀሐይ ስትገባ”*፡- ንጉሡ ሞቶአልና እያንዳንዱ ወደ ከተማው፥ እያንዳንዱም ወደ አገሩ ይሂድ፡ የሚል ጩኸት ሆነ።

“በሠራዊቱም መካከል ፀሐይ ስትገባ” የሚለው ይሰመርበት። በሠራዊት መካከል ፀሐይ ቃል በቃል ትገባለችን? እረ ይህ የሰው እይታ እንጂ ነባራዊ እውነታ አይደለም” ካላችሁ እንግዲያውስ ከላይ ያለውን የቁርአን አንቀጽ በዚህ ስሌትና ቀመር ተረዱት።

[የፀሐይ መጥለቂያ]

ገቢር ሁለት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

36፥38 *ፀሐይም ለእርሷ ወደ ሆነው መርጊያ ትሮጣለች፡፡ ይህ የአሸናፊው የዐዋቂው አምላክ ውሳኔ ነው*፡፡ وَالشَّمْسُ تَجْرِي لِمُسْتَقَرٍّ لَّهَا ۚ ذَٰلِكَ تَقْدِيرُ الْعَزِيزِ الْعَلِيمِ

ሚሽነሪዎች ቁርአንን ለመተቸት ሱሪ ባንጌ ካሉ ሰነባበቱ፥ እኛ ደግሞ እግር እራስን እንደማያክ እናሳያቸዋለን። እስቲ የሚተቹበትን ሐዲሱን እንመልከት፡-
ሡነን አቢ ዳውድ መጽሐፍ 32, ሐዲስ 34
አቢ ዘር እንደተረከው፡- “ፀሐይ ስትጠልቅ የአላህ መልክተኛ”ﷺ” በአህያ ላይ ተንቆናጠው ሳለ በአጠገባቸው ተቀምጬ ነበር። *”እርሳቸውም :-”እርሷ ወደየት እንደምትገባ ታውቃለህን? አሉ። እኔም፡- “አላህ እና መልእክተኛው የበለጠ ያውቃሉ” አልኩኝ። እርሳቸውም፡- “በሞቀ ውኃ ምንጭ ውስጥ ትገባለች” አሉ”*። عَنْ أَبِي ذَرٍّ، قَالَ كُنْتُ رَدِيفَ رَسُولِ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم وَهُوَ عَلَى حِمَارٍ وَالشَّمْسُ عِنْدَ غُرُوبِهَا فَقَالَ ” هَلْ تَدْرِي أَيْنَ تَغْرُبُ هَذِهِ ” . قُلْتُ اللَّهُ وَرَسُولُهُ أَعْلَمُ . قَالَ ” فَإِنَّهَا تَغْرُبُ فِي عَيْنٍ حَامِيَةٍ

እዚህ ሐዲስ ላይ “ሓሚያህ” ةَحَامِيَ ማለት “ሙቅ ውኃ” ማለት እንጂ ጥቁር ጭቃ ማለት አይደለም። “ጥቁር ጭቃ” ለማለት ከፈለጋችሁ “ሐሚአህ” حَمِئَة ነው። ሓሚያህ ከዐርሽ ሥር ያለ ውኃ ነው፡-
11፥7 *”እርሱም ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ ነው፡፡ ዐርሹም በውሃ ላይ ነበር”*፡፡ وَهُوَ الَّذِي خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ فِي سِتَّةِ أَيَّامٍ وَكَانَ عَرْشُهُ عَلَى الْمَاءِ
ኢማም ቡኻሪይ መጽሐፍ 59, ሐዲስ 2
ዒምራም ኢብኑ ሑሰይን እንደተረከው፡- “ነቢዩም”ﷺ” አሉ፡- *”በመጀመሪያ ምንም ነገር ሳይኖር አላህ ነበረ፣ ከዚያ ዙፋኑን በውኃ ላይ ነበረ፣ ከዚያ ሁሉን ነገር ጻፈ፣ ከዚያ ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ”*። عَنْ عِمْرَانَ بْنِ حُصَيْنٍ، قَالَ إِنِّي عِنْدَ النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم كَانَ اللَّهُ وَلَمْ يَكُنْ شَىْءٌ غَيْرُهُ، وَكَانَ عَرْشُهُ عَلَى الْمَاءِ، وَكَتَبَ فِي الذِّكْرِ كُلَّ شَىْءٍ، وَخَلَقَ السَّمَوَاتِ وَالأَرْضَ

እዚህ ድረስ ከተግባባን “በሞቀ ውኃ ምንጭ ውስጥ ትገባለች” የሚለውን በኢማም ቡኻርይ ላይ “ከዐርሽ ሥር እስክትሰግድ ድረስ ትጓዛለች” ተብሎ በደንብ ተፈሥሯል፡-
ኢማም ቡኻርይ መጽሐፍ 65, ሐዲስ 4802
አቢ ዘር”ረ.ዐ” እንደተረከው፡- “አንድ ጊዜ ፀሐይ ስትጠልቅ ከነቢዩ”ﷺ” በመሥጂድ ሆኜ ሳለ፥ *”እርሳቸውም :-”አቢ ዘር ሆይ! እርሷ ወደየት እንደምትገባ ታውቃለህን? አሉ። እኔም፡- “አላህ እና መልእክተኛው የበለጠ ያውቃሉ” አልኩኝ። እርሳቸውም፡- “ከዐርሽ ሥር እስክትሰግድ ድረስ ትጓዛለች፥ ይህ የአላህ ንግግር ነው፡- “ፀሐይም ለእርሷ ወደ ሆነው መርጊያ ትሮጣለች፡፡ ይህ የአሸናፊው የዐዋቂው አምላክ ውሳኔ ነው”*።

عَنْ أَبِي ذَرٍّ ـ رضى الله عنه ـ قَالَ كُنْتُ مَعَ النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم فِي الْمَسْجِدِ عِنْدَ غُرُوبِ الشَّمْسِ فَقَالَ " يَا أَبَا ذَرٍّ أَتَدْرِي أَيْنَ تَغْرُبُ الشَّمْسُ ". قُلْتُ اللَّهُ وَرَسُولُهُ أَعْلَمُ. قَالَ " فَإِنَّهَا تَذْهَبُ حَتَّى تَسْجُدَ تَحْتَ الْعَرْشِ، فَذَلِكَ قَوْلُهُ تَعَالَى {وَالشَّمْسُ تَجْرِي لِمُسْتَقَرٍّ لَهَا ذَلِكَ تَقْدِيرُ الْعَزِيزِ الْعَلِيمِ}"

የሥነ-ፈለክ ጥናት ታሪክን ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት “ምድር የሥርዓተ-ፈለክ እምብርት”Geocentric” ናት” ተብሎ ይታመን ነበር። ነገር ግን በ1533 ድኅረ-ልደት ኒክላስ ኮፐርኒኮስ ምድር ሳትሆን ፀሐይ የሥርዓተ-ፈለክ እምብርት”Heliocentric” ናት” ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ለዓለማችን አዲስ ጥናት አበረከተ። ያ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ፀሐይ ቋሚ እምብርት”stationary” እንጂ ትንቀሳቀሳለች ተብሎ አይታሰብም ነበር። ነገር ግን በ1783 ድኅረ-ልደት ዊሊያም ሃርቸል ፀሐይ በሰከንድ 16.5 ኪሎ ሜትር ትጓዛለች” ብሎ አዲስ ግኝት አመጣ፥ ይህ ጉዞ “ሶላር አፔክስ”solar apex” ይባላል። የምትሄድበትን ቦታ ምሁራን “local standard of rest”(LSR) አሊያም “Galactic Center” ይሉታል። ምሁራን ይህንን ጉዞዋን ሶላር አፔክስ ይበሉት እንጂ ከዐርሽ ሥር ወደላው ውኃ ልትጠልቅ እየተጓዘች እንደሆነ ከላይ ያለው ሐዲስ ያስረዳል። ይህ ከዐርሽ ሥር ያለው ውኃ ለእርሷ “መርጊያ” ተብሏል፡-

36፥38 *ፀሐይም ለእርሷ ወደ ሆነው መርጊያ ትሮጣለች፡፡ ይህ የአሸናፊው የዐዋቂው አምላክ ውሳኔ ነው”*፡፡ وَالشَّمْسُ تَجْرِي لِمُسْتَقَرٍّ لَّهَا ۚ ذَٰلِكَ تَقْدِيرُ الْعَزِيزِ الْعَلِيمِ

በመቀጠል ከሄደችበት ስትመለስ የሚኖራት የጊዜ ፍጥነት በሰከንድ 19.7 ኪሎ ሜትር ነው” ተብሎ በዊሊያም ሃርቸል ተዘክሯል። ይህም ምልሰት “ሶላር አንታፔክስ”solar antapex” ይባላል። ከጠለቀችበት ተመልሳ ስትወጣ ቂያማህ ይቆማል፡-

ኢማም ቡኻርይ መጽሐፍ 59, ሐዲስ 10

አቢ ዘር”ረ.ዐ” እንደተረከው፡- “ነቢዩም”ﷺ” እኔን፡- *”ፀሐይ ወደየት እንደምትገባ ታውቃለህን? አሉ። እኔም፡- “አላህ እና መልእክተኛው የበለጠ ያውቃሉ” አልኩኝ። እርሳቸውም፡- “ከዐርሽ ሥር እስክትሰግድ ድረስ ትጓዛለች፥ ተመልሳ እንድትወጣ ትጠይቃለች”*። عَنْ أَبِي ذَرٍّ ـ رضى الله عنه ـ قَالَ قَالَ النَّبِيُّ صلى الله عليه وسلم لأَبِي ذَرٍّ حِينَ غَرَبَتِ الشَّمْسُ " تَدْرِي أَيْنَ تَذْهَبُ ". قُلْتُ اللَّهُ وَرَسُولُهُ أَعْلَمُ. قَالَ " فَإِنَّهَا تَذْهَبُ حَتَّى تَسْجُدَ تَحْتَ الْعَرْشِ، فَتَسْتَأْذِنَ فَيُؤْذَنَ لَهَا،

ሙሥነድ አሕመድ 21459

አቢ ዘር እንደተረከው፡- “አንድ ቀን ፀሐይ ስትጠልቅ ኮርቻ ወይም ድብዳብ ባለው አህያ ላይ ነቢዩ”ﷺ” ተቀምጠው ሳለ በአጠገባቸው ነበርኩኝ። *”እርሳቸውም ለእኔ፡- “አቢ ዘር ሆይ! ፀሐይ ወደየት እንደምትገባ ታውቃለህን? አሉ። እኔም፡- “አላህ እና መልእክተኛው የበለጠ ያውቃሉ” አልኩኝ። እርሳቸውም፡- “በሞቀ ውኃ ምንጭ ለጌታዋ በዐርሽ ሥር እስክትሰግድ ትገባለች” አሉ። በምትወጣበት ጊዜ አላህ እንድትወጣና እንድትገባ ይፈቅላታል፥ ግን ይዘጋላል። እርሷም፡- “ጌታ ሆይ! ለመጉዝ ረጅም ርቀት አለኝ” ትላለች። አላህም፡- “በጠለቅሽበት ውጪ” ይላታል። 6፥158 “አማኝ ያልኾነችን ነፍስ እምነትዋ ወይም በእምነትዋ ጊዜ በጎ ያልሠራችን ነፍስ ጸጸትዋ አይጠቅማትም”*።

عَنْ أَبِي ذَرٍّ قَالَ : كُنْتُ مَعَ النَّبِيِّ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ عَلَى حِمَارٍ وَعَلَيْهِ بَرْذَعَةٌ أَوْ قَطِيفَةٌ. قَالَ : وَذَلِكَ عِنْدَ غُرُوبِ الشَّمْسِ. فَقَالَ لِي : " يَا أَبَا ذَرٍّ، هَلْ تَدْرِي أَيْنَ تَغِيبُ هَذِهِ ؟ ". قَالَ : قُلْتُ : اللَّهُ وَرَسُولُهُ أَعْلَمُ. قَالَ : " فَإِنَّهَا تَغْرُبُ فِي عَيْنٍ حَامِيَةٍ،تَنْطَلِقُ حَتَّى تَخِرَّ لِرَبِّهَا سَاجِدَةً تَحْتَ الْعَرْشِ، فَإِذَا حَانَ خُرُوجُهَا أَذِنَ اللَّهُ لَهَا فَتَخْرُجُ فَتَطْلُعُ، فَإِذَا أَرَادَ أَنْ يُطْلِعَهَا مِنْ حَيْثُ تَغْرُبُ حَبَسَهَا، فَتَقُولُ : يَا رَبِّ، إِنَّ مَسِيرِي بَعِيدٌ. فَيَقُولُ لَهَا : اطْلُعِي مِنْ حَيْثُ غِبْتِ." فَذَلِكَ حِينَ لَا يَنْفَعُ نَفْسًا إِيمَانُهَا ".

ኢማም ቡኻርይ መጽሐፍ 65, ሐዲስ 4635

አቢ ሁረይራህ”ረ.ዐ” እንደተረከው፡- “የአላህ መልክተኛ”ﷺ” እንዲህ አሉ፡- *”ፀሐይ በጠለቀበት እስክትወጣ ድረስ ሰአቲቱ(ትንሳኤ) አትቆምም”*። حَدَّثَنَا أَبُو هُرَيْرَةَ، رضى الله عنه قَالَ قَالَ رَسُولُ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم " لاَ تَقُومُ السَّاعَةُ حَتَّى تَطْلُعَ الشَّمْسُ مِنْ مَغْرِبِهَا،

የሚያጅበው ሁሉም ስለ ፀሐይ መጥለቅ በተዘገቡት ሐዲስ ላይ ተራኪው አቢ ዘር ነው። ስለዚህ በሐዲሳቱ ላይ የተጠቀሱት የፀሐይ በፀርሽ ሥር ካለው ውኃ መጥለቅ እና ዙልቀርነይን በጥቁር ጭቃ ስትጠልቅ ካያት ጋር ምንም አይነት ተዛምዶ የለውም። “ነቢያችሁ”ﷺ” ፀሐይ የምትጠልቀው ጥቁር ጭቃ ውስጥ ነው ብለዋል” ያላችሁት ቅጥፈት ተጋልጧል። አላህ ሂዳያህ ይስጣቸው፥ ለእኛም ጽናቱን ይስጠን! አሚን።

ምሥራቅ እና ምዕራብ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ፥ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

73፥9 *”እርሱም የምሥራቅና የምዕራብ ጌታ ነው፡፡ ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም፡፡ መጠጊያ አድርገህም ያዘው”*፡፡ رَبُّ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ لَا إِلَـٰهَ إِلَّا هُوَ فَاتَّخِذْهُ وَكِيلًا

“መሸሪቅ” مَشْرِق የሚለው ቃል “ሸረቀ” شَرَق ማለትም “ወጣ” “ታየ” “ተገለጠ” ከሚል ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን “መውጪያ” “መታያ” “መገለጪያ” “ምሥራቅ” ማለት ነው። “መግሪብ” مَغْرِب የሚለው ቃል “ገረበ” غَرَب ማለትም “ገባ” “ጠለቀ” “ተሰወረ” ከሚል ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን “መግቢያ” “መጥለቂያ” “መሰወሪያ” “ምዕራብ” ማለት ነው። ፀሐይ የፕላኔታችን ሥርዓተ-ብርሃን”Solar System” እምብርትና ከህልቆ መሳፍርት ከዋክብት አንዷ የንጋት ኮከብ ናት። ከመነሻው ፀሐይ በፍጹማዊ እውነታ መውጫ እና መግቢያ የላትም፥ ከእኛ እይታ አንጻር የምትወጣ እና የምትገባ ስለሚመስለን ነው። ስለዚህ መውጣትና መግባት አንጻራዊ እውነታ ነው። አምላካችን አላህ እርሱም የምሥራቅና የምዕራብ ጌታ ነው፥ ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም፡-

73፥9 *”እርሱም የምሥራቅና የምዕራብ ጌታ ነው፥ ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም፡፡ መጠጊያ አድርገህም ያዘው”*፡፡ رَبُّ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ لَا إِلَـٰهَ إِلَّا هُوَ فَاتَّخِذْهُ وَكِيلًا

“አደድ” عَدَد ማለት “ቁጥር” ማለት ሲሆን አደድ በሦስት ይከፈላሉ፥ እነርሱም፡- 1ኛ. “ሙፍረድ” مُفْرَد ማለትም “ነጠላ”singular” 2ኛ. “ሙሰና” مُثَنًّى ማለትም “ሁለትዮሽ”dual” 3ኛ. “ጀምዕ” جَمْع ማለትም “ብዜት”plural” ናቸው።

ይህንን ከተረዳን ዘንዳ የመሸሪቅ ሙሰና “መሸሪቀይኒ” مَشْرِقَيْنِ ሲሆን “ሁለቱ ምሥራቆች” ማለት ነው። ፀሐይ በበጋ ጊዜ በሰሜን ንፍቀ-ክበብ”north pole” ስትወጣ አንደኛው መውጫ ይህ ሲሆን በክረምት ጊዜ ደግሞ በደቡብ ንፍቀ-ክበብ”south pole” መውጣቷ ሁለተኛው መውጫ ይህ ነው፥ ሁለቱ ምሥራቆች የሚለው ይህንን ታሳቢና ዋቢ ያደረገ ነው።

የመግሪብ ሙሰና “መግሪበይኒ” مَغْرِبَيْنِ ሲሆን “ሁለቱ ምዕራቦች” ማለት ነው። ፀሐይ በበጋ ጊዜ በሰሜን ንፍቀ-ክበብ”north pole” ስትገባ አንደኛው መግቢያ ይህ ሲሆን በክረምት ጊዜ ደግሞ በደቡብ ንፍቀ-ክበብ”south pole” መግባቷ ሁለተኛው መግቢያ ይህ ነው፥ ሁለቱ ምዕራቦች የሚለው ይህንን ታሳቢና ዋቢ ያደረገ ነው፡-

55፥17 *”የሁለቱ ምሥራቆች ጌታ እና የሁለቱ ምዕራቦችም ጌታ ነው”*፡፡ رَبُّ الْمَشْرِقَيْنِ وَرَبُّ الْمَغْرِبَيْنِ

ታላቁ ሙፈሢ ኢብኑ ከሲር ይህንን አንቀጽ የፈሠረው በዚህ መልኩ ነው፡-

ተፍሢሩል ኢብኑ ከሲር 55፥17

”የሁለቱ ምሥራቆች ጌታ እና የሁለቱ ምዕራቦችም ጌታ ነው” ማለት “የበጋ እና የክረምት የፀሐይ መውጫዎች እና የበጋ እና የክረምት የፀሐይ መጥለቂያዎች” ማለት ነው። አላህ በሌላ አንቀጽ፡- “በምሥራቆችና በምዕራቦችም ጌታ እምላለሁ” አል-መዓሪጅ 40 ፥ ይህ የሚያመላክተው በእያንዳንዱ ቀን ለሰዎች የተለያዩ የፀሐይ መውጫዎች እና የፀሐይ መጥለቂያዎች ቦታዎች እንዳሉ ነው። አላህ በሌላ አንቀጽ፡- “እርሱም የምሥራቅና የምዕራብ ጌታ ነው፡፡ ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም፡፡ መጠጊያ አድርገህም ያዘው” አል-ሙዘሚል 9 ፥ ይህ የሚያመላክተው የተለያዩ የፀሐይ መውጫዎች እና የፀሐይ መጥለቂያዎች ቦታዎች እንዳሉ እና ይህ ልዩነት ለተፈጠሩት ለጂኒዎችም ሰዎችም ጥቅም ያመጣል”።

رب المشرقين ورب المغربين) يعني مشرقي الصيف والشتاء ، ومغربي الصيف والشتاء . وقال في الآية الأخرى : (فلا أقسم برب المشارق والمغارب) [المعارج : 40] ، وذلك باختلاف مطالع الشمس وتنقلها في كل يوم ، وبروزها منه إلى الناس . وقال في الآية الأخرى : (رب المشرق والمغرب لا إله إلا هو فاتخذه وكيلا) [المزمل : 9] . وهذا المراد منه جنس المشارق والمغارب ، ولما كان في اختلاف هذه المشارق والمغارب مصالح للخلق من الجن والإنس

እውነት ነው! አሜሪካ የፀሐይ መውጫ እና መጥለቂያ ከኢትዮጵያ፥ የኢትዮጵያ ከአውሮፓ፣ የአውሮፓ ከሩቅ ምሥራቅ ለየቅል ነው። ለዛ ነው በብዜት “ምሥራቆች እና ምዕራቦች” የተባለው። የመሸሪቅ ጀምዕ “መሻሪቅ” مَشَارِق ሲሆን “ምሥራቆች” ማለት ነው። የመግሪብ ጀምዕ “መጋሪብ” مَغَارِب ሲሆን “ምዕራቦች” ማለት ነው፡-

70፥40 *”በምሥራቆችና በምዕራቦችም ጌታ እምላለሁ፥ እኛ በእርግጥ ቻዮች ነን”*:: فَلَا أُقْسِمُ بِرَبِّ الْمَشَارِقِ وَالْمَغَارِبِ إِنَّا لَقَادِرُون

በተጨማሪም የእኛ የንጋት ኮከብ ፀሐይ ለእኛ ሥርዓተ-ብርሃን መውጣትና መግባት እንዳላት ሁሉ እያንዳንዳቸው ከዋክብትም በራሳቸው ሥርዓተ-ብርሃን ስላላቸው ለእኛ እይታ ላይ መውጣትና መግባት አላቸው። ከዋክብት በሌሊት ይወጣሉ፥ በንጋት ይገባሉ፥ ይህ የእነርሱ መውጫዎችና መግቢያዎች ምሥራቆችና ምዕራቦች ይባላሉ፡-

52፥49 *”ከሌሊቱም አወድሰው፥ በከዋክብት መደበቂያ ጊዜም ላይ አወድሰው”*:: وَمِنَ اللَّيْلِ فَسَبِّحْهُ وَإِدْبَارَ النُّجُومِ

56፥75 *”በከዋክብትም መጥለቂያዎች እምላለሁ”*:: فَلَا أُقْسِمُ بِمَوَاقِعِ النُّجُومِ

89፥15 *”ተመላሾችም በኾኑት እምላለሁ”*:: فَلَا أُقْسِمُ بِالْخُنَّسِ

89፥16 *”ኺያጆች ገቢዎች በኾኑት ከዋክብት”*:: الْجَوَارِ الْكُنَّس

እያንዳንዱ ኮከብ በራሱ ምህዋር እንደሚንቀሳቀስ የሥነ-ፈለክ ተመራማሪዎች በዘመናችን ደርሰውበታል። በዚህ ሪሩያ ዋቢ መጽሐፍት ይመልከቱ፡-

1. Reid, M.J. (1993). “The distance to the center of the Galaxy”.
2. Gillman, M.; Erenler, H. (2008). “The galactic cycle of extinction”.
3. Gregory, S. A. (1998). Introductory Astronomy & Astrophysics.